

መኢአድ በገዥው ፓርቲ
አመራሮች ቃል
እንደተገባለት ገለጸ

*ስንቱን ነገር እንራብ?*
*(እህል ተርበን፣ ሀቅ መስማትን ተርበን፣ እውነት መናገርን ተርበን፣ ...)*

«በስንት መከራ
ያጠመድኩትን አውሬ
አታባሩብኝ» ለማለት ይሆን?

*በደበበ እሸቱ*




# አውራምባ ታይምስ

ለመረጃ ቅርብ ይሁኑ

2ኛ ዓመት ቁጥር 90 | ህዳር 08 ቀን 2002 | ዋጋ 3.50 ብር




*ዶ/ር ያዕቆብ ኃ/ማሪያም፣ የቀድሞ ቅንጅት መሪዎች ሕዝብ ለሰጣቸው ውክልናና ኃላፊነት ብቁ እንዳልነበሩ በማስታወስ «የኢትዮጵያን ሕዝብ ተንበርክከን ይቅርታ ልንጠይቀው ይገባል» ብለዋል:: ከዚህ አንጻር ብዙዎች ወ/ት ብርቱካን ብቻዋን ዋጋ ከፋይ መሆን ይገባታልን ሲሉ ይጠይቃሉ:: መንግስትን ይቅርታ መጠየቅ ህዝብ እግር ላይ መውደቅ መሆኑን ታሳቢ በማድረግ ለብርቱካን ከእስር መፈታት አንድ ብቸኛ አማራጭ አለ::*

12

## ለብርቱካን ከእስር መፈታት ያለው አማራጭ

## «ገመና» የተሰኘው የኢቴቪ ድራማ ቁጣ እየቀሰቀሰ ነው

9



- የእምነት እሴቶቻችን ተንቋሸዋል (የእስልምና እምነት ተከታዮች)
- ፖሊስና ሕብረተሰብ ካቀረበው የበለጠ አላደረግንም (ደራሲው)
- የእምነታችንን ስርአት ማቅረቡ አስፈላጊ አልነበረም (የኢት.እስልምና ጉዳዮች ጠ/ጉባኤ)
- የተጫወትኩት ገጸ-ባህሪ ከቅዱሳን መጻህፍት የሚጠቅስ ሰይጣንን ነው(ተዋናዩ)


**በውስጥ ገፆች**

አንድነት «መርሕ ይከበር» የሚሉ አባላትን ከጽ/ቤቱ በፖሊስ ለማስወጣት ሞከረ

የኮፐንሃገን የአየር ንብረት ለውጥ ጉባዔ ስኬታማ ይሆን?

የድምፃዊት ማንአልሞሽ ዲቦ የደቡብ አፍሪካ ጉዞ እስካሁን አልተሳካም

የኢትዮጵያ የድርቅ አደጋና የመንግስት አቋም





<u>የመገናኛ ብዙሐንና የመረጃ ነጻነት አዋጅ</u>

አጋላጭ የሆኑትን ጨምሮ... በህገ
መንግስቱ የተረጋገጡትን ግልጽ
መንግስታዊ አሰራርና የተጠያቂነትን
እሴቶች ለማዳበርና ይበልጥ ለማጠናከር...





## ጸረ-ሰላምነት ወይስ ልማታዊ ጋዜጠኝነት?

6

# ኤዲቶሪያል

# የግል ሚዲያ የዴሞክራሲ ዋስትና እንጂ ጠላት አይደለም!!

ኢትዮጵያ ፈርማ ከተቀበለቻቸው «የተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብት ሰነዶች አንዱ በዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን አንቀጽ 19 ስር የሚገኘውና ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት የራሱን አስተሳሰብ ስለመያዝ መብቱ የሚደነግገው ክፍል ነው:: ድንጋጌው ሃሳብ በነፃነት የሚገለጽባቸውን የተለያዩ መንገዶች በመብትነት ያጎናፀፈ ሲሆን አጠቃቀሙን አስመልክቶም ግዴታዎችንና ኃላፊነቶችን አካቷል:: ከህግ መሰረታዊ ባህርይ አንፃር የተጣሉት ገደቦች የመብት ድንጋጌውን የተጐናፀፈ ማንኛውም ሰው መብቶቹን ሲጠቀም የሌሎችን መብትና ክብር፣ ብሔራዊ ደህንነትን፣ ሥነ ምግባርንና የመሳሰሉትን በህግ የተደነገጉ ጉዳዮች መጠበቅ እንዳለበት ተዘርዝሯል:: የኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 4 ደግሞ ድንጋጌዎቹን የሚያጠነክርና አስፈላጊው የህግ ጥበቃ የሚደረግበትን አግባብ ይገልፃል::

«ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ሃሳቦችና አመለካከቶች በነፃ መንሸራሸራቸውን ለማረጋገጥ ሲባል ፕሬስ በተቋምነቱ የአሰራር ነፃነትና የተለያዩ አስተያየቶች የማስተናገድ ችሎታ እንዲኖረው የሕግ ጥበቃ ይደረግለታል::» ይላል:: አውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ከተመሰረተችበት ጊዜ ጀምሮ የአገሪቱ ህጎች የሚያጎናጽፏቸውን መብቶች በመጠቀም፣ ኃላፊነቶቹንና ገደቦቹን በማክበር እንዲሁም የተጣሉት ህጋዊ ገደቦች ቢጣሱ የሚያስከትሉትን ተጠያቂነቶች በመገንዘብና የተቋቋመችበትን መረጃ የመስጠት፣ የማስተማርና የማዝናናት ተልዕኮዎች ለማሳካት «ለመረጃ ቅርብ ይሁኑ» የሚል መሪ ቃል አንግባ ስትታተር መቆየቷ ይታወሳል:: ወደፊትም ከአንድ ገለልተኛ ሚዲያ የሚጠበቁ መሰረታዊና ተጨማሪ ኃላፊነቶችን ለመወጣት ዝግጁ ናት::

ማንኛውም ሰው ሰብአዊ በመሆኑ ብቻ የተጎናፀፋቸውን የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች በመጠቀም ዓለም አቀፍ ቃልኪዳኖችም ሆኑ የኢትዮጵያ ህገ መንግስት የሚሰጣቸውን የማይገሰሱ መብቶች በመጠቀም ሙያዊ ተልእኳችንን ለማሳካት የምናደርገው መታተር ግን ግባቸው ተገማች ባልሆኑ አፍራሽ እንቅስቃሴዎች ጫና እየተደረገበት መሆኑን ለኢትዮጵያ ሕዝብና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት ማሳወቅ ግድ የሚለን «ታሪካዊ» አጋጣሚ ላይ እንገኛለን:: በተለይ ይህ አፍራሽ እንቅስቃሴ የመንግስት ዋነኛ የፕሮፓጋንዳ መሳሪያ ከሆነው «አዲስ ዘመን»ጋዜጣ ሲመጣ የተነሳውን ሃሳብ መሰረት ያደረጉ ጉዳዮችን በመመርመር ነባራዊውን ሁኔታ በዚህ መንገድ ማቅረቡ ተገቢ ይሆናል::

እድሜ ጠገቡ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ሕዳር 01 ቀን 2002 ዓ.ም በ69ኛ አመት 61ኛ እትሙ አቋሙን ከሚያንፀባርቅበት የርዕሰ አንቀጽ አምድ ጎን «ቆርኔሊዮስ» የተባሉ ፀሐፊን መጣጥፍ የአዘጋጆቹ ምንም አይነት ሙያዊ አርትኦት ያልዳሰሰው በሚያስመስል መንገድ የተዘጋጀውን

አሳዛኝና አሸማቃቂ ጽሁፍ እንዳለ በማተም አሰራጭቷል:: አዲስ ዘመን የሚያትማቸውን ጽሁፎች ይዘት አስመልክቶ የሚወስነው በመንግስት የተዘጋጀው ኤዲቶሪያል ፓሊሲው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከላይ በተጠቀሰው ዕለት ***«ከድርጊት ዘጋቢነት ይልቅ ወደ ድርጊት አስፈፃሚነት የተለወጡ ጋዜጦችና ጋዜጠኞች»*** በሚል ርዕስ በአውራምባ ታይምስ እና በአዲስ ነገር ጋዜጦች ላይ የቀረበው ጽሁፍ ሃሳብን በነፃነት ከመግለጽ መርህ ይልቅ ከሳሽና ፈራጅ በመሆን በነፃው ፕሬስ ላይ የተቃጣ ስልታዊ ጥቃት ሲሆን የመንግስትን ፖሊሲና እስትራቴጂዎች አበስራለሁ የሚለው 'አዲስ ዘመን ' ጋዜጣ ይህንኑ ጽሁፍ ከርዕስ አንቀጹ ጎን ያለውን ገኸ አምድ በመስጠት አትሞ ማሰራጨቱ የጉዳዩን አደገኝነት ያጎላዋል::

ፀሐፊው እውነተኛ ዘገባንና የፕሮፓጋንዳ ዘዴን እንደባለሙያ በማነፃፀርና ጋዜጣችን ሕዝብን ከሕዝብ ለማቃቃር ሌት ተቀን እየሰራች እንደሆነ በገለፁበት በዚህ አደገኛ ጽሁፋቸው «ጥላቻ» የሚለውን ቃል ብቻ ከ25 ጊዜ በላይ በመደጋገም የጽሁፋቸው መንስኤና የሚጠብቁት ውጤት ምን እንደሆነ አመላክተዋል:: ጥላቻን መንዛት፣ በጠላትነት መፈረጅ፣ ጠላት ነው የሚሉትን ግለሰብ ወይም ቡድን የሚሰጠውን አስተያየት ለማስተናገድ እድል መንፈግ፣ ጥላቻን መቀስቀስ፣ ጥላቻን በማራገብ ሥራ ላይ የተጠመዱ፣ ጥላቻን ማንፀባረቅ፣ ወዘተ ወዘተርፈ የሚሉ አገላለጾችን ከሰይጣናዊ አስተሳሰብ መጠናወት ጋር በማያያዝ ጭምር ለንባብ አብቅተውታል::

በጥላቻ ተጀምሮ በጥላቻ የተቋጨው፤ ይኸው ጽሁፍ ሙያው የሚጠይቅብንንና እንደ አንድ ገለልተኛ የሚዲያ ተቋም እናሳካዋለን የምንለውን ግብ የሚያደናቅፈው ቢሆንም ብዥታዎችን ለማጥራት ስንል በሌላም በኩል ይህ ጽሁፍ የቀረበው ከተዛባ አመለካከት ሊሆንም ይችላል ከሚል በጎ ሃሳብ በመነሳት የአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል በሰባት ነጥቦች ላይ ብቻ አጠር ያሉ ማብራሪያዎችን ለመስጠት ተገዷል::

1. **<u>ርዕሰ አንቀጽ</u>:-** ፀሐፊው «ሰይጣናዊ አስተሳሰብ» ሲሉ ነውረኛ መግለጫ የሰጡበት ርዕሰ አንቀጽ ተንከባክበንና አበልጽገን ለቀጣዩ ትውልድ የምናስተላልፋቸው በሌላ በኩል ደግሞ እንደሕዝብ ልንዋጋቸው ስለሚገቡን ጉዳዮች በማንሳት የውይይት መድረክ የከፈትንበት ነበር:: ተገቢውን እውቅናና ከበሬታ ልንሰጣቸው ስለሚገቡን እሴቶች ሊፈተሹ ስለሚገባቸው የመፍትሄ አማራጮችና ለቀጣዩ ትውልድ ማስረከብ ከሚጠበቅብን ቁሳዊ ኃብት ጋር ታሳቢ መሆን ስላለባቸው መንፈሳዊ እሴቶች ዳሰናል:: እየተፈፀሙ ያሉ ኢ-ፍትሃዊ አሰራሮች፣ ብልሹ አስተዳደሮችንና የስነ ምግባር ዝቅጠትን ኮንነናል:: የፖለቲካ ፓርቲዎች ደጋፊያችንና አባላችን ለሚሉት ግልጽ መሆን እንዳለባቸው፣ የዴሞክራሲ ዋልታዎች መጠበቅ እንደሚገባቸው አቋማችንን ገልፀናል:: ይህ አቋም ለሰይጣን ካልሆነ አገሬን እወዳለሁ ለሚል ዜጋ «ሰይጣናዊ አስተሳሰብ» ሊሆንበት አይችልም::

2. **<u>የምርጫ ስነ ምግባር ደንብና የውጭ ዲፕሎማቶች ውዳሴ</u>:-** ፀሐፊው በቅርቡ የተፈረመው የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ስነ ምግባር ደንብ ታሪካዊና በውጭ ዲፕሎማቶችና ሚዲያዎች ቢወደስም ማቅ ያለበሰ ሃዘን እንደጣለብን ገልፀዋል:: በመጀመርያ ደረጃ ማንኛውም ወገን የራሱን ነፃ አመለካከት የመያዝና የማራመድ መብት እንዳለው እናምናለን፤ እናበረታታለንም:: ሁለተኛውና የሃሳቡ አቀንቃኝ ሊያርሙት የሚገባው ደግሞ የአገራችንን ፖለቲካዊ ሁነት ልዕልና የሚያረጋግጠው የኢትዮጵያ ሕዝብ ምስክርነትና ሙሉ ተሳትፎ እንጂ «የውጪዎቹ» ውዳሴ

ያለመሆኑን ቢያስታውሱት:: ምክንያቱም በውስጥ ጉዳያችን ጣልቃ እንደገቡ ከተሰማን «በሊማሊሞ አቋርጡ» እስከማለት የሚያደርስ ወኔ እንዳለን ለምን ይዘነጋል::

3. **'የገዢውን ፓርቲ ተግባራት ማብጠልጠል'**:- ፀሐፊው ጋዜጣችን የገዢውን ፓርቲ ተግባራት በማጣጣል ብቻ እና ከስልጣን ለማስወገድ ይበጃል የምትለውን ብትር ለተቃዋሚዎች በማቀበል ትታወቃለች ብለዋል:: ስህተት ነው:: በእርግጥ አውራምባ ታይምስ የተቋቋመችው የገዢውን ፓርቲ ተግባራት ለማሞጋገስ ወይም በስልጣን ላይ የሚቆይበትን መንገድ ለማመቻቸት አይደለም:: ተቃዋሚዎችን ለመደገፍና ለስልጣን ለማብቃትም አይደለም:: እስካሁን እያደረግነው ያለነውን የገለልተኛ ሚዲያ ተልዕኮ ማራመድ ብቻ ነው:: ገንቢ ትችቶችንና እርምት ሊወሰድባቸው የሚገቡ ህፀፆችን መጠቆም «ማብጠልጠል» ሊባል አይገባም::

4. **ለኢ/ሩ መቆርቆር ወይስ ኢንጅነሩን መጎትጎት?**:- በአዲስ ዘመን ገኸ አምድ ላይ ከተሰነዘረው ገደብ የለሽ ውንጀላ ጐን ለጐን የጽሁፉ ማጣፈጫ ሆነው የቀረቡት የመኢአድ ፕሬዚዳንት «ስብዕናቸው ስለተነካ የክስ ፋይል እንዲከፍቱ» ሲጎተጉቱ ሁሉ እናያለን:: በኃይሉ ሻውል ላይ የጥላቻ አቋም እንደተያዘባቸው፣ አቶ የሚል ማዕረግ እንኳ እንደተነፈጉ፣ ሥማቸውን ላለመጥራት «አዛውንቱ» ተብለው መሰየማቸውንና የመሳሰሉትን ዘርዝረዋል:: እውቁን ኢትዮጵያዊ ባሃብትና ፖለቲከኛ «ኃይሉ ሻውል» ወይም «አዛውንቱ» በሚል ስያሜ መጥራት የአክብሮታዊና እውቅናዊ መገለጫ ጎኑ ለምን አልታያቸውም? በእርግጥ ስምምነቱን ከፈረሙ «ተቃዋሚ»ፓርቲዎች መካከል የአውራምባ ታይምስ አዘጋጆችን በየፍርድ ቤቱ የሚያጉላሉና የሚያዋክቡ ፓርቲዎች እንዳሉበት ይታወቃል:: መኢአድም ይህንኑ ፈለግ እንዲከተል መወትወት ይመስላል::

5. **'ሰላማዊ ትግልን መምረጥ ተገቢ ያለመሆኑን'**:- በአዛውንቱ የመኢአድ መሪ ላይ የቀረበው ዘገባ አላማ ግለሰቡ ሰላማዊ ትግልን መምረጣቸው ትክክል ያለመሆኑን ለማሳየት ብቻ እንደሆነ ፀሐፊው መቶ በመቶ ደምድመው ገልፀዋል:: ይህ ደግሞ የውንጀላ ድምዳሜ ነው:: በዘገባው ላይ የቀረው መረጃ ከአምስት አመት በፊት የነበራቸውንና የአሁኑን አቋም በማነፃፀር ፖለቲካውን በቅርብ የሚከታተሉ ወገኖች ለመጠየቅ የተገደዱትን ጥያቄ በማንሳት የስነ አመክንዮ ፍጭትን ማስተናገድ ብቻ ነው:: ኢ/ሩ ራሳቸው «ካለፈው ተምረናል፣ አውቀናል::» ብለዋል:: በፖለቲከኛው የትናንትና የዛሬ አቋም ላይ ሁላችንም ተመሳሳይ ግንዛቤ ካልወሰድን ሰላማዊ ትግልን እየተቃወምን ነው የሚል አስተሳሰብ ማራመድ ከጤነኛ ዜጋ የሚጠበቅ አይደለም::

6. **'ተቋማዊ አቋምና ፍላጎት'**:- ጸሐፊው በፓርቲዎች መካከል የተደረሰው ስምምነት የፈጠረውን አዎንታዊ ስሜት በማብራራት «መላው ሕዝብ የሚኖርበት ገጠራማው ክፍል» ድረስ በመሄድ ለማረጋገጥ አውራምባ ታይምስ ተቋማዊ አቋምም ፍላጎትም የለውም» በሚል ተቋማዊ ግምገማ ውስጥ ገብተዋል:: የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ ማንም ይሁኑ «የስምምነቱ አንድምታ መላውን የገጠር ህዝብ ያስደሰተ» ለማለት ምስክር ሆነው የተከሰቱበት ልዕለ ስብዕና የሌላውን ተቋም አቋምና ፍላጎት ገምግሞ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ያበቃቸው አተያይ ተጠየቅ የሌለበት 'ደፋርነት' ብቻ ይሆናል:: «ቆርኔሊዮስ» የምትል ባርኔጣ ደፍቶ ውንጀላና ነውረኝነትን ሊያንፀባርቁበት የፈለጉትን ተቋም አቋምና ፍላጎት እንዲህ ነው እያሉ በጋዜጣ ላይ ማተም መቻሉን ከማሳየት የዘለለ

አንድምታ የለውም:: ይህ አንድምታ ደግሞ እጅግ  አደገኛ ነው:: በተለይ ኢራቅ ውስጥ በሱኒ እና ሺዓ ሙስሊሞች መካከል ያለው ደም አፋሳሽ ግጭት ለጽሁፋቸው ግብአት ሆኖ ለዚህች አገር በምሳሌነትና በንጽጽር መቅረቡ «ለመሆኑ ጸሐፊው ኢትዮጵያዊ ናቸውን» ያስብላል:: ሻዕቢያን የመሳሰሉ የኢትዮጵያ ጠላቶች እንኳን ኢትዮጵያን ለመበታተን እንዲህ አይነት «ጋኔናዊ ምኞት» አልተመኙልንም:: ፀሐፊው ተንፀባርቋል ያሉት የጥላቻ ዘመቻ መንስኤ ጋዜጣው ይዞት የተነሳው ፀረ ሰላም አቋም ነውም ብለዋል:: ይህን ሰቅጣጭና በአንድ ህጋዊ ተቋም ላይ የተሰነዘረ ውንጀላ አትሞ ማሰራጨት አንባቢውን ያለማክበርና የህግ የበላይነትንም ማናናቅ ብቻ ነው:: አንድ ተቋም በመንግስት ጋዜጣ አማካኝነት «ፀረ ሰላም» ተብሎ ሲሰየም የአሳታሚ ድርጅቱ ባለስልጣናት «እሰየው» ይላሉ ማለት ነው? ይህስ ስርአት አልበኝነትን አያሰፍንም?

<u>7 'መዋእለ ንዋይን ማጋበስ'</u>:- በመጪው ምርጫ ሁከትና አመጽ በማራገብ መዋእለንዋይ ለማጋበስ ስለመሞከር የተነሳ ሃሳብም አለ:: አንድ ኢትዮጵያዊ ፕሬስ ብሔራዊ ደህንነትን በሚያናጉ፣ የንፁሃንን ደም በሚያፋስሱና በመሰል ተግባራት ላይ ተረማምዶ መዋእለ ንዋይ ለማጋበስ ይሞክራል ብሎ ማሰብ ከዘለፋው አስነዋሪነት ባሻገር  የኢትዮጵያዊነት ስብዕናን ማንኳሰስ ይሆናል እንስሳዊ አስተሳሰብም ነው:: ሌላው ቢቀር ጸሐፊው ስለ ጋዜጠኝነት ያስተማሩንን ያህል አዲሱ የመገናኛ ብዙሃንና የመረጃ ነፃነት አዋጅን መሠረት በማድረግ በአዲስ መልኩ የተዋቀረው የህትመት ውጤቶች አሰራር፤ ባለቤቶች ሀብት ለማካበት በሚል በህትመት ውጤቶቹ ላይ የግዴለሽነት ተጽዕኖ እንዳያሳድሩና የዋና አዘጋጅነት ሥልጣን እንዳይኖራቸው መደረጉን እንዴት አያውቁም?

በመሰረቱ የጋዜጣችን አሳታሚ ድርጅት እንደተቋም የጋዜጣችን ባልደረቦች እንደ ዜጋ ኩሩ ኢትዮጵያዊያን እንደመሆናቸው ከገንዘብም ሆነ ከየትኛውም መዋዕለ-ነዋይ በላይ የአገራቸውን ህልውና፣ሰላምና ብሄራዊ ጥቅም እንደሚያስቀድሙ በኩራት መግለጽ እንፈልጋለን::

በመጨረሻም እኒህ ጸሐፊ ያሻቸውን ያህል ውንጀላ ከደረደሩ በኋላ የሚመለከተው አካል እርምጃ እንዲወስድ በሚያሳስብ መልእክት ውንጀላቸውን ደምድመዋል:: ጋዜጣችን እስካሁን ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች፣ ሀሳቦችና ሁሉንም አመለካከቶች ለማንሸራሸር መሞከሯን እና ወደፊትም እንደምትቀጥልበት ከላይ ገልጸናል:: ይህንኑ ተልዕኮ ስትፈጽም ደግሞ «ፕሬስ በተቋምነቱ የህግ ጥበቃ ይደረግለታል» የሚለውን የህገ መንግስቱ መርህ በመተማመን ነው:: የጋዜጣዋ ባልደረቦች የአገሪቱን ህግ አክብረን የሚጠበቅብን ሙያዊ ስነምግባር ጠብቀን ኃላፊነታችንን እየተወጣን ባለንበት ሁኔታ ጸሐፊው (ማንነታቸው ያን ያህል ባያሳስበንም) የሚመለከተው አካል እርምጃ እንዲወስድ ጥሪ አቅርበዋል:: የእርምጃው አይነት ምን እንደሆነ ግልጽ ባይሆንልንም የጸሐፊው ማሳሰቢያ የተስተናገደበት ጋዜጣ ባለቤቱ መንግስት ነው:: ይህ አቋም የመንግስትም ይሁን የጸሐፊው መልእክታችን ግልጽ ነው:: የግል ሚዲያ የዴሞክራሲ ዋስትና እንጂ ጠላት አይደለም!! በእርሱ ላይ የሚወሰድ ማንኛውም  እርምጃ ደግሞ ኪሳራ እንጂ ትርፍ የለውም::

**ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!**

## Verbatim

**«ጥያቄያቸውን በሙሉ ፈትተን ተጨባብጠን እንለያያለን ከቢሮ እንደወጡ ግን ቦርዱ ገለልተኛ አይደለም ይላሉ»**

ዶ/ር አዲሱ ገ/እግዚአብሄር
የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት ም/ሰብሳሯሽ

አብዛኛውን ጊዜ ኢህአዴግ ብቻ የምርጫ ቦርድ ገለልተኝነት ይቀበላል:: ሌሎች ተቃዋሚዎች በእናንተ ላይ እምነት የላቸውም፤ ምንድነው ችግሩ? ገለልተኝነታችሁን ማሳመንና ማሳየት አትችሉም? ተብሎ ከሪፖርተር ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ::

**«ፈረንጆቹ ይሄንን ዓይነቱን ነገር «ሳይኮፋንት (sycophant) ይሉታል:: ባዶ ነገር የሚናገሩ አሞጋሾች የሚሉት ነው:: ማንም ማንንም ይተካዋል:: ጠቅላይ ሚኒስትር መለስም ሰው ናቸው::»**

ዶ/ር ያዕቆብ ኃ/ማርያም
የቀድሞው የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ም/ሊቀመንበር

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊን የሚተካቸው ሰው የለም የሚሉ ሰዎች መኖራቸውንና በተለይ ፓርቲያቸው ያለእሳቸው የሚል እምነት ያለው መሆኑን አስመልክቶ ከሪፖርተር ጋዜጣ ጋር ሰሞኑን በነበራቸው ቆይታ የተናገሩት::

**«የመረጃ ነፃነት ሕጉ ከክልከላ ይልቅ ለመረጃ ነፃነትና መብት የሚሰጠው ትኩረት ይጎላል»**

አቶ ሽመልስ ከማል
የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽሕፈት ቤት ሚኒስትር ዴኤታ

አዲሱ የፕሬስ አዋጅ ያጎናጸፈውን መብት አስመልክተው በአንድ ሲምፖዚየም ላይ የተናገሩት

## ዜናዎች

# «ገመና» የተሰኘው የኢቴቪ ድራማ ቁጣ እየቀሰቀሰ ነው

- የእምነት እሴቶቻችን ተንቋሸዋል (የእስልምና እምነት ተከታዮች)
- ፖሊስና ሕብረተሰብ ካቀረበው የበለጠ አላደረግንም (ደራሲው)
- የእምነታችንን ስርአት ማቅረቡ አስፈላጊ አልነበረም (የኢ.ት.እስልምና ጉዳዮች ጠ/ጉባኤ)
- የተጫወትኩት ገጸ-ባህሪ ከቅዱሳን መጻህፍት የሚጠቅስ ሰይጣንን ነው (ተዋናዩ)

በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የእሁድ መዝናኛ ፕሮግራም ላለፉት ተከታታይ ሳምንታት እየቀረበ ያለው «ገመና» የተሰኘ ድራማ የእምነት እሴቶቻችንን የሚያንቋሽሹ ሁነቶችን አንፀባርቋል ሲሉ የእስልምና እምነት ተከታዮች ለዝግጅት ክፍላችን ገለፁ፡፡ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ጉባኤ ም/ፕሬዝዳንት የሆኑት ሼህ ሙሐመድ ኢብራሂም በበኩላቸው የዚህ አይነት ፕሮግራሞች ሲዘጋጁ የእምነቱን ባለቤቶች ማነጋገር ያስፈልግ ነበር ብለዋል፡፡

ጉዳዩ ወደ ህግ የሚሄድበትን ሁኔታ እያመቻቸን ነው ያሉት የእምነቱ ተከታዮች በድራማው ላይ ያሉት ገፀ-ባህርያት የእስልምና እሴቶች የሆኑትን ለፈጣሪ የሚቀርቡ ውዳሴዎች ከነውረኛ ተግባራት ጋር አጣምረው በማስተላለፍ፣ በአለባበስና በአነጋገር ማለፍ የማይገባቸውን መስመር በ«ማስተማር» ሽፋን አልፈዋል ሲሉ ቅሬታቸውን ገልፀዋል፡፡ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ጉባኤ ም/ፕሬዝዳንት ሼህ ሙሐመድ ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፁት «አፍራሽ የሆኑ ነገሮችን እንቃወማለን፡ ፕሮግራሙ የተላለፈው ለማስተማር ቢሆንም የሚተላለፈው መልዕክት የአንድ እምነት አባላትን የሚያስከፋ መሆን የለበትም፡፡ በድራማው ላይ ያሉት ገፀ-ባህሪያት እስልምናንም ክርስትናንም አይወክሉም፡፡ ስለዚህ የእምነታችንን ስርአት ማቅረቡ አስፈላጊ አልነበረም፡፡» ብለዋል፡፡

የገመና ድርሰት ፀሐፊ የሆኑት አዱኒስ የድራማውን መተላለፍ ተከትሎ ተመሳሳይ ጥያቄዎች እንደቀረቡላቸው አስታውሰው «ድርሰቱ የተዘጋጀው ሕበረተሰቡን እያዝናኑ ለማስተማር ብቻ መሆኑንን በተደጋጋሚ አስታውቀናል፡፡» ሲሉ ለአውራምባ ታይምስ ገልፀዋል፡፡ «እኛ ያቀረብነው ድራማ የፖሊስና ሕብረተሰብ ፕሮግራም አቶ ታምራት ገለታን አስመልክቶ ለማስተማሪያነት ካቀረበው ያነሰ እንጂ የበለጠ አይደለም፡፡» ሲሉ በንጽጽር ገልፀዋል፡፡ የኢቴቪ መዝናኛ ክፍል ም/ኃላፊ የሆነት አቶ ሺበሺ አለማየሁ ጉዳዩ የእኛን ክፍል አይመለከትም ሲሉ የገለጹ ሲሆን በድራማው ላይ አጭበርባሪ ባለውቃቢ ሆኖ የሚተውነው አርቲስት ዘላለም በበኩሉ በሰጠው አስተያየት «ሰይጣን ለአመሉ ከቅዱስ መፅሀፍ ይጠቅሳል እንደሚባለው እኔ በድራማው ላይ የወከልኩት ገፀ-ባህሪ «አጭበርባሪ» ነው፡፡ ገፀ-ባህሪው ተከታዮቹን ለማጭበርበር እና ለማሳመን ሀይማኖታዊ እሴቶችን እንደሚጠቀም ለማሳየት እንጂ የትኛውንም የሀይማኖት ተቋም የሚንቋሸሽ አላማ የለውም፡፡ደግሞም ይህ አጭበርባሪነት የተደመደመው በሽንፈት በመሆኑ የሚያስተላልፈው መልእክት አለ፡፡» ብሏል፡፡

## መኢአድ በገዥው ፓርቲ አመራሮች ቃል እንደተገባለት ገለጸ

የመላው ኢትዮጵያውያን አንድነት ድርጅት (መኢአድ) በየዞኑ ያሉ የገዥው ፓርቲ አስተዳዳሪዎችም ሆኑ ሰራተኞች ከዚህ ቀደም ያደርሱብን የነበረውን በደል እና መገፋት እንደማይፈጽሙ በገዥው ፓርቲ አመራሮች ቃል ተገብቶልናል ሲል ለዝግጅት ክፈላችን በላከው መግለጫ አስታወቀ፡፡

የዋናው መ/ቤት እና የዞን አመራሮች በምርጫ ስነ ምግባር ደንቡ ላይ ውይይት ማድረጋቸውን ያወሳው መግለጫው ላለፉት 18 ዓመታት በገዥው ፓርቲ እና በተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል ከፍቅር ይልቅ ጥላቻ፣ ከመቀራረብ ይልቅ የመለያየት አላስፈላጊ ግንኙነት እንደነበር ገልጿል፡፡ የተደረሰበትን ስምምነትም መልካም አጋጣሚ ብሎታል፡፡

በአይቤክስ ሆቴል የተደረገው ሰፊ ማብራሪያና ገለጻ የድርድሩን አስፈላጊነት፣ ጠቃሚነት እና ለሰላም የሚኖረውን አስተዋጽኦ እንድንረዳው አድርጉናል ያሉት አመራሮች ሰነዱን በሙሉ ድምጽ ተቀብለናል ብለዋል፡፡

## አንድነት «መርሕ ይከበር» የሚሉ አባላቱን ከጽ/ቤቱ በፖሊስ ለማስወጣት ሞከረ

«መርሕ ይከበር» የሚለውና ፐ/ር መስፍን ወ/ማርያምን ጨምሮ ከ20 በላይ የተሰረዙ አመራሮችን ያቀፈው አካል ከትናንት በስቲያ በጽ/ቤቱ እያካሄደ የነበረውን ውይይት በፖሊስ ኃይል ለማስቆም የፓርቲው አመራር ያደረገው መከራ መክሸፉን  ለዝግጅት ክፍላችን ገለፀ፡፡

ኢ-ፍትሃዊ በሆነና በተሳሳተ አምባገነናዊ ስሌት ከአባልነታችን «ተሰርዘዋል» ብንባልም ከትናንት በስቲያ ያካሄድነው ውይይት ፓርቲያችን ያለበትን አሳሳቢ ሁኔታ ታሳቢ ያደረገ ነበር ብለዋል፡፡ የም/ቤት አባልና የጽ/ቤቱ ሰራተኛ በሆኑት በወ/ሮ ሙሉነሽ አበባይሁ  አሳሳቢነት ወደውይይቱ ስፍራ የመጡት የፖሊስ አባላትም የተፈጠረ ችግር ያለመኖሩን ካረጋገጡ በኋላ ጽ/ቤቱን ለቀው መውጣታቸውን አባላቱ ገልፀውልናል፡፡ ከውይይቱ መጠናቀቅ በኋላ የጽ/ቤቱ የጥበቃ አባል የሆኑት አቶ መንገሻ ብሩ ከሥራቸው መባረራቸውን የደረሰን መረጃ አመልክቷ ፡፡

## የቀድሞ የኤፍ.ኤም. 97.1 ጋዜጠኛ ሙያዊ ተጽዕኖ ይደረግብኝ ነበር አለች

በኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ስር በኤፍ.ኤም. 97.1 በጋዜጠኝነት ታገለግል የነበረችው ጋዜጠኛ ነቢያት ገቢሳ መንግስት በመገናኛ ብዙሃን ላይ ከፍተኛ ጫና እንደሚያሳድር

ለውጭ ድረ-ገጾች ገለፀች፡፡ በአሁን ሰዓት ሆላንድ፣ አምስተርዳም የምትገኘው ነቢያት በኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ውስጥ የሚገኙ ጋዜጠኞች በመንግስት ቅድመ ምርመራ አማካኝነት የተለያዩ ገደቦች እንደሚጣልባቸውና የራስ ቅድመ ምርመራንም እንደሚተገብሩ ተናግራለች፣ «በመንግስት ላይ ማንኛውንም ወሳኝ ትንታኔዎች ከማቅረብ የምንቆጠበውም በዚሁ ምክንያት ነው፡፡» በማለት

በምርጫ 97 ወቅት በሰራችው ዘገባ ምክንያት ለ43 ቀናት መታሰሯንና በመጨረሻም ከመስሪያ ቤቱ እንድትለቅ መደረጓን በድረ-ገጾቹ የገለፀችው ጋዜጠኛ ነብያት ገቢሳ ከሀገር ከመውጣቷ በፊት በኢትዮጵያ በጎ ፍቃድ ጋዜጠኞች ማህበር ስር «ላምባዲና» በተሰኘች በነፃ የምትሰራጭ ጋዜጣ ላይ ትሰራ እንደነበር ለማወቅ ተችሏል፡፡

# የድምፃዊት ማንአልሞሽ ዲቦ የደቡብ አፍሪካ ጉዞ እስካሁን አልተሳካም

በናፍቆት ዮሴፍ

በባህል ዘፈኖቿና በተስረቅራቂ ድምጿ እውቅናንና ተወዳጅነትን ያተረፈችው ድምፃዊት ማንአልሞሽ ዲቦ የደቡብ አፍሪካ የህክምና ጉዞ አልተሳካም፡፡

ድምፃዊቷ በአንጀት ካንሰር ህመም ለአንድ አመት ያህል እንደተሰቃየችና ለሰባት ጊዜ ያህል ቀዶ ጥገና የተደረገላት ቢሆንም ከህመሟ ልትድን ባለመቻሏ እንደውም ወደ ውጭ ሄዳ ካልታከመች በህይወት የምትቆየው ለአንድ ወር ብቻ እንደሆነ በዶክተሮች ተነግሯት ገንዘብ በእርዳታ እየተሰባሰበላት እንደነበር በመገናኛ ብዙሃን በሰፊው መዘገቡ ይታወሳል፡፡

በደቡብ አፍሪካ ለሚገኙ ሀኪሞች የድምጻዊቷ የህመም ሁኔታ ተልኮ እንደነበርና ብትመጣ ልትድን እንደምትችል በሰጡት ምላሽ መሠረት ሼህ መሀመድ ሁሴን አላሙዲን የህክምናዋንና የአስታማሚዋን እንዲሁም የጉዞዋን ጠቅላላ ወጪ ሸፍነው ሊያሳክሟት መወሰናቸውንና ልትሄድ ዝግጅት ላይ እንደነበረች ታውቋል፡፡ እንደ አስተባባሪዎቹ ገለፃ ከሆነ ማንአልሞሽ ወደ ደቡብ አፍሪካ ሄዳ ለመታከም መጀመሪያ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ዶክተሮች መታየት እንደነበረባትና ባለፈው ቅዳሜ ጠዋት 3፡00 ሰዓት ላይ ወደ አየር መንገዱ ሀኪሞች መቅረብ የነበረባት ቢሆንም ቅዳሜ ጠዋት በጣም ታማ ራሷን በመሣቷ ወደ አየር መንገድ ሳትሄድ መቅረቷን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ይሁንና በነጋታው (እሁድ) ጠዋት በተያዘላት ቀጠሮ አየር መንገድ ዶክተሮችጋ ብትቀርብም በአየር መንገዱ አውሮፕላን መጓዝ እንደማትችል ተነግሯት መመለሷን ከእርዳታ አስተባባሪዎቹ አንዱ የሆነው ሰይፉ ፋንታሁን ለዝግጅት ክፍላችን አስታውቋል፡፡ «ካፕቴይኑ አይተዋት መጓዝ አትችልም ብለዋታል» ሲል በሀዘን ሰይፉ በስልክ ገልጾልናል፡፡ ሆኖም ዝግጅት ክፍላችን ስለጉዳዩ ያነጋገራት የማናልሞሽ እህት አልማዝ ዲቦ «ጉዟችን የተስተጓጐለው በራሳችን በኩል ያላሟላነው

ዶክመንት ስላለ እንጂ አየር መንገዱ አንዳንዴድ ከልክሎን አይደለም፡፡» ካለች በኋላ ከትላንት ወዲያ እሁድ ጠዋት ማናልሞሽ ጭራሽ ወደ አየር መንገድ እንዳልሄደችና የአየር መንገዱ ዶክተሮችም እንዳልተመለከቷት ገለፃልናለች፡፡

# መጣጥፎች

## መልዕክተ አቤቶ

**ከዝግጅት ክፍሉ**

**ዓምደኞችን የሆነው አቤ ቶኪቻው ከአቅም በላይ በሆነ ችግር የተለመደው ወጉን ሊያደርሰን እንደማይችል ሲገልጽልን የለም በአንድ አረፍተነገርም ቢሆን በራስህ መንገድ መልእክትህን አስተላልፍ እንጂ እኛ አናደርገውም ባልነው መሰረት ይህችን አጭር መልእክት አድርሶናል፡፡**

ወዳጄ እንዴት ሰንብተውልኛል? አፈር ስሆን «አለሁልህ» ይበሉኝና ደስ ልሰኝልዎ! እኔም እርስዎን ደስ ይልዎት ዘንድ «አለሁልዎ» ብቻ ሳይሆን ረገጥ አድርጌ «እጅግ በጣም ደህና ነኝ» ልልዎት እወዳለሁኝ፡፡

የዛሬው አመጣጤ እርስዎ ወዳጄ «ምን ዋጠው?» ብለው እንዳይጨነቁ በክፉ የሚያዩን ደግሞ «እሰይ እንደ ክረምት መብራት ጠፋልን!» ብለው ጮቤ እንዳይረግጡ ያኽል ነው፡፡ እንጂ ብዙ ላወጋዎ አይደለም፡፡

አይዞት ወዳጄ አይደንግጡ በደህናዬ ነው፡፡ ፀሀዩ መንግስታችን ቦግ ብሎ እስከበራ ድረስ ምን ክፉ ይገጥመኛል ብለው ነው?

ለዚህም አይደል «ፀሀዩ ለዘላለም ይብራ» ብለን በመፀለይ እየተጋን ያለነው! (በቅንፍ ትንሽ ጨዋታ፣ በቅርቡ የዓለም መልካም አሳቢ አገሮች እና መሪዎቻቸው «ፀሀዩ በዛ፣ ህዝቡም ተቃጠለ፤ በዚሁ ከቀጠለ ትልቅ ስጋት ነው» የሚል ዘገባ በአንድ ሬድዮ እየሰማን ሳለ አንዱ ወዳጄ ዜናውን ሙሉ በሙሉ አልሰማው ኖሮ «እነዚህ ሬድዮኖች ሃይ ባይ አጡ ማለት ነው?» ሲል ጠየቀን፡፡ «እንዴት?» አልነው፡፡ «ሃያ ዓመት ምን አላት እና ነው «ፀሀዩ በዛ ህዝቡም ተቃጠለ...» እያሉ የሚዘግቡት?» ሲል ጠየቀን፡፡ «የምን ሃያ ዓመት ...?» አልነው በመደነቅ እርሱም «ፀሀዩ በዛ የሚሉት ፀሀዩ መንግስታችንን አይደለም እንዴ?» ብሎ ቢጠይቀን ስቀን! ስቀን! ስቀን! ተሳቀን ስናበቃ ወዳጃችንን በዛ የተባለው ፀሀይ የአየር ንብረቱን እንጂ የእኛን ፀሀይ አለመሆኑን አስረድተነው፣ የእኛ ፀሀይ ለዘላለሙ ቢበራም እንደማያቃጥለን፤ ቢያቃጥልም በሬድዮ እንደማይነገር ነግረነው እርሱም ሂሱን ውጦ ተለያየን እልዎታለሁ፡፡)

ቅንፋችን ሲዘጋ፣ እናም ፀሀዩ መንግስታችን ሳለ ምንም አልሆንምና አያስቡ፡፡ በሚቀጥለው ሳምንት በአግባቡ ላወጋዎ ቃል እገባለሁኝ፡፡ እንደው ዝም ብሎ ጥፍት ከማለት ይሻላል ብዬ ያሰፈርኩት የሰላሜ መልዕክት የሚከተለውን ግጥም ያስከትላል፡-

.....እቴ
ነሽ መብራቴ
ብርሃኔ ነሽ አንቺ
ፏ! የምታደርጊኝ
ምንም ሳትሰለቺ
....እቴ
መብራት ኃይሌ
በርግጥ አይሳካም
በርቶ መኖር ሁሌ
ቢሆንም መብራቴ
አትጥፊብኝ በቃ
ዘወትር ብሪልኝ
አልወድም ፈረቃ::

***በመጨረሻም***

ሰሞኑን ክረምት በገባ ቁጥር «ፈረቃ ይመጣ ይሆን?» እያሉ ከመተከዝ ሊያድነን የተከዜ ኃይል ማመንጫ ግንባታ ተጠናቆ ተመርቋል! እሰይ! እንኳን ደስ ያለን! በበኩሌ «ተከዜ ያወጣል ከትካዜ» የምትል መዝሙር አዘጋጅቼያለሁኝ፤ መብራት ኃይሎች ስፖንሰር ካደረጉኝ በቅርቡ ለህዝብ ይፋ አደርጋታለሁኝ::

ይበሉ ወዳጄ ለሰላምታ የመጣሁት ሰው «ቶክ» አበዛሁብዎ መሰል:: አሁን መሰነባበቻችን ደርሷል:: ቆይ ከመሰነባበታችን በፊት ግን «ቶክ» ስትል ምን ትዝ አለህ ይበሉኝ? አንድ ወዳጄ «አቤ ቶኪቻው» የሚለውን ስሜን ማን ብሎ እንደጠራው ያውቃሉ? «አቤ ቶከኛው!» (ከእንደዚህ ዓይነት ነገረኛ ይሰውርዎ::)

አሁን መሰነባበት ይቻላል::
አማን ያሰንብተን !

**ባለፈው ማክሰኞ ህዳር 01 ቀን 2002 ዓ.ም ዕለታዊው አዲስ ዘመን ጋዜጣ «ከድርጊት ዘጋቢነት ይልቅ ወደ ድርጊት አስፈፃሚነት የተለወጡ ጋዜጦችና ጋዜጠኞች» በሚል ርዕስ በጋዜጣችን ላይ በርካታ ውንጀላዎችን ሰንዝሯል:: ውድ አንባቢያን ይህንኑ ጽሁፍ አንብበው ህሊናዊ ፍርድ እንዲሰጡ ከዚህ በታች አቅርበነዋል::**

# ከድርጊት ዘጋቢነት ይልቅ ወደ ድርጊት አስፈፃሚነት የተለወጡ ጋዜጦችና ጋዜጠኞች

**ቆርኔሊዮስ (ከአአዩ)**

... አንዳንድ የግል ጋዜጦች ኃላፊነት የጐደለው ተግባር እየፈፀሙ መሆናቸውን በተጨባጭ ማየት ይቻላል፡፡ በራሳቸው ሃሳብ አመንጪነት ሕዝብን ከሕዝብ ለማቃቃር ሌት ተቀን እየሰሩ ያሉ ጋዜጦች የትኞቹ እንደሆኑ በስም ዘርዝሮ መግለጽ ይቻላል፡፡ ለዚህ ማስረጃ የሚሆነን በቅርቡ በአገሪቱ የታየውን ታላቅ ፖለቲካዊ ክንውንን ማየት እንችላለን፡፡ እርግጥ ሰላማዊ ትግልንና አመጽን አቀላቅለው እንደትግል ስልት የመጠቀሙ አዝማሚያ በአገራችን የፖለቲካ ህይወት ውስጥ እየተዳከመ መምጣቱንና የፖለቲካ ፓርቲዎች አንዱን ዓይነት የትግል ስልት ለመምረጥ የተገደዱበት ጊዜ ላይ መድረሳቸውን ተከትሎ በግል ጋዜጣ ስም የሚታተሙና የሚሰራጩ ጋዜጦችም ሚናቸው በግልጽ እየተለየና እየተሠመረ የመጣበትን ሁኔታም አብሮ መመልከት ተችሏል፡፡

እውነታውን ከመዘገብ ይልቅ ራሳቸው የሚፈልጉትን መጥፎ ክስተት ለመፍጠርና ለማራገብ ቋምጠው እየተራወጡ ያሉት አንዳንድ የግል ጋዜጦች ይህን ዓላማ ለማሳካት የሚጠቀሙት የፕሮፓጋንዳ ዘዴን ሲሆን፤ የሚፈጽሙት ተግባር ደግሞ ጥላቻን መንዛት ነው፡፡ የሚጠቀሙትን ዘዴና የሚያከናውኑትን ተግባር ለመዘርዘር ሰፊ ቦታን የሚጠይቅ በመሆኑ በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ሁሉንም ማካተት አስቸጋሪ ቢሆንም አንዳንድ ነጥቦችን ማንሳት ይቻላል፡፡

... አዲስ ነገር እና አውራምባ ታይምስ የሚጠቀመበት ዘዴ ከዋነኛ የፕሮፓጋንዳ ሥራዎች ጋር የሚያመሳስሏቸው በርካታ ነጥቦች አሉ፡፡ ፕሮፓጋንዲስቶችን ሁሉ የሚያመሳስላቸው ዋነኛ ነጥብ በጠላትነት የፈረጁትን ግለሰብ ወይም ቡድን የሚሰራውም ይሁን የሚናገረው ሁሉ መጥፎ ነው የሚለው መነሻ ሀሳብ ነው፡፡ ይህ የሁሉ ነገር መነሻቸው ነው፡፡ በጠላትነት የፈረጁት አካል ለአገርና ለሕዝብ የሚጠቅም ሥራ ቢሰራ እንኳ ይህን ያደረገው ለራሱ እንጂ ለሕዝብና ለአገር አስቦ አይደለም በማለት ሕዝብን ለማሳመን ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ጠላት ነው የሚሉት ግለሰብ ወይም ቡድን የሚሰጠውን አስተያየት በጋዜጣቸው ለማስተናገድ እድሉን አይሰጡትም፡፡ ለመካድ አስቸጋሪ የሆነ ጠቃሚ እርምጃ ካለም ስለዚያ ጉዳይ እንዳይነሳ፤ ማንሳቱ የማይታለፍ ከሆነም በጋዜጠኛው የግል አስተያየት እንዲደበዝዝ ሲደረግ በአንጻሩ ጽንፈኛ የፖለቲካ መሪዎች የሚሉትን ብቻ እንዳለ ማስተጋባት፤ ከዚያም አልፎ አሟሙቆና አዳምቆ በማቅረብ ላይ ብቻ ያተኩራሉ፡፡ በኋላ ሊከሰት የሚችለውን መዘዝ እያወቁ (የማያውቁ መስለው በመቅረብ) አመጽና ብጥብጥን የሚጋብዙ ዘገባዎችን በማቅረብም ላይ ይጠመዳሉ፡፡

ሌላው ፕሮፓጋንዲስቶችን የሚያመሳስላቸው ሥራ ጠላት ብለው የሚፈርጁት አካል ጉዳት ሊደርስበት ወይም ሊወገድ ይገባዋል የሚል መልዕክት ለተደራሻቸው በግልጽም ይሁን በስውር ማስተላለፋቸው ነው፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ በጥላቻ ፕሮፓጋንዳና በገንቢ ትችት መካከል ያለው ቁልፍ ልዩነት ከዚህ የሚመነጭ ነው፡፡

በሚዲያው ዓለም ጥላቻ መቀስቀስ ተብሎ የሚታወቀው ተግባር ቀዳሚው አንድ የተወሰነ እርምጃ እንዲወስድ ለማነሳሳት ታስቦ ከፍተኛ የጥላቻ ስሜት እንዲያድርበት የሚደረግን ጥረት ለመግለጽ ነው:: በሌላ አገላለጽ ጥላቻ መቀስቀስን ከትክክለኛ ትችት የሚለየው አንባቢያንን ወይም አድማጭን በማሳመን የሚዲያው አዘጋጆች የሚጠሉትን ግለሰብ ወይም ቡድን (ፖለቲካ፣ የሃይማኖት፣ የብሔረሰብ፣ ወዘተ) ለማስወገድ አስበውበት የሚያደርጉት መሆኑ ነው:: ትክክለኛ ትችት የሚባለው ደግሞ ትችቱ የቀረበበት አካል ድክመቶቹን እንዲያርምና የበለጠ እንዲስተካከል ለማድረግ ታስቦ የሚሰራ በመሆኑ የሚፈለግና የሚበረታታ ነው::

እንደተገለፀው ጥላቻ የማራገብ ዘዴ የበተለያየ መልኩ የሚከናወን ሲሆን ጠቅለል ተደርጐ ሲታይ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የሚከናወን ተብሎ ሊፈረጅ ይችላል:: ቀጥተኛ የሚባለው የሚዲያው አዘጋጆች የሚጠሏቸውን ቡድኖች የሚጐዳ ማንኛውንም እርምጃ ታዳሚዎቻቸውን እንዲወስዱ በቀጥታ የሚማጸኑበት ነው:: ይህ ዘዴ በግልጽ ስለሚታወቅና አግባብ ባለው ሕግ የሚያስጠይቅ በመሆኑ ጽንፈኞች አይመርጡትም:: እነሱ የሚመርጡት በማር የተለወሰ ጥላቻን ማራገብ ሲሆን፤ ይኸውም ከተጠያቂነት የሚያድን መስሎ ስለሚታያቸው ነው::

ይህንኑ በምሳሌ አስደግፈን ለማየት እንሞክር:- ለምሳሌ በኢራቅ የሚታተሙትን የግል ጋዜጦችን ብንወስድ ሁሉም የየራሳቸውን ጥላቻ ያራግባሉ:: ጥላቻን የሚያራግቡት በተዘዋዋሪ መንገድ ሲሆን፤ ይኸውም የሱኒ እምነት ተከታይ የሆነ ባለቤት /ዋና አዘጋጅ የሚያስተዳድረው ጋዜጣ ሁሌ የሚያስተላልፋቸው ዘገባዎች ሺዓዎች በሱኒዎች ላይ ያደረሷቸውን በደሎችና ጥቃቶች ብቻ የሚያትቱ ናቸው:: ሱኒዎች በሺዓዎች ስለሚፈጽሟቸው በደሎችና ጥቃቶች አንድም ቀን ለመዘገብ ሞክረው አያውቁም:: የሚፈለገው አንባቢዎቻቸው የሆኑት የሱኒ እምነት ተከታዮች በሺዓ ወንድሞቻቸው የተፈፀሙባቸው በደልና ጥቃት አስቆጭቷቸው ለበቀል እርምጃ እንዲነሳሱ ሲሆን፤ ይህንን ፊት ለፊት አይነግሯቸውም:: የሺዓ እምነት ተከታይ የሆነ አዘጋጅ ባለቤትም እንዲሁ በእሱ እምነት ተከታዮች ላይ ሱኒዎች ያደረሱትን ጥቃት ብቻ እየመረጠ ይዘግባል:: የራሱ ወገን በሌሎች ላይ የፈፀመውን ጥቃት በፍፁም አያነሳም:: በመሆኑም አገሪቱን በማያባራ ግጭት ውስጥ በመንከር ረገድ ሚዲያው ግንባር ቀደም ሚና እየተጫወተ ይገኛል:: ሰላምን በአስተማማኝ ሁኔታ ለመፍጠር በሚደረገው ጥረት ውስጥ አንዱ አስቸጋሪ ጉዳይም ይኸው የሚዲያ ጉዳይ መሆኑ ይታወቃል::

ወደ አገራችን ስንመለስ አዲስ ነገር እና አውራምባ ታይምስ እየሰሩት ያለውን ስንመለከት ከዚሁ ያልተለየ ነው:: ከነዚህ ጋዜጦች መካከል አንዱ አውራምባ ታይምስ የተባለው የግል ጋዜጣ ደግሞ የሰሞኑ ዋነኛ ተዋናይ በመሆን የፕሮፓጋንዳ አጋሮቹን ለመቀላቀል ሲውተረተር ይታያል::

እነዚህ ጋዜጦች ጥላቻን በማራገብ ሥራ ላይ ከተጠመዱ የእድሜያቸውን ያህል ረዘም ላለ ጊዜ ቢሆንም የጥላቻው አድማስ ምን ያህል ሰፊና አደገኛ እንደሆነ አመላካች የሚሆኑት ሰሞኑን በአገራችን ከተካሄደው የፖለቲካ ፓርቲዎች የስነ-ምግባር ድርድር ጋር አያይዘው ያቀረቧቸውን ዘገባዎች መመልከት ይቻላል:: በተለይም አውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ጥቅምት 24 ቀን 2002 ባወጣው እትም ይዟቸው ከወጡት ዘገባዎች ይዘት አኳያና በተለይም የራሱን አቋም ካንፀባረቀበት ርዕሰ አንቀፁ አኳያ ሲፈተሽ የጋዜጣው ዋና አዘጋጅ የተጠናወታቸውን ሰይጣናዊ አስተሳሰብ

አመላካች ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በአገራችን ሰላማዊ፣ ዴሞክራሲያዊ፣ ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ እንዲኖር የሚያስችል ቀዳሚና ታሪካዊ እርምጃ በመባል በውጭ ዲፕሎማቶችና ሚዲያዎች የተወደሰው የሥነ-ምግባር ደንብ ስምምነት መፈረሙ ጋዜጠኛውን ክፉኛ ከማሳዘን አልፎ ማቅ እንዳለበሳቸው ከዘገባዎቹ መረዳት ይቻላል፡፡ እንዲያውም ሌሎች ፓርቲዎችም ሰላማዊ ትግሉን ይቀላቀሉ ይሆን ወይ የሚል ስጋት ጭምር የተንፀባረቀበት መሆኑ ሲታይ የጋዜጣውን አደገኛነት በማያሻማ ቋንቋ ጠቋሚዎች ናቸው፡፡

አዲስነገር እና አውራምባ ታይምስ የፕሮፓጋንዳ ዋነኛ መገለጫ የሆነውን ገዥው ፓርቲ የሚያደርገውን ማንኛውንም ተግባር በማጣጣል ብቻ ሳይሆን ከሥልጣን ለማስወገድ ይበጃል ብለው የሚያስቡትን በትር (አጀንዳ) ለተቃዋሚ ኃይሎች በማቀበልም ጭምር የሚታወቁ ናቸው፡፡ በተለይም አዲስ ነገር የራሱን ፕሮፖጋንዳ ለመሸፈን በሚያደርገው ጥረት የርዕዮተ ዓለም መጽሄት የሆነውን አዲስ ራዕይ የፕሮፖጋንዳ መሳሪያ ነው እስከማለት የደረሰበትን ሁኔታ ማስታወስ ይቻላል፡፡ አንድ አይነት አመለካከት ያላቸው የኢህአዴግ አባላት በስምምነት በተቀበሉት ርዕዮተ ዓለም ዙሪያ የሚያጠነጥነውን የፓርቲ ርዕዮተ ዓለም መጽሄት የፕሮፖጋንዳ መሳሪያ የሚያደርገው አንዳች ነገር የለም ታቅዶ የሚዘጋጀው ለአባላት ብቻ በመሆኑ፡፡ በአንጻሩ ሁለቱ ጋዜጦች የፕሮፓጋንዳ መሳሪያ መሆናቸውን የሚያስረዳው ለአባላት የሚሰራጩ ሳይሆኑ በውል ተለይቶ ላልታወቀ ታዳሚ በመሆናቸው የፕሮፓጋንዳ መሳሪያ ለመሆናቸው ጥርጥር የለውም፡፡ ከዚያ በላይ ማስረጃ የሚሆነው የፕሮፓጋንዳ መነሻ የሆነውን ጥላቻ መሠረት አድርገው የሚንቀሳቀሱ መሆናቸው ነው፡፡ ይኸውም ገዥው ፓርቲ የፈለገውን ውሳኔ ቢያስተላልፍ መጥፎ ነው ብለው የሚገልፁ እንጂ እንደ ነፃ አስተያየት ሰጪ ለውሳኔው ገንቢ ግብአቶችን ለማቀበል ታስቦ እንዳልሆነ ይታወቃል፡፡ ይህንን አቋማቸውን ግልጽ አድርጐ ያመለከተው በአገራችን ለሰላማዊ፣ ዴሞክራሲያዊ፣ ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ መረጋገጥ እንደበጐ እርምጃ መታየት የሚገባውን የፖለቲካ ፓርቲዎች ድርድርና ስምምነት አስመልክተው፤ ያራመዱትን አቋም መውሰድ ይቻላል፡፡

አውራምባ ታይምስ በጥቅምት 24 ቀን 2002 ዓ.ም እትሙ ይዞት የወጣውን ስንመለከት ገዢውን ፓርቲ መኮንን የጋዜጣው የተለመደ ተግባር ስለሆነ ይህን ወደጐን ትተን ከስምምነት ተፈራራሚ ፓርቲዎች የአንደኛው ፓርቲ መሪ በሆኑት ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል ላይ የወሰደውን የጥላቻ አቋም እንመልከት፡፡ የሚገርመው እኚህ የፖለቲካ ፓርቲ መሪ ስምምነቱን የፈረሙት ፓርቲያቸውን ወክለው መሆኑን እንኳ ለመቀበል ምን ያህል እንደተቸገረ ከጋዜጣው መረዳት ይቻላል፡፡ የግለሰቡን ስብዕናና የፓርቲውን ሥም እስከማጥፋት ደረጃ መድረሱንም መገንዘብ ይቻላል፡፡ የግለሰቡን ሰብእና መነካት አስመልክቶ ግለሰቡና ፓርቲያቸው አግባብ ባለው ሕግ ፀሐፊውን ሊጠይቁ ስለሚችሉ ለጊዜው ይህን ጉዳይ ለእነርሱ እተወዋለሁ፡፡ እኔን የሚያሳስበኝ ከአንድ ግለሰብና ፓርቲ ጉዳይ በላይ የሆነ ነገር በመሆኑ ይህንኑ ለማብራራት እሞክራለሁ፡፡

«ኢንጂነር» በሚል መጠሪያ ሲያሞካሻቸው የነበሩትን የፓርቲ መሪ መጠሪያቸው የሆነውን ኢንጂነር ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያውያን የተለመደውን የክብር ማዕረግ «አቶ» ጭምር በመንፈግ ገና ከርዕሱ ጀምሮ ጥላቻውን አንፀባርቋል፡፡ «ኃይሉ ሻውል ፖለቲከኛ? ልማታዊ ባለሀብት? ወይስ ሁለቱንም?» በሚል በገጽ 13 ላይ ዜና በሚል ገዥ አምድ ሥር የቀረበ ዘገባ ወይም ዜና ያልሆነ

ጽሑፍ በጥያቄ መልክ የተዘጋጀ የዓለማችን የመጀመሪያው ዜና ሆኖ ቀርቧል:: በዜናው መነሻም ላይ ሥማቸውን እንኳ ላለመጥራት  አዛውንቱ ብሎ በመሰየም ጽሁፉ በመነሻው በስፋት ትኩረት የሰጠው በጣት ከሚቆጠሩት ኢትዮጵያውያን ባጸጋዎች አንዱ መሆናቸውንና በኢትዮጵያ ሰማይ ሥር በስኬት  እየገሰገሱ ካሉ ጥቂት ኩባንያዎች የፊት መስመር ላይ የሚገኙ መሆናቸውን ለመግለጽ ሞክሯል:: በአገር ውስጥና በውጭ ያሏቸውን አንዳንድ ሀብቶች ከዘረዘረ በኋላም ለሀብታቸው መከማቸት በሰምና ወርቅ የተባጀ መሰላል እንዳለ ይጠቁማል::

እንግዲህ የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ የሚጀምረው የግለሰቡን ስብእና ከማንቋሸሽ ነው:: ጋዜጣው ቀደም ሲል ሲያከብራቸው በነበሩት በእኚህ ሰው ላይ ለምን ይህ ሁሉ የጥላቻ  መርዝ ሊረጭ ቻለ? ማለታችን አይቀርም:: የሰውየውን የሀብት መጠን እንዲህ እየዘረዘረ ለአንባቢያን ለማቅረብ የሞከረው ከመጥፎ ቅናት በመነጨ ስሜት ብቻም አይደለም:: ምስጢሩ ሌላ ነው:: እኚህን ሰው ኢንጂነር እያለ ሲያሞካሻቸው እንዳልነበር የተለመደውን ማዕረግ  «አቶ» እንኳ እንዲነፍጋቸው ያደረገው ጉዳይ ምንድነው? ማለታችን አይቀርም:: ከላይ ከላይ ሲታይ እኚህ ሰው የሚመሩት የፖለቲካ ፓርቲ ከገዥው ፓርቲና ከሌሎች ሁለት ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር በመሆን ተደራድረው የጋራ ስምምነት ላይ መድረሳቸው ይመስላል:: ግን ጉዳዩ ከዚያ በላይ እንደሆነ ከጋዜጣው ይዘት መረዳት ይቻላል:: ይህም ለጥላቻው መነሻ የሆነውን ስምምነቱን መፈረማቸው ሳያንስ ከሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ውጭ ሌላ አማራጭ እንደሌለ ከፊርማ ሥነ-ሥርዓቱ በኋላ መናገራቸው እንደሆነ በርዕሰ አንቀፁም ይሁን ዜና ተብሎ በቀረበው ጽሁፍ ላይ በግልጽ ተመልክቷል::

የአውራምባ ታይምስ ፀሐፊ ልበለው አዘጋጅ ኢንጂነር ኃይሉ ሻውልን አስመልክቶ በዚሁ እለት ባስነበበን ዘገባ እኚህ አዛውንት ብዙዎች በሩቅ በሚሉት  የተቃውሞ ፖለቲካ መድረክ በተለይ አንፀባራቂ ኮከብ ሆነው ከተከሰቱበት የ97 ምርጫ ወዲህ ባለፈው አርብ ከገዥው ፓርቲና ከሌሎች ሁለት ፓርቲዎች ጋር በጋራ ሲወያዩበት የቆዩትን ድርድር ከተፈራረሙ በኋላ ግን በርዕሳችን የተመለከተው (ኃይሉ ሻውል፣ ፖለቲከኛ? ልማታዊ ባለሀብት? ወይስ ሁለቱንም?) በሚል መጠይቅ ጉላ ብሎ መቅረብ ጀምሯል ሲል እቅጩን ነግሮናል::

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በኢንቨስትመንቱ ዘርፍ ስኬትን እየተቀዳጁ ከመጡ ወዲህ ከገዥው ፓርቲ ጋር ቅሬታ ቀርቶ በወዳጅነት መተያየት ጀምረናል በሚል የገዥውን  ፓርቲ ሰጥቶ ለመቀበል ሆደ ሰፊ መሆን ያወደሱት ኃይሉ ሻውል ከምርጫ 97 ማግስት  ሲያራምዱት ከነበረው አቋም መለወጣቸውን ለማስረዳት ጋዜጣው ሲሞክር ጥልቅ ሃዘን  እየተሰማው ጭምር ነው:: ልብ ይበሉ! ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኢንቨስትመንቱ ዘርፍ ስኬትን እየተቀዳጁ መጥተዋል የምትለዋን ሃረግ ቅሬታ ቀርቶ በወዳጅነት መተያየት ጀምረናል ከማለታቸው ጋር አያይዞ ለማቅረብ የፈለገው ሰላማዊ ትግልን መምረጣቸው ተገቢ አለመሆኑን ለማሳየት ብቻ እንደሆነ ሊገነዘቡ ይገባል::

ጋዜጣው የኢንጂነሩ የፖለቲካ ህይወት በሦስት ምዕራፎች እንደሚከፈሉ ይገልፃል:: ምዕራፎች ምን ምን እንደሆኑ በይፋ ለመግለጽ ወኔውንና አቅሙን ያጣ  መስሎ ቢፍረከረክም ምዕራፎቹን በጊዜ ገደብ ለያይቶ ስላስቀመጠው ክፍተቱን  አንባቢያን ራሳቸው እንዲሞሉበት ያሰበ ነው የሚመስለው:: በመሆኑም አንደኛው  ምዕራፍ ከእስር በፊት የነበራቸውን ጽንፈኛ አቋም ሲያመላክት፣ ሁለተኛው ከእስር ከተለቀቁ በኋላ በእርስ በርስ የፖለቲካ ሽኩቻ ውስጥ ያሳለፉትን፣

ሦስተኛው ደግሞ የሥነ-ምግባር ደንቡን ስምምነት ከፈረሙ በኋላ መሆኑን ያመላክታል:: የአውራምባ ታይምሱን ፀሃፊ ወይም አዘጋጅ ተብዬ ክፉኛ ያበሳጨውና በንዴት ቆሽቱን አሳርሮ ሊገድለው የደረሰውም ይኸው ሦስተኛው ምዕራፍ ማለትም ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ለመጀመር መዘጋጀታቸውን በይፋ የገለፁበት ክስተት ነበር::

ከዚህ ሁሉ በኋላ እንግዲህ የሚነግረን ኢንጂነሩ ስምምነቱን መፈረማቸው በአገር ውስጥና በውጭ የነበራቸውን ድጋፍ ዜሮ እንዳደረገው ነው:: 99 በመቶ የዳያስፖራ ድጋፋቸውን አጥተዋል ሲሉ የተለያዩ ድረ ገጾች ዘግበዋል ያለን አውራምባ ታይምስ የአንደኛውን ሥም እንኳን ለመግለጽ አለመቻሉ ራሱ የፈጠረው የቅዠት መረጃ መሆኑን አመላካች ነው:: ለነገሩ ይህን አኃዝ አሁን ግለሰቡ ሰላማዊ መንገድ ከመረጡ በኋላ ያላቸውን ድጋፍ ለማሳየት ተጠቅሞበት ከሆነ ያስማማናል:: ምክንያቱም ሰላም ወዳድ የሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ በፓርቲዎች መካከል አሁን የተደረሰውን ስምምነት በአዎንታዊ መንፈስ እንደተቀበለው መላው ህዝብ የሚኖርበት ገጠራማው ክፍል ድረስ ወርዶ ማረጋገጥን ይጠይቃልና አውራምባ ይህን ለማድረግ የሚያስችል ተቋማዊ አቋምም ፍላጎትም ይኖረዋል ብለን አንጠብቅም:: ሆኖም ይህን ለማድረግ ያልቻለ ግን ቢያንስ ሃሰት ሲነዛ ሕዝብ ይታዘበኛል ብሎ ሊያስብ ይገባዋል::

ግለሰቡ በአገር ውስጥም ድጋፍ እንዳጡ ለመግለጽ የሞከረው ጋዜጣው በርካታ አንባቢዎች ስልክ በመደወል «የምናውቃቸው ኃይሉ ናቸው ወይስ ሌላ? ከፖለቲከኛነታቸው ይልቅ ለሚያካሂዷቸው የኢንቨስትመንት ሥራዎች የተለየ ትኩረት የሰጡ ብለውናል በማለት ነው::

የጋዜጣው አዘጋጅ የጭቃ ጅራፉን ከማቆም በፊት ያንፀባረቀውን የጥላቻ መንፈስ ደግሞ ስንመለከት «የኡኡታ ፖለቲካ መቆም አለበት» የሚለው ቁርጠኝነት የተንፀባረቀበት አገላለጽ ምን ያህል እንዳበሳጨው የሚያስታውቀው ኡኡታው ይብቃ ማለታቸው ብቻ ሣይሆን ይኸው አቋማቸው ቁርጠኝነት የተንፀባረቀበት መሆኑንም ጭምር በመጥፎ ጐኑ በማየት ነው::

ከዚያም ጽሁፉን የሚቋጨው ቀጣዩ ሰው ማን ይሆን በሚል ፀረ ሰላም የሆነውን የስጋት ጥያቄውን በማስቀመጥ ነው::

እንግዲህ ጥለነው ወደመጣነው ጉዳይ ተመልሰን አውራምባ ታይምስ ለምን ይህን ሁሉ ሊል ቻለ ስንል ኢንጂነሩ የሰላምን መንገድ በመምረጣቸው መሆኑን ከላይ ለመግለጽ ተሞክሯል:: በማስከተል የጥላቻው ግብ ምንድነው የሚለውን ማየት አለብን:: ከጽሁፎቹ ይዘት ለመረዳት እንደሚቻለው ግቡ ኢንጁነሩን በማስፈራራት አሁን ከያዙት ሰላማዊ የትግል አቋም እንዲያፈገፍጉ ማድረግ ነው:: ከዚያ በመለስ ደግሞ የጥላቻው ዓላማ ሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎችንና አመራሮቻቸውን በማሸማቀቅ ወደ ሰላማዊ ትግሉ እንዳይቀላቀሉ ከወዲሁ ማስፈራራት፣ ማስጠንቀቅ እና መከላከል ነው:: አሳሳቢው አገራዊ ጉዳይም ይኼው ነው::

ሌላው ቀርቶ ሌሎች የግል ጋዜጦች ስምምነቱን ታሪካዊ ብለው መጥራታቸው ትክክል እንዳልሆነ ለመግለጽ ሞክሯል:: ይህንንም ጥቅምት 28 ቀን 2002 ዓ.ም የወጣው አዲስ ነገር ጋዜጣም ታሪካዊ የሚለውን ቃል የተጠቀሙ ሚዲያዎችን በማጣጣል ለአውራምባ ታይምስ ያለውን አጋርነት አሳይቷል:: በነገራችን ላይ እኒህ ሁለት ጽንፈኛ ጋዜጦች እርስ በእርስ በመሞካሸትና ፀረ ሰላም አጀንዳ በመቀያየር አንዱ ለአንዱ በተመጋጋቢነት እየሰሩ እንዳለ መገንዘብ

ይቻላል:: አውራምባ ታይምስ ኢንጂነሩ የኡኡታ ፖለቲካ ማካሄድ ፋይዳ የለውም፣ ከድርድር ውጪ ሆኖ መድረክ ጠቧል እያለ ከመጮህ ይልቅ ለኢትዮጵያውያን የሚጠቅመው ችግርን በክብ ጠረጴዛ ዙሪያ እየተወያዩ መፍታት ነው ማለታቸው ጋዜጣው ይዞት የተነሳውን ፀረ ሰላም አቋም የሚፃረር በመሆኑ ፀሃፊው ወይም አዘጋጁ በግለሰቡ ላይ ይህን መሰል ሰፊ የጥላቻ ዘመቻ እንዲከፈት አድርጓል::

በአጠቃላይ የአውራባ ታይምስ ዘጋቢን ወይም አዘጋጅን ለማስገንዘብ የምፈልገው ባለፈው በ97 ምርጫ እንደ ተከሰተው ሁሉ በመጪው ምርጫም ሁከትና አመጽ በማራገብ ላይ የተመሰረቱ ስሜታዊ ዘገባዎችን በማቅረብ መዋእለ ንዋይ አጋብሳለሁ የሚል ተራ ቅዥት አድሮበት ከሆነ ጊዜው ሰላማዊ ትግልን እንጂ ይህንን ለማራመድ የሚፈቅድ እንዳልሆነ ሁኔታዎች እያመላከቱ መሆኑን ልገልጽልዎት እወዳለሁ:: ሆኖም እንዲህ ዓይነት አፍራሽ አካሄዶች መጪውን ምርጫ ሰላማዊና ዴሞክንሲያዊ ለማድረግ የተጀመረውን መልካም ጅማሮ አደናቃፊ ናቸውና የሚመለከተው አካል ይህን ሁኔታ በንቃት በመከታተል ሰላም ፈላጊው ህዝብ የጣለበትን አደራ በአግባቡ ሊወጣው ይገባል እላለሁ::

ሰላም!

# «በስንት መከራ ያጠመድኩትን አውሬ አታባሩብኝ» ለማለት ይሆን?

**በደበበ እሸቱ**

**ለአውራምባ ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል**
**የአክብሮት ሰላምታዬን አቀርባለሁ**

ሰሞኑን በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ አውራምባ ታምስን አስመልክቶ የወጣውን እርግማን አየሁት:: አዘንኩ:: እና ይህቺን ደብዳቤ ላክሁላችሁ:: እያንዳንዱን ርዕስ በማንሳት መጻፍ ይቻል ነበር ግን እንደ አዲስ ዘመን አምዳችሁን ለእንካስላንቲያ ለማዋል ስለማይሆንላችሁና በርካታ ሕዝባዊ ጉዳዮች ስለሚኖሩ በአጭሩ ጽፌ ልኬዋለሁና ቦታ ካለችሁ አስፍሩልኝ::

ሰሞኑን በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ "ከዩኒቨርሲቲ" በሚል አድራሻ የቀረበ ረጅም አሰልቺ፤ ፍርሃት ፍርሃት የሚሸት፤ የደራሲውን አገልጋይነት በሚገባ የሚገልጽ፤ በአለቆች ተመዝኖ ለሽልማት የሚያበቃ ሊሆን ይችላል በሚል የቀረበ ጽሁፍ አየሁ:: ጸሃፊው እንኳንስ ዩኒቨርሲቲ ሊማሩ ቀርቶ፤ ለመብታቸው የቆሙ ተማሪዎችን ያዘው፤ አጋጨው፤ በለው ለማለት ካልሆነ ዝር ያሉበት አለመሆኑ ያስታውቅባቸዋል::

ወይም በሌላ ጊዜ ተማሪዎቹ አለፈቃዳቸው መስመር እንዲገቡ ይህ ይደረግልሃል ይህ ይሰጥሃል ብለው በድብቅ ጨለማን ተገን አድርገው ፎረም ለማስሞላት ካልሆነ በቀር ድርሽ ብለው የሚያውቁ አይደሉም፡፡

አንድ ሰው ከኖረበት ቤት የሚለቀው ወይም የመልቀቅ ሃሳብ ለቤተሰቡ የሚያሰማው፤ ኪራይ መክፈል አቅቶት ነው አሊያም በአካባቢው ካለው ሕብረተሰብ ጋር መኖር ስላልቻለ ነው፤ ካልሆነም በሰፈሩ ያለው ተቀባይነትና ተደማጭነት ባርቆበት ነው፤ ይህም ካልሆነ ሰውየው ትንሽ ነካ አድርጎት ነው ብሎ ወደምደምም ይቻላል፡፡

ኢንጂነሩ ደግሞ ከዚህ የተለየ አላደረጉም፡፡ በፓርቲያቸው ውስጥ ከሕመምም፤ ከመሳትም፤ ከዕድሜም፤ ከሥልጣን ፍለጋም፤ (የመጪውን ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ልብ ይሏል እሳቸው ደሞ መመዘኛውን ሁሉ ያሟላሉ፤ ከዘራም መያዝ ጀምረዋልና፤) የኖሩበት ቤት ምቾቱን እየቀነሰባቸው ተደማጭነቱም እየቀዘቀ፤ የጥቅምም ነገር በቃኝ የማይባልበት ነውና፤ ሌላ መንገድ ያዙ፡፡ ችግሩ መንገድ መምረጣቸው አይደለም ወደ መንገዱ ለመግባት የተጠቀሙበት የስርቆት በር መሆኑ ነው፡፡

"እኛ ለሕዝባችን" ተብሎ ሕዝብ በረሃብ አለቀ፤ ለስቃይ ተዳረገ - በጃንሆይ ዘመን፡፡ "ለሰፊው ሕዝብ" እየተባለ ሕዝብ በጥይት ተቆላ አስከሬኑ ሜዳ ላይ ተሰጣ - በደርግ ዘመን፡፡ "ለሕዝብ" በሚል አሁንም እንደገና ግፍ ተሰራ በደል ተፈጸመ - በኢህአዴግ ዘመን፡፡ «ለሕዝብ ፍላጎት ስል ነው ያደረግሁት» በሚል የሕዝብን ፍላጎት ያደበዘዘ፤ የሕዝብን አመኔታ ገደል የከተተ ተግባር ደግሞ ሊተገበር በሚስጥር በር እየተጓዘ ነው፤ በኢንጅነሩ አካሄድ፡፡ እና ይህን መናገር፣ የህዝብ አደራ በድብቅ አይብሉ ማለት ምን ክፋት አለው? ሰውን ከስህተቱ ጋር ከማቀፍ ስህተቱን ነግሮ በንጽህናው ማራቅ ይመረጣል እኮ፡፡

ሰውዬው ያነሱት በጣም አስቂኝ የሆኑና እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ሃሳቦችን አቅርበው የአውራምባን ቤተሰቦች ለማሳሰር፤ የአዲስ ነገርን ቤተሰቦች ለማስጠንቀቅ የተጠመደ እንደሆነ ጽሑፉ ያስረዳል፡፡ ይህ ደግሞ አዲስ አይደለም ላለፉት በርካታ ዓመታት የታየ ነው፡፡ የነጻው ፕሬስን ሰዎች ፍርድ ቤት ማቅረብ ዋስትና ካቅም በላይ መጫንና ገቢ ማድረግ አዲስ ክስተት አይደለም፡፡ ብቻ ክፋቱ ለሕዝብ የቆሙትንና በሕዝብ ፍላጎት ላይ ብቻ ትኩረት አድርገው ያንን ተግባራዊ ማድረግን የመረጡ ባለሙያ የነጻው ፕሬስ አባላትን ከቆሙለት ዓላማ ማናጠብ የማይሞከር ነው፡፡

ካነሱት አንድ አስቂኝ ጉዳይ ልጥቀስ፡- ከዚህ ቀደም ኢንጅነር እያሉ ሲያከብሯቸው የነበሩትን ሰው ዛሬ ኃይሉ ብለው ጠሯቸው ይሉናል፡፡ እራሳቸው ባለፈው ምርጫ ወቅት ፌውዳል፤ የማያውቅ፤ ያልገባው፤ ሕዝብን የሚያሳስት፣የደርግ ሹመኛ ... ሲላቸው የነበሩትን ሰውዬ ዛሬ ተደፈሩ ብሎ መቆጨት ምን ይባላል? መብትን ሲጠይቁ ውግዘት፤ ሲያጎበድዱና መርህ ሲጥሱ ምስጋና ነው ትክክለኛው ማለት ነው? ለማጎብደድና መርህ ለመጣስ የራስን ህሊና መካድ ያስፈልጋል ያን ለማድረግ ደሞ አሁን ወቅቱ አይደለም ያረጀ ዘዴ ነው፡፡ ያን ማድረግ ከራስ ጋር መጣላት ነው፡፡

«የዩኒቨርሲቲው» ሌላ ያነሱት ጉዳይ ጸሃይ የሞቀውን እውነት ለመካድ የሞከሩበት ነው፡፡ ሁለቱንም ጋዜጦች ባለፈው ምርጫ የፈጠራ ወሬ እየጻፉ ጋዜጣቸውን እንደሸጡ እንደማለት

ሞክሯቸዋል:: ባለፈውማ ነጻው ፕሬስ ተገቢውን ሚና ተጫውተ፤ ሕዝብ የማወቅ መብት አለው የሚለውን ዲስፕሊን በአግባቡ ተወጣና ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ ፍርድ ተጭኖበት ጠፋ:: እርስዎስ የዚህ የደባው ፈጠራ አካል ሆነው እያለና በቃልም ለይስሙላም ቢሆን ሃሳብን በነጻ ማንሸራሸር መብት ነው የሚለው ሃይል አካል ሆነው እንዴት በአደባባይ የድርጅትዎን ሚስጢር ይፋ ያወጣሉ? ያሉበትን ድርጅት ሚስጥራዊ አሰራር ይፋ አውጥተዋልና መገምገም አይቀርልዎትም::

ጸሃፊው አዲስ ዘመንን ምን ያህል ቢቆጣጠሩት አሊያም ቢያዙት ነው ያን ያህል ገጽ መስጠቱ:: ጽሁፍ አኮ በበዛ እውነት አይሆንም:: ፍሬ ሃሳቡን አውጥተን የኚህን የዩኒቨርስቲው ነኝ ባይ ሰው ጽሁፍ ብንመለከተው የሚያስተላልፈው መልእክት አጭር ነበር:: «አውራምባና አዲስ ነገር በራሳቸው የሚተማመኑ የተሳሳተውን የሚያጋልጡ ፤ ዕውነት የሚያቀርቡ፤ ሕዝባዊነታቸው የተረጋገጠ ስለሆነ አልተመቹንምና ይወገዱ» ማለት ነው:: በቃ:: አጠረም በዛም መልዕክቱ ይኸው ነው::

ለነገሩ ከጽሁፉ የቃላት አደራደር ከየት እንደወጣ ማወቅ አያስቸግርም:: ቁጭቱ ለኢንጅነሩ በመቆርቆር ሳይሆን «በስንት መከራ ያጠመድኩትን አውሬ አታባሩኝ» ለማለት ይመስላል::

ውድ የ«ዩኒቨርሲቲው» እባክዎ ስለበቀደሙ ፊርማና መጨባበጥ ለምን መንገድ ላይ የሕዝቡን ስሜት አታደምጡም:: አውራምባ ከገለጸው በበለጠና በመረረ መንገድ ተከዳን ብሎ እየተናገረ ነው:: ሃይሉ ሻውል ከምርጫ 97 ማግስት የጀመሩትን የቤት ስራ ጨረሱ ብሏል::

በሃገራችን የተለመደው የፖለቲካ ሂደት የመረጠናቸውን ወይም ተመርጠናል ብለው ሥልጣን ላይ ያሉትን አቤት አቤት! ጌታዬ፤ የተነፈሱት ሁሉ መድሃኒትነት የተናገሩት ሁሉ ዴሞክራሲያዊ ባይሆንም የሆነ፤ ከእርስዎ ሌላ ማንም በማለት ብቻ እጅ ባወጡ እጅ ሰቅለን፤ በተቆጡ ደንፍተን፤ የተናገሩትን ሁሉ እንደበቀቀን ሌት ተቀን ደግመን፤ ያልሆኑትን አንደዓምላክ ሰግደንላቸው መኖርን ነው::

ዘመኑ ደሞ በሉና የራሳችሁ የሆነውን የምታምኑበትን፤ ቃል የገባችሁለትን፤ ራዕይ ብላችሁ የተነሳችሁበትን ተግባራዊ የሚያደርግ መሆን አለበት በሚል በሰለጠነ ፖለቲካ መስመር ሂዱ እያለን ነው:: ጊዜው የተቀበለውም ያን ነውና እንደ ግመል ሽንት ወደኋላ አይመልሱን::

አንድ ተረት ልንገርዎ የ«ዩኒቨርሲቲው» በፓርቲው አባላት እግዚኦ እግዚኦ እየተባለ አላቅሙ ይወደስ የነበረ ሰው ወደ ማይቀበሉትና አካሄድህ ትክክል አይደለም ብለው ዕውነቱን ተናግረው ተለይተውት ለዕውነት ከቆሙት ሰፈር በስውር እንዳይታወቅ ሆኖ ይደርሳል:: የዚያ ግድም ሰዎች ደግሞ ብልሆች ናቸውና ወዲያው ቢያውቁትም እንዳላወቁ ሆነው ማስተናገድ ያዙ:: ምን እንደሚፈልግ ሲጠይቁት አንድ ሙሉ ልብስ ለማሰፋት ነበር ወዲያ ካለሁበት ሰፈረ ጠይቄ 4 ሜትር ተኩል ያስፈልግሃል ቀጠሮውም ከሁለት ወር በኋላ አሉኝ ከዚህ አልፎ ያለውም ተመሳሳይ ሆነብኝና እዚህስ ምን ትለኛለህ አለው ሰፊውን::

ሰፊው ሳይለካው ሳይመትረው 1 ሜትር ከሩብ ይበቃሃል ማታ ይደርስልሃል ሲለው ተገርሞ ሳይከራከር የተባለውን ጨርቅ 1ሜትር ከሩብ አምጥቶ ሰጥቶ ለማታ ቀጠሮ ተለያዩ:: ማታ አሰፊው ሲመጣም ሙሉ ልብስ ከነሰደሪያው ተሰፍቶ እሩብ ሜትር ጨርቅ ትርፍ ነው ተብሎ ተመለሰለት

ሂሳቡን ከፍሎ ከተረከበ በኋላ ተገርሞ እንዴት እንዴት ሆነ? ሲላቸው፤ «አዩ ሰውዬው እርስዎ እዚያ እናንተ ሰፈር ትልቅ ሆነው ቢታዩም እዚህ እኛ ሰፈር ግን በጣም ትንሽ ነዎትና ለዚህ ነው የበቃዎት» ብሎ ሸኘው።
ለእኚህም ጸሃፊ ባሉበት የተከበሩ የተናገሩት ሁሉ እኔን ተብሎ ተቀባይነት ማግኘት ለምዶባቸው ከሆነ እዚያው እለመዱበት እንጂ ሕዝቡ በዚያ ደረጃ አያይዎትምና በከንቱ አይልፉ።

አመሰግናለሁ።

ነጻነት ለኢትዮጵያ

# ጸረ-ሰላምነት ወይስ ልማታዊ ጋዜጠኝነት?

**በውብሸት ታዬ**

በአብዛኞቹ ታዳጊ አገራት እንደሚታየው ሁሉ በአገራችም ስር የሰደዱ የሙስና ተግባራት፣ አድሎአዊና ብልሹ አሰራሮች፣ በተዛባ የፖለቲካ ወገንተኝነት ጦስ የሚቀጣጠሉ ውዝግቦች፣ ለአገርና ለህዝብ ከመቆርቆር ይልቅ ስግብግብነትና እኔነትን መሰረት ያደረጉ ምዝበራዎች በስፋት ይፈፀማሉ። ፍትህ ይዛባል፣ የግል ጥቅም ለማካበት ሲባል ማህበረሰቡ ይበዘበዛል። በዚህም ከሚባክነው የአገርና የሕዝብ ሐብት በተጨማሪ ሰላም ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር አደጋ ላይ ይወድቃሉ። ይህ ለምን ሆነ? ብለን መጠየቅ እንችላለን።- ከአንድ ገለልተኛ የሚዲያ ተቋም የሚጠበቅ በመሆኑ መጠየቅም አለብን።

አድሎአዊና ብልሹ አሰራሮች የሚሰፍኑት፣ በተዛባ የፖለቲካ ወገንተኝነት ጦስ የሚከሰቱ ውዝግቦች ህይወት አካልና ንብረት የሚያጠፉትና ምዝበራ የሚስፋፋው ተጠያቂነት በማጣት፣ የህግ የበላይነት በግለሰባዊ ልእልና ሲጨፈለቅ፣ ይህን እንዋጋለን የሚሉ አካላት ቁርጠኝነትም በእጅጉ ያነሰ ሲሆንና በመሳሰሉት ነው።

እንዲህ በመሆኑም የታሪካችን አንዱ አካል ሆኖ የተጣባን ድህነትና ርሃብ እንዲቀጥሉ የተመቻቸ ሁኔታ ተፈጥሮላቸዋል። ማሕበራዊ ደህንነት በየጊዜው እየተቃወሰ፣ የዜጎች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እየተጣሱ፣ የገነባናቸው መንፈሳዊ እሴቶች ተሸርሽረው መተማመን እየጠፋ እንዲሄድ እየተደረገ ነው። ሊታረሙ የሚገባቸው ህፀፆች እንደትክክለኛ ተግባር ተቆጥረው ሲሞካሹ ገንቢ አስተሳሰቦችና መፍትሄ አመላካች ሙከራዎች ደግሞ ሲብጠለጠሉ እንመለከታለን።

እንደእውነቱ ከሆነ የችግሮቹ ሽክሞች ተቆጥረው አያልቁም። በተለይ ከ50 በመቶ በላይ የሚሆነው ህዝባ ከድህነት ጠለል በታች የሚኖሩባት አገራችን ከሌሎች የበለጠ ትግል በማድረግ ያሉብንን ችግሮች ፈልፍሎ የማውጣትና የመፍትሄ አማራጮችን መጠቆም የግድ ይሆናል። ለዚህም ኃላፊነት የሚሰማቸው የመገናኛ ብዙሃን የሚጫወቱት ሚና በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

ይህ የመገናኛ ብዙሃን ኃላፊነትን በአግባቡ የመወጣት ሚና እንዴት ይገለፃል? በምጣኔ ሃብታዊ፣ ባህላዊና ማህበራዊ፣እንዲሁም ፖለቲካዊ መስኮች ያሉ ጎታችና አፍራሽ ተግባራት በመንግስታዊ የተጠያቂነት እሴትና የአጋላጭ መረጃዎች ትሩፋት እንዴት መጠቀም ይቻላል?

የመገናኛ ብዙሃንና የመረጃ ነፃነት አዋጅ የተደነገገበት አንደኛው ምክንያት አጋላጭ መረጃዎችን ለመሰብሰብና ለማሰራጨት ነፃ የመገናኛ ብዙሃን ህልውና እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ እንደሆነ በመግለጽ ለሁነቱ የተሰጠውን ትኩረት ለማመላከት ይሞክራል:: የድንጋጌውን መርሆች ታሳቢ በማድረግ በመንግስት ቁጥጥር ስር ያሉ የፕሬስ ውጤቶች ይህን የመንግስታዊ ተጠያቂነት እሴት በማረጋገጥ እንዲሁም የአጋላጭነትን ሚና በመሸከም በኩል ያላቸው ታሪክ እንዴት ይመዘናል? በተለይ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ እነዚህ ፕሬሶች አገራችንን የዓለም ጭራ ያደረጓትን የመልካም አስተዳደር እጦቶች፣ አድሎአዊ አሰራሮች፣ የመብት ጥሰቶችና የስነ ምግባር ዝቅጠቶች በማጋለጥ ፖሊሲውንና ስትራቴጂውን የሚያራምዱለት መንግስት እርምጃ እንዲወስድ የሚያስችሉትን አይነተኛ ኃላፊነቶች ከመወጣት ይልቅ ይህን የሚያደርጉትን «ድክመትን ብቻ የሚመዙ፣ ተስፋ የሚያስቆርጡ፣ ጥላቻን የሚነዙ» በማለት እንደኛ አስቡ፣ እንደኛ «ተመረቀ፣ ተፈረመ፣ ተጀመረ፣ ተጠናቀቀ» ብቻ በሉ ከማለት አልፈው «ፀረ-ሰላም» እስከማለት የዘለቀ አጉራ ዘለልነትን እያስተናገዱ ነው:: ይህም ቀጥሎ ያለውን ጥያቄ እንድናነሳ ያደርገናል::

## ልማታዊነት - እንዴት? ልማትስ?

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማሕበር «ርዕይ 2020» በሚል ባዘጋጀው የውይይት መድረክ ላይ ዘሪቱ ንዳ እና ጎኛም ቦጋለ የተባሉ እንስት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በልማትና የሰው ኃይል ዙሪያ ባቀረቡት ጽሁፍ አንዲት አገር አደገች ለማለት ስለሚያስችሉት ግብአቶች ባቀረቡት ትንታኔ «አንድ አገር አድጋለች የሚባለው ባላት ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ስትራቴጂዎች እንዲሁም ባህላዊ እሴቶች በፊት ከነበራት አቅም አንፃር ተሻሽላ እና ይበልጥ ጐልብታ እንዲሁም ከሌሎች አገሮች ጋር ሲነፃጸር ከፍተኛ ሆና ስትገኝ ነው::» ብለዋል:: በዚህ ትንታኔ የማይስማማ ወገን ይኖር ይሆን? የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ጽ/ቤት የሚያሳትማት «ኢትዮጵያ» የተሰኘች መጽሔት ደግሞ 85 በመቶ ያህሉ ሕዝብ በግብርና ስለሚተዳደርባት አገራችን አርሶ አደሮች የኑሮ ሁኔታ የገጠር ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ ውጤት በሚል የሚከተለውን አስፍራለች::

«...የሚሊዮን ብሮች ባለቤት የሆኑ፣ ትራክተር፣ ኮምባይነርና አይሱዙ የገዙ፣ ጋራዥ ሆቴልና ዘመናዊ መኖሪያ ቤት የገነቡ እንዲሁም በተለያዩ የኢንቨስትመንት መስኮች መሳተፍ የጀመሩ በርካታ ቁጥር ያላቸው ሞዴል አርሶ አደሮች በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች ተፈጥረዋል::...» ይህን አማላይ ጽሁፍ የሚያነብ፣ ምናልባት ኢትዮጵያ ስለምትባለው አገር ሙሉ መረጃ የሌለው ሰው እንደዚህ የሚነገርላት አገር በኢኮኖሚ ደረጃዋ ዓለምን ከሚመሩና ለኑሮ አመቺ ከሆኑት አገራት አንዷ እንደሆነች ሊገምት ይችላል:: ከረድኤት ተቋማት ያገኘነውን የእርዳታ እህል

እያብቃቃን የወገኖቻችንን ህይወት ለማቆየት የሞት ሽረት በምናደርግበት ሁኔታ ጋራዥና ዘመናዊ መኖርያ ስለገነቡ አርሶ አደሮች የምናወሳበት የልማታዊነት ስሌት ያለውን የተዛባ ግንዛቤ ማጤን የግድ ይላል::

በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች ተፈጥረዋል ስለተባሉት የሚሊዮን ብሮች ባለቤት አርሶ አደሮች ስለኮምባይነሩ፣ ስለአይሱዙው፣ ስለሆቴልና ዘመናዊ ሆቴል ግንባታው ሲነሳ ግን «አንድ አገር አደገች የሚባለው...» በሚል የምጣኔ ሃብት ሳይንስ ታሳቢ የሚያደርጋቸውን ግብአቶች ስንመረምር ልማታዊነት በ«ተመረቀ፣ ተፈረመ፣ ተጀመረ፣ ተጠናቀቀ» ዘገባዎች የእጅግ አስፈላጊ ነጻ የመገናኛ ብዙሃንነት ሚናን መወጣት እንዳልሆነ ለማመት ጠቢብ መሆንን አይጠይቅም:: ከትናንት ዛሬ ተሽሏል? ከሌሎች አገራት ጋር ያለው ንጽጽርስ ምን ይመስላል?

በሌላ በኩል ከታክስ በፊት ስለተገኙ የቢሊዮን ብር ትርፎች፣ በማህበር ስለተደራጁ ወጣቶች ስብሰባ መካሄድ እና ወዘተ በመዘገብ የተፈረመ፣ ተመረቀ፣ ተጀመረ ተጠናቀቀ ዜና ሃተታ ሙያውን «ልማታዊ» የሚያሰኘው ከምን አንጻርና በየትኛው ሳይንስ ነው? እነዚህ አዘጋገቦች ብዙ ሙያዊ ትንታኔዎች ውስጥ መግባት ሳያስፈልግ የመንግስታዊ አሰራርና የተጠያቂነት እሴቶችን የሚያዳበሩና «ልማታዊነት» ከተሰኙ ቀጥሎ የምንመለከታቸውን፤ ለአገር ተቆርቋሪና ሃላፊነት የሚሰማቸው የባለድርሻ አካላት ከተገኙ ፖሊሲዎቻቸውንና አሰራሮቻቸውን ለመመርመር የሚያነሳሱ ዜናዎችስ ምን ሊሰኙ ነው?

ለውድ አንባቢያን ንጽጽር ይረዳ ዘንድ በግል ፕሬሶችና በመንግስት ይዞታ ስር ባለው አዲስ ዘመን ጋዘየጣ አማካኝነት እየቀረቡልን ያሉ ዜናዎችን ጎን ለጎን እንመልከታቸው

# በግል ፕሬሶች ከተሰሩ ዜናዎች መካከል ጥቂቶቹን እነሆ

- በየዓመቱ 75 በመቶ የሚሆኑ የተማሩ ኢትዮጵያውያኖች ከአገር ወጥተው እንደሚቀሩ ተገለፀ::

**ፍትሕ - ጥቅምት 13 ቀን 2002 ዓ.ም**

- ከቻይና ብድር ባለመገኘቱ የሙገር ማስፋፍያ ማጠናቀቂያ ተራዘመ

**እንቢልታ - ግንቦት 22 ቀን 2000 ዓ.ም**

- የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ከሩብ ሚሊዮን ብር በላይ ያስከፈለበትን አሰላ ራስ ሆቴልን ለከፋዮቹ አላስረከበም

**ኢኮኖሚ - ሐምሌ 10 ቀን 2001 ዓ.ም**

- መድረክ የምርጫ ቦርድ ለፓርቲዎች ያስተላለፈውን ጥሪ ተቃወመ

**ሰንደቅ-ጥቅምት 25 ቀን 2002 ዓ.ም**

- የምስክርነት ቃሉን የሰጠው የአንድነት አባል ወደመጣበት ሲመለስ ንብረቱ እንደወደመበት ገለጸ

***መሰናዘሪያ ጥቅምት 24 ቀን 2002 ዓ.ም***

- አዲስ አበባ የዓለም 6ኛዋ የቆሸሸች ከተማ ተባለች

**ኤ.ቢ.ቢ.አይ - *መጋቢት 5-11 2000 ዓ.ም***

- የጉግል ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ያለ ፍ/ቤት ትዕዛዝ በቁጥጥር ስር ዋለ

**ጉግል - የካቲት 6 ቀን 2001 ዓ.ም**

- የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ 690 ሰራተኞች ከሥራ ተሰናበቱ

**አዲስ አድማስ - ነሐሴ 2 ቀን 2001 ዓ.ም**

- ከ540 በላይ አርሶ አደሮች «የንብረትና የአካል ደህንነት መብታችን ተገፈፈ» ሲሉ ለጠ/ሚ/ሩ አመለከቱ

**አውራምባ ታይምስ- ህዳር 01/2002**

- አራት ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ለንደን ላይ ጠፉ

**ኢትዮ ቻናል - ነሐሴ 23 ቀን 2001 ዓ.ም**

- ቅድሚያ ክፍያ ካርድ ለማከፋፈል ጨረታ ያሸነፉ ተጫራቾች ሳይሰጠን አመት አለፈን አሉ -

እያንዳንዳቸው መቶ ሺህ ብር አስይዘዋል

***ሪፖርተር ጋዜጣ - ጥቅምት 11 ቀን 2002 ዓ.ም***

# በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከተሰሩ ዜናዎች በጥቂቱ

- አርሶ አደሮች የተፈጥሮ ማዳበሪያ እያዘጋጁ ነው (ጥቅምት 6 ቀን 2002)
- የአማራ ወጣቶች ማህበር የሽግግር መድረክ ሆኖ ማገልገሉ ተገለጸ (ጥቅምት 6 ቀን 2002)
- በምዕራብ አርሲ:- የደረሰ ሰብል በዘመቻ ሊሰበሰብ ነው (ጥቅምት 7 ቀን 2002)
- የጎንደር- ደባርቅ የጠጠር መንገድን ወደ አስፋልት የማሳደግ ስራ ተጀመረ (ጥቅምት 8 ቀን 2002)
- በአፈርና ውኃ ጥበቃ ስራ የታየው ለውጥ ለአፍሪካም በምሳሌነት ሊጠቀስ ይችላል (ጥቅምት 9 ቀን 2002)

ከላይ የተመለከትናቸውና በአራት ቀናት ውስጥ በተከታታይ የወጡ የአዲስ ዘመን ዜናዎች እንዲሁም የተለያዩ የግል ሚዲያዎች የዘገቧቸውን ዘገባዎች ከአዲሱ የመገናኛ ብዙሐንና የመረጃ ነጻነት አዋጅ አንጻር እንመልከታቸው:: አዋጁ በመግቢያው ላይ «... መገናኛ ብዙሀን አጋላጭ የሆኑትን ጨምሮ መረጃዎችን የመሰብሰብና የማሰራጨት መብት ያላቸው መሆኑን በመገንዘብ ... በህገ መንግስቱ የተረጋገጡትን ግልጽ መንግስታዊ አሰራርና የተጠያቂነትን እሴቶች ለማዳበርና ይበልጥ ለማጠናከር እንዲሁም የህዝብ ጥቅምን የሚመለከቱ ጉዳዮች ይፋ ወጥተው ህዝብ

እንዲወያይባቸው ለማድረግ ይቻል ዘንድ ለመገናኛ ብዙሐን መረጃዎችን የማቅረብ ግዴታ» ማመቻቸቱን ያትታል:: ታዲያ ከእነዚህ ዜናዎች ውስጥ አጋላጭና አስፈጻሚውን አካል ለእርምት የሚያነሳሱ ዜናዎች የትኞቹ ናቸው? ከ540 በላይ አርሶ አደሮች የንብረትና የአካል ደህንነት መብታችን ተገፈፈ መፍትሄ ይሰጠን ማለታቸውን ወይስ አርሶ አደሮች የተፈጥሮ ማዳበሪያ እያዘጋጁ መሆናቸውን ማቅረብ? ዜናው እንደ ዜና መቅረቡን መቃወማችን ሳይሆን ማዳበሪያ እያዘጋጁ መሆናቸውን መዘገብ «ልማታዊ ጋዜጠኝነት»፤ አርሶ አደሮች መብታችን ተገፈፈ እያሉ ነው የሚመለከተው አካል ተገቢው መፍትሄ ይስጣቸው ብሎ ተጠያቂነት እንዲኖር መወትወት «ጸረ-ሰላምነትና ጥላቻን አራማጅነት» የሚሆነው በየትኛው መመዘኛ ነው? አዲስ አበባ የዓለም 6ኛ ዋ የቆሸሸች ከተማ ተብላለችና የሚመለከተው አካል ገጽታችንን ለመለወጥ ህዝብን ያስተባብር ማለት ተስፋ አስቆራጭና ጥላቻን ማራመድ፤ ሰብል በዘመቻ ሊሰበሰብ ነው ብሎ በዜና ገጽ ማወጅ ግን አገር ወዳድነትና ፍቅርን ሰባኪነት? ፍርዱን ለእርስዎ ትቻለሁ::

# ብርቱካን ከእስር እንድትፈታ ያለው አማራጭ . . .

በግዛው ለገሰ

«የሕግ የበላይነት» የመንግስት ኃላፊዎችን ጨምሮ ማንኛውም ሰው ከሕግ በላይ መሆን እንደማይችል የሚያመላክት መርህ ብቻ ሳይሆን የትኛውም የመንግስት እርምጃ በግልጽ የተደነገጉ ሕጎችን የተከተለ ይሆን ዘንድ የሚያዝ መሠረተ-ሥርዓት ነው:: በእርግጥ ተግባራዊ የሚሆነውም ሆነ የበላይነት ዙፋን የሚሰጠው ሕግ መሠረታዊ የሕግነት መርሆዎችን (principles of legality) ማዕከል ያደረገ መሆኑ ዋነኛው የሕግ የበላይነት ርዕሰ-ጉዳይ ነው:: ይኸውም ፍትሃዊነት ለጎደለው፣ መሠረታዊ የሕግ አወጣጥ ሥርዓትን ላልተከተለ፣ አልያም ጥቅልነት ላጠረውና ለአንድ ወይም ለተወሰነ ዓላማ ብቻ ለፀደቀ ሕግ የበላይነት ቦታ መስጠትም፣ ተግባራዊ ማድረግም የሕግ የበላይነትን አያሰፍንም::

ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ ሁለት በልዩነት ላይ የነበሩ ወገኖች የሕግ የበላይነትን ግዙፍነት በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ ያወደሱበትን ክስተት እናስታውስዎ:: ሁለቱ ወገኖች ኢትዮጵያ መንግስት እና ወ/ት ብርቱካን ሚዴቅሳ ሲሆኑ፣ ይህ የሆነውም ብርቱካን ዳግም ወደ እስር ቤት በተመለሰች ሰሞን ነው:: ምርጫ 97ን ተከትሎ በተከሰተው ታሪካዊ ቀውስ በወቅቱ ጉልህ የፖለቲካ ተፎካካሪ የነበረው ቅንጅት አመራሮቹ ዓመት ከስምንት ወራት ከታሰሩ በኋላ የይቅርታ ሰነድ ፈርመው መፈታታቸው ተሰማ:: ዓመት ከአምስት ወራት ገደማ አለፈ፤ በዚህ ጊዜ ውስጥ ብርቱካን የአንዱ ቅንጅት ስንጣቂ፣ የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ ሊቀመንበርነትን በመያዝ ፖለቲካውን

ዳግም ትያያዝ ጀምራለች፡፡ የፓርቲዋንም ዓላማ ለማስተዋወቅ ወደ አውሮፓ አገራት በማቅናት የተለያዩ ህዝባዊ ንግግሮችን አደረገች፤ በስዊዲን አገር የተናገረችው ግን እዚያው አልቀረም - ተከትሏት አገር ቤት ድረስ መጣ፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት «በስዊዲን አገር የይቅርታ ሰነድ አልፈረምኩም ያልሽውን በሦስት ቀናት አስተባብይ» ሲል ብርቱካንን ጠየቀ፡፡ የብርቱካን ምላሽ «ምን አልባትም የመጨረሻ ቃሌ ይሆናል» የሚለውን ዓረፍተ ነገር ከመግቢያው አካባቢ ባሰፈረው «ቃሌ» በተሰኘው ጽሁፏ የተገለፀ ነበር፡፡ በዚህ የመጨረሻ ቃሏ ብርቱካን በሽማግሌዎች አማካኝነት መንግስትንና ሕዝብን ይቅርታ መጠየቋን ያልካደች ቢሆንም «በሕግ በተሰመረ አግባብ የይቅርታ ጥያቄ አላቀረብኩም» ማለቷም አይዘነጋም፡፡

ከጥቂት ቀናት በኋላም ወ/ት ብርቱካን ዳግም መታሰሯና የቀደመው የእድሜ ልክ ፍርድ እንደፀናባት ተሰማ፡፡ መንግስት በበኩሉ ይህ «የሕግ የበላይነትን» የማስፈን እርምጃ ስለመሆኑ በተለያዩ መድረኮች የገለፀ ሲሆን፣ ብርቱካንም በመጨረሻ ቃሏ «ሁሌም የምኖርለት፣ የምቆምለት፣ አንዳንዴም የምታሰርለት እና የምፈታት ታላቅ ቁም ነገር - የሕግ የበላይነት ወይም ሕገ መንግስታዊነት» በማለት የሕግን የበላይነት መስክራለች፡፡

እነሆ የሁሉ መነሻ የነበረው ምርጫ 97 አምስት ዓመታትን አስቆጠረና ሌላ ምርጫ መጣ፡፡ ወ/ት ብርቱካን ከቅርባችን ባለው የ2002 ምርጫ ይቅርና ከዚህ በኋላም በሚመጡ ምርጫዎች ላይ ደግማ ደጋግማ እንደምትታወስ ጥርጥር የለንም፡፡

የዚህ ጽሁፍ ዓላማ የወ/ት ብርቱካን ዳግም መታሰር ላይ የሚያነጣጥር አለመሆኑን፣ ይልቁንም ዳግም መፈታቷ ላይ የሚያውጠነጥን ስለመሆኑ ልንገልጽ እንወዳለን፡፡ የወ/ሪት ብርቱካን ደጋፊዎች የእርሷን መፈታት አጥብቀው ይፈልጋሉ፤ እንደውም መጪው ምርጫ ይበልጥ ሲቃረብ ኢሕአዴግ ለነጥብ ማስመዝገቢያነት ሊፈታት እንደሚችል ግምታቸውን የሚሰጡ አሉ፡፡ «የአሳሪዎቿን ልብ አራርቶ» ብርቱካን ትፈታላቸው ዘንድ የሚማፀኑ ወገኖችም አሉ፡፡ ለመሆኑ የመንግስት ሩህሩህነት ለብርቱካን መፈታት አስተዋጽዖ ይኖረው ይሆን? ሰሞኑን ደግሞ «የፖለቲካ እስረኛ መሆኗን እና አለመሆኗን እናጣራለን» የሚሉ ወገኖችንም ሰምተናል፡፡ የማጣራቱ ሂደት በምን መልኩ ሊካሄድ እንደታሰበ ባይታወቅም፤ መንግስት በሕግ መሠረት እንደታሰረችና የፖለቲካ እስረኛ ሳትሆን የሕግ ታራሚ መሆኗን እንደሚያምን፤ ሌሎች ደግሞ ምንም ጥፋት ሳታጠፋ ለእስር የተዳረገች የፖለቲካ እስረኛ፡፡ ታዲያ ብርቱካን ልትፈታ የምትችልበት መንገድ የትኛው ይሆን?

## የፖለቲካ እስረኛ/የሕግ ታራሚ

የፖለቲካ እስረኛ ማለት በፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎቹ ወይም በፖለቲካ እምነቱ ሳቢያ የታሰረ ሰው ነው፡፡ በአሜሪካ የሲቪል ራይትስ አክቲቪስት እና ጸሀፊ አንጄላ ዳቪስ የፖለቲካ እስረኛ ጥፋት በፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ጐልቶ መታየቱ ብቻ እንደሆነ ይጠቁማሉ (The offence of the political prisoner is his political boldness)፡፡ እናም መንግስት ብርቱካንን መልሶ ያሰራት ከቅንጅት ፈጣን ክፍፍል በኋላ በተቃዋሚው ጐራ ገዝፋ እየወጣች የነበረች ፖለቲከኛ በመሆኗ ነው ብለው

የሚያምኑ ብዙዎች ናቸው:: በዚህም አማካኝነት የመፈቻዋ መንገድ አንድም የመንግስት ልብ መራራት፣ ሁለትም «ድርድር» እንደሆነ እየገለፁ ነው:: ይሁንና ግን ይህ የኢሕአዴግን አካሄድ ጠንቅቆ ካለማወቅ የመነጨ ይመስለናል::

በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ተከታትለው የወጡ ሕጐችን በአንክሮ የተመለከተ ሰው የኢሕአዴግን አካሄድ ለመገንዘብ አያዳግተውም:: ኢሕአዴግ ማንኛውንም እርምጃ ለመወሰድ ሕግን መሠረት የሚያደርግበት አንድ የሆነ መንገድ ይፈልጋል፤ ያገኛልም:: የብርቱካንን ጉዳይ በተመለከተ በዚያኛው ጎን የሚባለውን ሁሉ ለጊዜው በመተው የመንግስትን እያንዳንዱን አቅጣጫ ብንመለከት የምናየው ይኼንኑ ነው:: ብርቱካን በመጨረሻ ቃሏ «በሕግ በተሰመረ አግባብ የይቅርታ ጥያቄ አላቀረብኩም» ማለቷ ለሁሉም የመንግስት እርምጃ መነሻ ነው:: መንግስትም ይህንን ምላሿን መሠረት በማድረግ፣ በይቅርታ ሥነ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 395/1996 አማካኝነት የይቅርታ ጥያቄ አለመቅረቡን በመግለጽ ወ/ት ብርቱካንን በተመለከተ የተሰጠው ይቅርታ «የተጭበረበረ» ነው ሲል ደመደመ:: እናም በዚሁ አዋጅ «ይቅርታን ስለመሰረዝ» በሚል ርዕስ በአንቀጽ 16 ላይ ከተደነገጉ ሁኔታዎች አንዱን በመምዘዝ እርምጃውን ወሰደ:: ብርቱካንም ከመንግስት አኳያ የሕግ ታራሚ ሆነች:: የትኛውም ወገን መጥቶ በፖለቲካ አቋም የታሰረችውን ብርቱካንን ፍታት ቢለው አንቀጽ በመጥቀስ የሕግ ታራሚ ስለመሆኗ የሚያስረዳበት መንተራሻ አለው:: ስለዚህ መንግስት ለነጥብ ማስመዝገቢያም ሆነ ለሀገሪቱ የፖለቲካ መንፈስ ብርቱካንን የመፍታት እቅድ ቢኖረው እንኳን አንድ የሚመረኮዝበት ሕግ ይፈልጋል፤ ምክንያቱም ብርቱካንን ያለምክንያት መፍታት፣ ያለምክንያት ማሰርን ያመላክታልና::

## የመንግስት ሩህሩህነት

(ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማሪያም 10ኛ የቃሌ ምሽትን በጸሎት በከፈቱበት ዕለት «የአሳሪዎቿን ልብ አራርተህ እንድትወጣልን አድርግልን» ብለው ነበር::)

መራራት የግለሰብ ባህሪ ነው:: በእርግጥ መንግስት የግለሰቦች ስብስብ ነው፤ ነገር ግን የግለሰቦች ስብስብ ሁሉ መንግስት አይደለም:: በሰለጠነ ግንዛቤ ሲቃኝ የመንግስት ሚና ማስተዳደር ነው:: ህዝቡ ሰላማዊ አንቅልፍ እየኮመኮመ ያድር ዘንድ ቆመው የሚያስተዳድሩት የተወሰኑ ግለሰቦችን መልምሎ ሰየመ:: እነዚህ በጥቅል መንግስት የሚባሉት ግለሰቦች የህዝብ ሹሞች፣ ተወካዮች፣ ተቀጣሪዎች ሲሆኑ ለእርምጃዎቻቸው ሁሉ ምክንያታቸውን ለህዝብ ያሳውቃሉ:: በመርህ ደረጃ ካየነው የኢትዮጵያ መንግስትም የነዚህ ግለሰቦች ስብስብ ነው::

ለብርቱካን መፈታት የመንግስት መራራትን እንደ አንዱ መንገድ ስንመለከተው መሠረታዊ ጥያቄዎችን ያስነሳል:: የብርቱካንን መፈታት አብዛኛው ሰው ይፈልገዋል፤ የመንግስት ኃላፊዎችም ቢሆኑ በግላቸው ይህንን ሊፈልጉ ይችላሉ:: ነገር ግን መንግስት ብርቱካንን ከእስር አስወጥቶ «አሳዝናኝ ፈታኋት» ቢል መርህን የተከተለ አይሆንም:: «እንዴት ይሆናል፣ የእድሜ ልክ ፍርደኛ ነች፣ ሕግ ጥሳ እኮ ነው የታሰረችው ...» ብሎ የሚጠይቅ ወገን ባይኖርም እንኳን ኢሕአዴግን «ራርተህ ፍታልን» ብንለው ህዝብ እንደዚያ ብሎ ይጠይቀኛል እንደሚል መገመት ያሻል:: ሁሉንም ነገር ወደጐን አድርገን ጉዳዩን በመርህ ደረጃ ስንመለከተውም ይህ አባባል ኢሕአዴግን ልክ

ሊያደርገው ይችል ይሆናል ብለን እናስብና። ለማለት የተፈለገው፣ የመንግስት መራራት ለብርቱካን መፈታት ፋይዳ እንደማይኖረው ማስገንዘብ ነው። ይህ ማለት ግን ብርቱካን ልትፈታ የምትችልበት መንገድ የለም ማለት አይደለም።

## «ድርድር»

(አቶ ልደቱ አያሌው የፖለቲካ እስረኞችን ጉዳይ በተመለከተ ወ/ት ብርቱካንን ጨምሮ ሌሎቹም የፖለቲካ እስረኞች መሆናቸውን ለማጣራት በፓርቲዎች ምክር ቤት ጥረት እንደሚደረግ በተገለጹበት የፓርቲያቸው ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ «በእኛ በኩል የፖለቲካ እስረኞች አሉ ብለን እናምናለን፤ ስለዚህም በዚህ ጉዳይ ላይ ከገዢው ፓርቲ ጋር ለመደራደር አጀንዳ ተይዟል» ብለው ነበር።)

በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል የሚደረግ የትኛውም ድርድር እውነታው ምንም ይሁን ምን፣ ዓላማው አንድ እንደሚሆን እናምናለን - ሰላማዊ መንፈስ። ሰሞኑን ወ/ት ብርቱካን የፖለቲካ እስረኛ መሆኗን አና አለመሆኗን እናጣራለን የሚሉት ወገኖች የፖለቲካ እስረኛ መሆኗን በማስረጃ ካረጋገጡ ከመንግስት ጋር የመፈታቷን ነገር እንደሚደራደሩ ገልፀዋል። የማረጋገጫ ዘዴውን እንተወውና፣ የማረጋገጥ ሂደቱ ሁለት ውጤቶችን ሊያስከትል እንደሚችል እርግጥ ነው። አንደኛው ብርቱካን የፖለቲካ እስረኛ ናት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የሕግ ታራሚ መሆኗን የሚያረጋግጥ ይሆናል።

እንበልና፣ የፖለቲካ እስረኛ ናት ተብሎ ቢረጋገጥ የመንግስትን የቀደሙ እርምጃዎች ፉርሽ ያደርገዋል። በቅርቡ የፓርቲዎች ድርድር ላይ ድርድራቸው «ሰጥቶ በመቀበል» መርህ ላይ የተመሠረተ ስለመሆኑ ነግረውናል። እውን ኢሕአዴግ «ብርቱካንን ዳግም ያሰርኩት በፖለቲካ አቋሟ ነበር» ብሎ እስከማለት ዝግጁ ሆኖ ይሆን? ይህም ከሕግ በላይ ሆኜ ነበር ማለቱ ነውና፣ እዚህ ድረስ የመሸነፍ (የማመን) ሞራል ያለው ተደራዳሪ ይሆን?

እንግዲህ የወ/ት ብርቱካን የፖለቲካ እስረኛነት ገና በማጣራት ሂደት የሚታወቅ ነው። በሂደቱ ግን፣ ማን ያውቃል የሕግ ታራሚ ሆናም ልትገኝ ትችላለች። ይህን ጊዜ ድርድሩ በምን ዙሪያ ይሆን የሚሆነው? ወይንስ የማስፈታት ድርድሩ ይቋረጣል? በጥያቄ ላይ ጥያቄ ይደረባል።

አስቀድመን የዚህ ጽሁፍ ዓላማ የብርቱካን መፈታት ላይ እንደሚያውጠነጥን አስታውቀናል። በመሆኑም ልትፈታ የምትችልበትን መፍትሔ ሳንጠቁም አናልፍም።

## ብቸኛ መፍትሔ

ወ/ት ብርቱካን ዳግም ለእስር የበቃችው «በተጭበረበረ ይቅርታ» በመውጣቷ እንደሆነ ከመንግስት ተገልጿል። በርግጥ የማጭበርበር ተግባሩን ማን እንደፈፀመ አልተነገረም፤ እኛም አንመለስበትም። ቁም ነገሩ ግን ብርቱካን የተፈታችው ባልተጠየቀ ይቅርታ መሆኑ ነው። ይህንን አጥብቀን በመያዝ እንቀጥል።

የቅንጅት አመራሮች በእስር ሳሉ የይቅርታ ሰነዱን ለመፈረም ካንገራገሩት አንዷ ብርቱካን እንደነበረች ተሰምቷል። ብርቱካን የልጅ እናትና የጧሪ ጠባቂ እናት ልጅ መሆኗም ይታወቃል።

ስፍር ቁጥር የሌለው ህዝብ የእርሷን መፈታት አጥብቆ እንደሚመኝም መገንዘቧ እርግጥ ነው:: የፖለቲካ አጋሮቿ በየአቅጣጫው የተበታተኑ ቢሆንም በሰላማዊ ትግል የቀጠሉም አሉ፤ 97 ምርጫን ላለመድገም ከኢሕአዴግ ጋር ስምምነት የፈርሙም እንደዚያው:: በተጨማሪም በአንድነት ፓርቲ ውስጥ ምክትሏና በቅርቡ ፓርቲውን መሰናበታቸው የተሰማው ዶ/ር ያዕቆብ፣ የወቅቱ ፖለቲከኞች የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሰጣቸው ውክልናና ኃላፊነት ብቁ ሆነው አለመገኘታቸውን በመግለፅ «የኢትዮጵያን ሕዝብ ተንበርክከን ይቅርታ ልንጠይቀው ይገባል» ማለታቸውን አንብበናል::

በርግጥ ከላይ የጠቀስናቸው ሁኔታዎች የብርቱካንን የዓላማ ግትርነት ሊሰብሩም፣ ላይሰብሩም ይችላሉ:: ሆኖም ብቻዋን ዋጋ ከፋይ የምትሆንበት ክስተት ተገቢ አለመሆኑን አያሌዎች ያምናሉ:: መንግስትን ይቅርታ መጠየቅ ህዝብ እግር ላይ እንደመውደቅ መሆኑን ብርቱካን ትረዳዋለች:: እናም ለብርቱካን ከእስር መፈታት ብቸኛ መፍትሔ አለ:: እሱም- ሕግን መሠረት ያደረገ ይቅርታ መጠየቅ ነው::

የይቅርታ ሥነ-ሥርዓት ሕጋችን እንኳን ላልተጠየቀ ይቅርታ ይቅርና ተጠይቆ ውድቅ የተደረገ ይቅርታ ቢኖርም ዳግም መጠየቅን አይከለክልም:: ለእርምጃዎቹ አንቀፅ የሚጠቅስ መንግስት ባለበት ሀገር አንቀፅ ያልተጠቀሰበት መፍትሔ የሚበጅ አይመስለንም:: ስለዚህም ጉዳዩን ከመንግስት አንፃር ማየት መፍትሔውን ቀላል ያደርገዋልና አዲስ ይቅርታ መጠየቅ ብርቱካንን ሊያስፈታት ይችላል:: በርግጥ ይቅርታ መጠየቅ የራሱ የሕግ ሂደትና ጥያቄው ውድቅ ሊደረግ የሚችልበት ሁኔታ ቢኖርም፣ ብርቱካን ባልጠየቀችው ይቅርታ ተፈታለች በተባለ ጊዜ ሁሉም መስፈርቶች መሟላታቸው ተረጋግጧል:: ተመልሳ በታሰረች ጊዜም የሕጋዊ መስፈርቶች ጥያቄ አልተነሳም፤ ይቅርታ ከመጠየቅና ካለመጠየቅ በቀር::

አሁን ካለው ነባራዊ ሁኔታ አንፃር ይህ ሁሉንም ወገን ሊያስደስት እንደሚችል የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ ያምናል:: ምክንያቱም ጠ/ሚኒስትር መለስ ራሳቸው «በመታሰሯ እኔም በግሌ አዝናለሁ» ማለታቸው አንዱ እማኝ ነው:: እናም የይቅርታ ጥያቄ የማቅረቡን ሂደት እርሷ የሕግ ባለሙያዋ ታጣዋለች በሚል ሳይሆን፣ የይቅርታ ጥያቄው ከእርሷ ባሻገር በቅርብ ዘመዶቿ፣ በወኪሏ ወይም በጠበቃዋ ሊቀርብ መቻሉን ሕግ እንደሚደነግግ ማስገንዘብ እንወዳለን:: ከዚህ አኳያ ከ97 በኋላ የፈለቁት የሀገር ሽማግሌዎች የበኩላቸውን ቢሉ የመፍትሔው አካል የመሆን እድል ይኖራቸዋል፤ መልካም ስምም ያተርፋሉ::

# ስንቱን ነገር እንራብ?

## (እህል ተርበን፣ ሀቅ መስማትን ተርበን፣ እውነት መናገርን ተርበን፣ ...)

**በወንድሙ ኢብሣ**

***1ኛ መልዕክት፡-*** የኢቴቪ ራዲዮና የአንዳንድ የአዲስ አበባ (የየዞን እና ወረዳ) ነዋሪዎች ለገዢዎች ታማኝነት እና ምስክርነት ህዝባዊ፣ ህጋዊ፣ ህሊናዊ እና አገራዊ አንድምታ አለውን? ኢትዮጵያ አፍሪካ ናት፤ በብዙ ነገርዋም ተምሳሌትም ናት ::አፍሪካውያን እና ኢትዮጵያውያን የራሳችን ባህላዊ እሴት እና ዘመናዊ አስተሳሰብን እየተቀዳጀን ነው፤ ይህም ጥሩ ይሉኝታ ነው::

ጥሩ ይሉኝታ ማለት ህዝብ ምን ይለናል? አገር ምን ይለናል? ህሊናዬስ ምን ይለኛል? ቀጣይ ትውልድስ እንዴት ይመዝነኛል? ታሪክስ ምን ፍርድ ይሰጠኛል? ብሎ በጥልቀት በማሰብ የማያስፈልግ ምስክርነት ከመስጠት (የማያስፈልግ ዘፈን ከመዝፈን፣ ያልተገባ ፍራቻን በማስወገድ) ወቅታዊ እና ተጨባጭ አገራዊ እውነታን በእውቀት በእውነት በእምነት መመስከር መቻል ነው:: ያለበለዚያ እንደ አበው አባባል የማይሆን ተናግሮ ከመታዘብ «ዝምታ ወርቅ ነው» የሚለውን መጠቀም ይመረጣል:: እስቲ ወደፊት ራቅ አድርጌ ላስብ እና ዛሬ የምንሰጠው አስተያየት፣ አመራር እና ክንውን ከዛሬ 30 እና 50 ዓመታት በኋላ ልጆቻችን፣ የልጅ ልጆቻችን ምን ይለናል ማለት ይገባናል ለዚያውም ከ1889 ዓ.ም በንጉስ ምኒሊክ ረሃብ ጀምረን በኃ/ስላሴም ቀጥለን በደርግም የባሰ ጨምረን በ1977 ዓ.ም አንድ ሚሊዮን በረሃብ ያለቁ ወገኖቻችንን ታሪክ ይዘን በኢህአዴግ ዘመንም በሚሊዮኖች ባይሞቱም በሚሊዮኖች ተርበን በሚሊዮኖች ቁጥር ላይ ተከራክረን ከትናንት እስከዛሬ ሚሊዮን ርሃብተኞችን እና ይህንን ታሪክ ተሸክመን እየገሰገስን ነው:: 'ከስድስት ሚሊዮን' ርሀብተኛ ወገኖቻችን መካከል የአርሲ፣ ዝዋይ ዱግዳ፣ ወረዳ የ2001፣2002 ሰብል በዝናብ እጦት ሙሉ በሙሉ ስለጠፋ እንደ ማስረጃ የሚጠቅስ እስከዛሬም በቂ እርዳታ እንዳልሰጠ ታሪክ ይዘን ምንም የሌለን ወይም ካለን ጥሩ ገጽታ ርሀብ ክፉ ገጽታችን አይሎ በዓለም መዝገበ ቃላት ተመዝግቦ የጀግኖች አትሌቶቻችንን እና የአትንኩኝ ባይነት አገራዊ የነፃነት ቀናነታችን እየተፈታተነን ባለንበት ጊዜ፤ ለዚያውም የውጭ አገር መንግስታት በጭምጭምታም ሆነ በግልጽ የርሀብተኞች ቁጥር ከ10 ሚሊዮን በላይ ነው እመኑን እና እንርዳችሁ የሚል የተለያየ ዳታ እያቀረቡ እኛም እርዳታን ተቀብለን ወገኖቻችንን እንደመርዳት በሌለን መልካም ገጽታ እንወዛገባለን:: የሚነሱትን የኃሳብ ልዩነቶች ግራ ቀኙን ደጋፊ እና ተቃዋሚን በንጽጽርና ሚዛናዊነት ከማቅረብ ይልቅ ኢቲቪ እና አንዳንድ የአዲስ አበባ የዞን እና የወረዳ ነዋሪዎች አስተያየት ስጡ እያልን ጭፍን የአንድ ወገን ምስክርነት በመታዘብ ነው ይህንን መልዕክት መጻፍ የፈለግኩት::

በንጉሱ ዘመን (በ1960ዎቹ) ሬዲዮ እና ቴሌቪዥን ብርቅ ቢሆንም ጥሩ የመስማት እና የማየት እድል ከነበራቸው አንዱ በመሆኔ በዛን ዘመን የመነቃነቅ የሳንሱር መቀስ (ሃሳብን መቆጣጠር፣ ህሊናን ማስቆጣት፣ መጨቆን) ጨካኝ አመራር ቢኖርም ከንጉሱ ዘመን ጋዜጠኞች ተምሳሌታዊ የሆነው የአርሲ ሁሩታው ጋዜጠኛ አሳምነው ገብረወልድ የሀሳብ ቁጥጥሩን ተጋፍጦ በቋንቋ ጥበብ መቀሷዋን ሸልቅቆ የህዝብ ወገናዊነቱን አረጋግጦ የአመራሩን ብልሹነት በጀግንነት

ይገልጽ እንደነበረ ትዝ ይለኛል:: እና ወይ ነዶ ወይ የዛን ጊዜ ጋዜጠኞች ለህዝብ፣ ለህግ፣ ለአገር እና ለህሊና የነበራቸው ተቆርቋሪነት ፊት ለፊት ስርዓቱን ሲጋፈጡ ክብር ይገባቸዋል እላለሁ:: የዛሬዎቹ ጋዜጠኞች ግን ህዝብን፣ ህግን እና ህገ መንግስትን አገርን እና ህሊናን ችላ ብለው የገዢዎችን ፍላጐት ብቻ ተሸክመው ኖረው የኢትዮጵያን ምድር በየብስ በባህር ወይም በአየር መሻገራቸውን ሲያረጋግጡ ኢቲቪ እና ሬዲዮ ሙያዉ ነጻነት ሰፊ ችግር እንዳለባቸው ሲመሰክሩ እታዘባቸዋለሁ:: መጋፈጥ ተሸሽጐ ብቻ አይደለም :: ስለዚህ ጋዜጠኞቻችን ሙያችሁን፣ ህዝባችሁን፣ አገራችሁን፣ ታሪክን መፍራት መጀመር አለባችሁ:: ገዢዎቹ ይቀራሉ ታሪክ ግን ቀጥሎ ይመሰክርብናልና::

ከንጉሱ ዘመን በኋላ ደርግ ሆድ አደር ምሁራኖችን አሰባስቦ ቀልባቸውን ግን ገፎ ሁሉ በእጄ በደጄ በሚል ነገን በማያስተውል ታሪክን ዋጋ በነሳ ጭካኔ በቀይ እና በነጭ ሽብር የወንዝ ልጆችን ጉራ ለያይቶ አጫርሷል:: ያልተሰራ ታሪክን ተሰራ ሲል፣ ያልለማን ለማ ሲል ገድሎ ሬሳን በገንዘብ ግዙ ሲል ቃላት ሊገልጽ የማይችለውን አረመኔያዊ ጭካኔ ሲፈጽም ይህ ጉደኛ ኢቲቪ እና ሬዲዮ እንደዛሬው ሁሉ የአንድ ወገን ምስክርነትን ሚዛናዊነት የጐደለው አቀራረብ ይከተል ነበር:: አንዳንድ የአዲስ አበባ (ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ቀበሌ) ነዋሪዎችን በአስረጂ ምስክርነት ሲያቀርብ እንደነበረ ዛሬም መቀጠሉን የኢቲቪ እና ሬዲዮ ጋዜጠኞች ሌላው ቢቀር የኢቲቪ እና ሬዲዮ ዶክመንተሪ ፊልም መጋዘናቸውን እና በታሪክ የተፃፉትን እያስታወሱ ለምን ሚዛናዊ አስተያየት (ደጋፊ እና ነቃፊ) አያቀርቡም? ስል የሚሊዮኖችን ጥያቄ አቀርባለሁ::እነዚህ ሜዲያዎች በእጃቸው ያለውን የደርግ ዘመን «አንዳንድ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች» ምስክርነት መለስ ብለው ቢመለከቱት የሚሰጣቸው ምስል ይኖራል:: ለደርግ የነበረው የፍርሃት ድጋፍ አይነት በዛሬዋ ኢትዮጵያ ሊደገም አይገባም:: ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ ሰፊ ተጽእኖ እና ጭቆና አለ ብንልም ህገ መንግስቱን እና ህጋዊነቱን ምድር ላይ ለመስራት ከሁላችንም (ከጋዜጠኛ (የግል - የመንግስት) የገዢ እና የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንደ ዜጋ) ህገ መንግስትን እና በህገ መንግስቱ ትክክለኛ መንፈስ የወጡትን ዝርዝር ቀጥተኛ ጠቃሚ ሕጎች (ሕገ መንግስትን ተጻራሪ ህጎችም ወጥተው ስላሉ) ስራ ላይ እንዲውሉ ትንሽ ትንሽ፤ በጉልበት ሳይሆን በእውቀትና በእውነት ለህዝባችን መስራት ይጠበቅብናል:: ይህን ለማድረግ ደግሞ ከፓርቲ ዊልቸር ጉዞ ተላቀን በህሊናችን አስበን መራመድ መጀመር ዘመኑም 'ትንሽ ትንሽ' ይፈቅዳል:: የጠፋው የእውቀት፣ የእውነትና የእምነት መግለጫ ብቃት አቅማችን ነው::

በእውቀትና በእምነት የተገነባ መረጃ ስናስተላልፍ እንደኔ አስቡ፣ እንደኔ ተናገሩ፣ እንደኔ ተግብሩ የሚሉንን ገዥዎቻችንን በህግ እና በስነ አመክንዮአዊ አስተሳሰብ ሰላማዊ ትግል ልንገጥማቸውና ልንፈትናቸው እንችላለን:: ይህን ካደረግን ተጎታች የገደል ማሚቶ ፓርቲዎችን እና አንዳንድ ደጋፊዎቻቸውን የዴሞክራሲ ባቡር ሀዲዱን ከመስመር እንዳያወጡ ማድረግ በእርግጠኝነት ይቻላል:: ለዚህ ኢቲቪ እና ሬዲዮ እንደገዢዎች ሳይሆን እንደ ህዝብ እንዲያስቡ ይህቺ መልዕክቴ ትማፀናለች:: ገዢዎቻችን የሚሉንን እያልን ሰላማዊ ተቃዋሚዎች የሚሉትንም አለማስቀረት አይዟችሁ ህጉ ይፈቅዳል፣ ይህን ለማስፈጸምም ከፖለቲካ የዊልቸር ቋንቋ ውጪ ብቃት ያለው እውቀት እና የእውቀት ቋንቋ ያስፈልጋል:: ይህ ቋንቋ ሙያዊ ብቃት ነው::ካለፈው ክፉ ስርዓት

ክፉ ነገርን ሁሉ መለወጥ ሲገባን ስርዓቱ ቢለወጥም ኢቲቪ እና ሬዲዮ ያንኑ መሰል የወገንተኝነት ድርጊት እየፈጸሙ መቀጠላቸው ጥያቄ ያጭራል::

ንጉሱ ከ1953 ዓ.ም ጀምሮ በተገቢው ሰዓት የስልጣናቸው መልቀቂያ እንደደረሰ ደም ተቀብቶ ቢነገራቸውም ለመስማት ፈቃደኛ አልነበሩም::ከነሹማምንቶቻቸው በሰፈሩት ቁና እስኪሰፈሩ በርስት መሬትና የከተማ ቤት ግንባታ ላይ ነበዛሬም ተመሳሳይ ነገር እየተመለከትን ነው::ሆድ ከብዶ ራስ እየቀለለ ነውና:: በ21ኛው ክፍለ ዘመን ውስጥ ሆነን በረቀቀ ቴክኖሎጂ ተከበን ነገሮችን መደባበቅ ዛሬ ያወጣነውን ህግ ነገ በተግባር ማምከን ሸፍጥ እንጂ የማይደበቅ መሆኑን ሁላችንም ወገኖች ተረድተን እጅ ለእጅ ተያይዘን የጌታ እና የሎሌን ግንኙነት ሳይሆን የወንድማማችነት ግንኙነትን ከበቀል እና ከቂም በጸዳ መልኩ በአቻነት መደራደር ይጠይቃል:: ስለዚህ ኢቲቪ እና አንዳንድ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ስለ እግዚአብሔር ብላችሁ ከጥቅምና ከፖለቲካዊ ወገንተኝነት ባሻገር የቀጣዩን ትውልድ እሳቤ ምስክርነታችን 20 እና 30 አመታት በኂላ ይመሰክርብናል «ቆንጆ የኢትዮያ ልጆች እየተወለዱ ናቸው!» ኢ-ቆንጆ ገጽታችንን ቀንሰንና አጥፍተን መልካም ገጽታችንን ልናቆይላቸው ይገባል:: አገሮች ሁሉ፣ ፓርቲዎች ሁሉ፣ ሰዎች ሁሉ ሲሳሳቱ እየተማማሩ የጋራ አጀንዳ በጋራ፣ ለጋራ፣ የጋራ አድርገውታል፤ እያደረጉትም ይገኛሉ::

አገራችንና ወገኖቻችን ዛሬም እንደትላንቱ አንዱን ቡድን ለመድፈቅ አንዱን ቡድን ለማግዘፍ (የደርግን፣ የመኢሶንን፣ ኢህአፓን፣ ወዝሊግን፣ ኢማሌድህና የዚህ መንግስት ታሪክን ህወሓት ኢህአዴግን ህብረትን እና ቅንጅትን ዘንድሮም የመድረክ (ስምንቱ ፓርቲዎች) እና የአራቱ ፓርቲዎች ቅንብር ከኢቲቪ እና ሬድዮ እንዲሁም ከአንዳንድ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች የቆየ እና ዛሬም የቀጠለ የሚያሳምን ምስክርነት መብት መሆኑን ብናውቅም ውሸት በራሱ መብት መሆኑን እና ያለመሆኑን የህግ ባለሙያዎች የሚሉትን ጠብቁ በእኔ እምነት ግን ያስቀጣል ቢያንስ 'ዋጋ' ያሳጣል እላለሁ ሊታረምም ይገባል::

ስለዚህ ከትናንት ታሪካችን አለመማራችን ብቻ ሳይሆን ዛሬም ያለፉት ሹማምንቶች ልጆች በወላጆቻቸው ታሪክ እንደሚሸማቀቁ ለምሳሌ የፕሬዚዳንት መንግስቱ ኃ/ማርያም ልጆች በውጭ አገር የህክምና ዶክተሮች ሲሆኑ ስለ አባታቸው ታሪክ እና ስለኢትዮጵያ የሚያወራ ሰው ሲያጋጥማቸው እንደጠላት በማየት በፍርሃት ተውጠው ለመሸሽ ሲጣደፉ ከሰነዶች አንብቢያለሁ:: በውጭ አገር ኢትዮጵያውያኖችን ሲያዩ ተደናብረው ይሸማቀቃሉ ቢያንስ እንደመሪ ልጆች ክብርና ኩራት አይሰማቸውም:: የኢትዮጵያ ገዢዎች ከዚህ የባሰ ምን ትምህርት ይሆናቸዋል? ምንም:: የመንግስቱ ልጆች ምን በወጣቸው ይሸማቀቃሉ? የልጅ እና አባት ግንኙነት የደም እንጂ የወንጀል አልነበረም:: የአንድ ወገንና የአንዳንድ ነዋሪዎች ዘገባ ጉዳይ በዚህ እሳቤ ይቃኝ::

ከዚህ በተረፈ የኢቲቪ እና የራዲዮ ጋዜጠኞቻችን ይቅር ባይነትን ለማስፈን፣ ብሔራዊ እርቅን ለመጀመርና ብሔራዊ መቻቻልን በብሔራዊ አጀንዳ ለመገንባት፣ መቻቻልን ሰጥቶ መቀባበልን በእውቀት፣ በእውነትና በእምነት እንዲሰብኩ መልእክቴ ይድረሳቸው እላለሁ::

መላው አካላችን አይናችን፣ ጆሯችን፣ እጃችን፣ ምላሳችን፣ አምስቱ የስሜት አንቀሳቃሽ ህዋሶቻችን በአንጎል እንደሚመራ ሁሉ (ጥሩም ሆነ መጥፎ አእምሮ) አገሮችም ኢትዮጵያም

በገፎዎች፣ በመሪዎችና በአስተዳዳሪዎች ትመራለች (ጥሩም ሆነ መጥፎ አእምሮ)፡፡ የእነዚህ ወገኖች ድርሻ የዝሆን እና የአንበሳ ድርሻ ሊሆን ይገባል የምንለው አእምሯችን ለአካላችን ቅንጅታዊ ስራ ከሚያስፈልገው ትልቅ አስተዋጽኦ አንጻር ነው፡፡ በመሆኑም የአንበሳ ድርሻ ያላችሁ ወገኖች ድሉና እድሉም በእጃችሁ የሆነና የተሳካላችሁ ወገኖቼ ታሪክን እንድትሰሩ መልእክቴን እነሆ፡፡ አንዳንድ የአዲስ አበባ ነዋሪዎችን ሚዛናዊ አስተያየት በመስጠት ታሪክ ስሩ፤ ታሪክ እንስራ ሚዛናዊነት የህዝብ ስሜት እና አስተያየት፣ የህዝብ ፍላጎት እና አላማ የጠራም ያልጠራም እውነትም ሃሰትም ከአንድ ወገን ብቻ ከማስተጋባት በንጽጽር ደጋፊ እና ተቃዋሚን ከነ ምክንያቱ ለህዝብ ማቅረብ ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡

የዛሬ መልእክቴን በአንድ ባህላዊ አነጋገር ልቋጭ፡፡ «መቻቻል ያስማማል፣ ጥጋብ ያስገሳል፤ አለመቻቻል ያነታርካል፣ ረሀብም ያዛጋል፤» ወገኖቼ ስንቱን ነገር እንራብ? እህል ተርበን፣ ዓለምን ለምነን (ስንት ዘመን)፣ ሀቅን ተርበን፣ እውነት መናገርን ተርበን፣ ለአለቆቻችን ህግን መሰረት አርገን በእውቀት መናገርን ተርበን፣ አቅም እና አቅል አጥተን ዛሬም ስድስት ሚሊዮን ርሀብተኞችን ተሸክመን መልካም ገጽታችን ወዴት ነው? ህዝቡ የሚለው ሌላ ኢቴቪ እና ራዲዮ እንዲሁም አንዳንድ የአዲስ አበባ ምስክሮች የሚሉት ሌላ መሆኑ ያብቃ፡፡ ለሁላችንም ሀብት ከቸርነት (ከንፉግነት እና እኔነት ይልቅ) እድሜ ከጤንነት ለመልካም ስራዎቻችንና አላማዎቻችን መምከንን ሳይሆን ስኬትን በእግዚአብሔር ስም እመኛለሁ፡፡

***/አቶ ወንድሙ ኢብሳ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት አባልና የኦህኮ ስራ አስፈጻሚ ናቸው/***

# ህልም ተፈርቶ ሳይተኛ ይታደራልን?

**በታምራት ታረቀኝ**

መድሀኒት ያልተገኘለትን ቀሳፊ በሽታ የስርጭት ፍጥነቱን ለመግታትና አድማሱን ለማጥበብ ዋንኛው መፍትሄ በህብረተሰቡ ዘንድ ግንዛቤ መፍጠር በመሆኑ ለዚሁ ተግባር ተብሎ የተዜመው «ማለባበስ ይቅር» የሚለው ዜማ አንድ ሰሞን የራዲዮኑንም የተሌቭዥኑንም የአየር ሰዓት አጣቦት ነበር፡፡ ያስገኘው የአስተሳሰብ ለውጥም ቀላል አይደለም፡፡ እናማ ፖለቲካውም የማይድን በሽታ ተጠናውቶታልና ማለባበስ ይቅር የሚል ዘመቻ ልንከፍትበት ተገቢ ይሆናል፡፡ የሩቁን ትተን የአሁኑ እንኳዋን ለመንግስትነት ከበቃ 17 ዓመት ቢያስቆጥርም የሚነገረውን ሰምቶ ወይንም ከራሱ ተሞክሮ ተምሮ ለውጥ ሊያመጣ አልቻለም፡፡

እኛ ተቀዋሚዎችም የምናወግዘውን ድርጊት ራሳችን ስንፈጽመው፤ እንደ አቅማችን በአባሎቻችን ላይ አምባገነን ስንሆን እንጂ ዲሞክራሲን ስንለማመደው ታይተን አናውቅም፡፡ ምርጫ ሲደርስ ህብረት ፈጠርን ተቀናጀን እንበል እንጂ ሥልጣን ከማለም ያለፈ ዲሞክራሲያዊ ሥርአትን እውን በማድረግ የህዝቡን የሥልጣን ባለቤትነት ለሚያረጋግጥ የጋራ ትግል የተዘጋጀንበት ጊዜ የለም፡፡

ስለሆነም ለመድህኒት የለሹ በሽታ «ማለባበስ ይቅር» ብለን እንደዘመትነው ሁሉ በፖለቲካውም «ዝም አይነቅዝም » ከሚለው አደንዛዥ አስተሳሰብ ተላቀን «ዝምታ ወርቅ ነው» የሚለው አስተሳሰብ ጊዜ ያለፈበትና በዛሬ ዘመን እንደማይሰራ ተገንዝበን ማለባበስ ይቅር ብለን እንነሳ። ከዚህ አንጻር ምረጡን ስለሚሉን ድርጅቶች በጥቅሉ ፡ዕጩ ሆነው ስለሚቀርቡት ተወዳዳሪዎች ደግሞ በተናጠል በዝርዝር እንጠይቅ። የምናውቀውን እንናገር። እንጻፍ። ለምርጫ የሚቀርብ ማንም አካል ጉድለቱን አምኖ ስህተቱን ተናዞ ለመመረጥ ብቁነቱ ተበጥሮ እና ታውቆ መሆን አለበት። የገዢው ፖርቲ ስላቀረበው ብቻ የኢህአዴግ አባላት የስነ ምግባር ጉድለት ያለበትንና ከራሱ በቀር ስለሀገር ደንታ የሌለውን ሰው ሊመርጡ አይገባም። በተቀዋሚ በኩል የቀረበውንም ቢሆን ኢህአዴግን ባለመፈለግ ብቻ መምረጥ የባለፈው ይበቃናል። በንግግራቸው የሚያሳፍሩ በአድራጎታቸው የመረጣቸውን ህዝብ ለአፍታም የማያስታውሱ ሰዎችን ፓርላማ ውስጥ ለአንድ የፓርላማ ዘመን አይተናል። ከመጀመሪያው ባይኖራቸው እንኳዋን በአራት ዓመት የፓርላማ ቆይታቸው ብዙ መሻሻል ማድረግ በቻሉ ነበር። የምናየው ግን የራሳቸውን ህይወት ሲያደላድሉ እንጂ የመረጣቸውን ህዝብ ሲያስቡ አይደለም። በአራት ዓመት ውስጥ በጣት ለሚቆጠሩ ጊዜያት ብቻ ፓርላማ ስብሰባ መገኘት የተመራጭ የተግባር ባልሆነ ነበር። የህዝብ ውክልናቸው ቢቀር ስለሚበሉት ደመወዝ ሲሉ በፓርላማው ስብሰባ መገኘት ነበረባቸው። ስለሆነም ከለፈው ተምረን ለወደፊቱ የተሻለ ነገር የምንመኝ ከሆነ ማለባበስ ይቅር ብለን እንነሳ።

ማለባበስ ይቅር በፖለቲከውም
በእጅጉ ጎድቶናል የይሉኝታ ልጓም
አለብብሰን አርስን አረም ስናመርት
ሁሉን እየቻልን ስንገፋ ህይወት
ያተረፍነው ቢኖር ኋላ ቀር ድህነት
ከእንግዲህ ይብቃ ማለባበስ ይቅር
ሁሉን አፍረጥርጠን ግልጽ እንነጋገር።

ለዚህ የጋዜጣው ዝግጅት ክፍል ፈቃደኛ ሆኖ አንድ አምድ ቢከፍት እላለሁ። ይህን ስል ግን ከስጋት ነጻ ሆኜ አይደለም። ይህችን ጽሁፍ እያዘጋጀሁ ባለበት ሰአት አውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ኢ/ር ኃይሉን አስመልክቶ የጻፈውን በመቃወም አዲስ ዘመን ጋዜጣ በአጀንዳ አምዱ ያሰፈረውን ጽሁፍ ለመቃኘት ችዬ ነበር። የመንግስትን ፍላጎት ለማወቅና ድርጊቱን ለመረዳት የሚያስችለው የዘመኑ አጀንዳ አምድ ያሰፈረው ረዥም ጽሁፍ ኢህአዴግ ለወዶ ገቦቹ ጥብቅና የቆመ መሆኑን የሚያሳይ ነው። እንደ ማስፈራራትም ይቃጣዋል። «እንኳዋን እናንተን አይነኬ ይመስሉ የነበሩትንም አስገብሬአለሁ» የሚል ይመስላል። ህልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም ነውና ማስፈራሪያው በተግባር ደርሶ እስከምናየው በብዕራችን ላይ ማዕቀብ አንጥልም። እናም በስማችን ለተሰየመው ምክርቤት (ፓርላማ) ለመብቃት የእኛኑ ድምጽ የሚፈልጉትን ፓርቲዎችም ሆነ ተወዳዳሪዎቻቸውን የመተቸት የማጋለጥ የባሰም ሲያጋጥም ገመናቸውን አጋልጠን ከውድድር ውጪ የማድረግ የዜግነት መብት አለን ብለን

እናስባለንና የምንችለውን እናደርጋለን፡፡ ሌሎችንም እናበረታታለን፡፡ አራቱ ፓርቲዎች ያሉባቸውን ጉድለቶች እያሰቡ መተቸትን የሚከለክል ህግ እንደማያወጡ እገምታ ለሁ፡፡

የዛሬ ጅምሬን ጠንካራ ተፎካካሪ እንደሚሆን እየገለጸ ባለውና በተለያየ መንገድ የመገናኛ ብዙሀንን ትኩረት እየሳበ ባለው መድረክ ዙሪያ ላድርግ፡፡ በቅድሚያ ግን ትችትን ማዳከሚያ፤ ጥያቄ ማንሳትን ባላንጣነት አድርጎ ከመመልከት የማሌ አስተሳሰብ ያልተላቀቁ ወገኖቼ መነሻ መድረሻዬም ፓርላማ ውስጥ በትክክል የሚወክሉኝን አውጥቶ አደር ያልሆኑ ሰዎችን ማየት መሆኑን እንዲረዱልኝ እጠይቃለሁ፡፡ ትችት የሚያጠናክር ጥያቄም ያላዩትን ለማየት የሚረዳ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በነገራችን ላይ የአንድነቱ ምክትል ሊቀመንበር ዶ/ር ያዕቆብ ኃ/ማርያም ከፓርቲው መልቀቃቸውን ለነገሩት ጋዜጣ ሁላችንም የፓርቲ አመራሮች በማርክ ሲዝም ሌኒንዝም ርዕዮተ ዓለም ጥርሳችንን ነቅለን ያደግን በመሆናችን የሀሳብ ልዩነትን በውይ ይት የመፍታት ችግር አለብን በማለት የተናገሩት የገባቸው ወይንም ያወቁት ዘግይቶ ቢሆንም ሁሉንም የሚመለከት ነውና ምረጡን የሚሉ ፓርቲዎችና ተወዳዳሪዎቻቸው ኢህአዴግን ጨምሮ ከዚህ መጽዳት አለያም አምነውበት የሚያራምዱት ርዕዮት መሆኑን ሊነግሩን ይገባል፡፡ የምንመርጠው አውቀንና አምነን እንጂ ፈርተንና ጠልተን መሆን የለበትምና፡፡ ግን እኮ ውይይት አንዱ የዴሞክራሲያዊነት መገለጫ ነው፡፡

መድረክ የስምንት ፓርቲዎች ቅንጅት መሆኑን በየዕለቱ እንሰማለን፡፡ በሀገራችን ፓርቲ ለመ ባል የምርጫ ቦርድን የምስክር ወረቀት መያዝ ብቻውን በቂ መሆኑን ብናውቅም እኛ ግን ፓርቲ ብለን ለመቀበል በየግላችን የምንመዝንባቸው መስፈርቶች ይኖሩናል፡፡ እንደውም ዶ/ር በየነ ጴጥ ሮስ ኢምፔሪያል ሆቴል በመድረክ በተዘጋጀ ሲምፖዚየም ላይ ባቀረቡት የጥናት ወረቀት የአን ድና ሁለት ሰው ፓርቲዎች ፓርቲ እየተባሉ የህብረት አባል እንዲሆኑ መደረጉ ላለፉት ህብረ ቶች መዳከም ዋና ምክንያት እንደነበረ ገልጸዋል፡፡ የራሴን ፓርቲ ፓርቲ ብዬ ለመቀበል የሚያ ስችሉኝን መስፈርቶች ልተውና በፕ/ር በየነ ሀሳብ መነሻነት ጥያቄ ላንሳ፡፡

- የመድረኩ አባል የሆኑትና ስምንት ለመባል ያበቁት ኦህኮና ሶዴፓ ሁል ጊዜ ከምናያቸ ውና ከምንሰማቸው ሊቀመንበሮቻቸው ቀጥሎ ምክትል፣ ጸሐፊ፣ የድርጅት ጉዳይ ወዘተ የሚባል ኃላፊነት የያዙ ሰዎች አሉዋቸው? አሉ ከተባለም እንወቃቸው፡፡ ኦፌዴንን ያልጨመርኩት ምርጫ 97 የወለደው ፓርቲ ስለሆነና ሁለት አመታትን ያስቆጠሩ በመሆናቸው ነው፡፡
- ኢዴአን ማነው? አመራሮቹ እነማን ናቸው? ጽ/ቤቱ የት ይገኛል? መሰረቱ የት ነው? በየትኛው የሀገሪቱ አካባቢ በመንቀሳቀስ ነው የሚታወቀው?ወዘተ
- ሶዴኃቅ ስሙ የሚያስረዳው የተለያዩ ፓርቲዎች ቅንጅት መሆኑን ነው፡፡ ቅንጅቱን የፈጠ ሩት ፓርቲዎች እነማን ናቸው? የፓርቲው መሪዎችስ? ድርጅታዊ አቅማቸውስ እንዴት ይገለጻል?

- ደቡብ ህብረት ባለፈው 15 ኣመታት የምናውቀው ነው ወይንስ ሌላ? በደቡብ ህብረትና በሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲ መከከል ያለው ልዩነትስ ምንድን ነው? የሁለቱም አባላት አንድ አይነት ሰዎች እንደሆኑ ይገለጻልና በስም ሁለት በድርጅታዊ ቅርጽ አንድ የሆኑት ፓርቲዎች በሁለት ፓርቲነት የመድረኩ አባል የሆኑበት ምክንያት መስፈርት ምንይሆን? መቼም የቁጥር ብዛት ተሰሚነትን ይፈጥራል ተብሎ እንደማይፈጸም እገምታለሁ::

በእኔ ሚዛን አረናና አንድነት የአደረጃጀት መደበላለቅና የአንድ ሰው አመራር ጥያቄ የሚነሳባ ቸው አይደሉም:: ሌላው የሚነሳ ጥያቄ መድረክ የተመሰረተው በሰጥቶ መቀበል መርህ ነው የሚለውን ተከትሎ በተለይ በአንድነት አመራሮች ተደጋግሞ የሚነገረውን ይመለከታል:: ሰዎቹ አንቀጽ 39 ን :የኢትዮጵያ ሉአለዊነትንና የአሰብ ወደብን በተመለከተ መድረኩ የደረሰበት አቋም የአንድነት አመራር ውጤት እንደሆነ በመግለጽ አንድነት መሰረታዊ አላማዎቹ ተሸርሽረዋል የሚሏቸውን ሲሞግቱ ይሰማል:: እዚህ ላይ ተለባብሶ ሊታለፍ የማይገባው ግልጽ መደረግ ያለበት ጉዳይ አለ:: ይኸውም:-

- ከመድረኩ አባል ድርጅቶች መካከል የመገንጠልን አቋም የሚያራምዱ ነበሩ? ከነበሩ እነማን ናቸው?
- በኢትዮጵያ ሉአላዊነት ላይ ጥያቄ የነበራቸው ፓርቲዎችስ የትኞቹ ናቸው? አሁንስ አቋማቸውን ከመሰረቱ ሰርዘዋል ወይንስ የአንድነት ሰዎች ያልተግባባንባቸውን በልዩነት አስመዝግበናል እንዳሉት እነርሱም በልዩነት በይደር የያዙት ነው?
- አሰብ የኢትዮጵያ የተፈጥሮ የባህር በር እንደነበረና ያጣነው በሻዕቢያና ኢህአዴግ ውል አልባ ፍቅር ምክንያት መሆኑን የማይቀበል የመድረኩ አባል ድርጅት አለ? (በነገራችን ላይ የፈሰሰ ውኃ አይታፈስ ሆኖ እንጂ የአሰብ ጉዳይ ገዢዎቻችንንም ሳያንገበግባቸው የቀረ አይመስለኝም:: በአንድ ወቅት ብጻይ ኢሣያስ ኢትዮጵያውያን ሲራቡ የሚጨክን አንጀት የለንም:: የእርዳታ እህል በአሰብ በኩል እንዲገባ እንፈቅዳለን በማለት የተናገሩት ምጸት ለወደብ ኪራይ ከሚወጣው ገንዘብ ይበልጥ የሚያንገበግብ ነው:: የጫርኩት እሳት ፈጀኝ እንደሚባለው ሳይሆን ይቀራል!!

- ሶስቱ የመድረክ ሊቀመናብርት በተለያየ ጊዜና በተለያዩ ጋዜጦች መድረክ በአባል ፓርቲ ዎቹ ጥንቅር ብሄር ብሄረሰቦችንና ህዘቦችን ከኢህአዴግም በተሻለ እንደሚወክል ተናግረ ዋል:: የኦሮሞ የትግራይ የደቡብ የሶማሊ ውክልና ግልጽ ነው:: የሌሎቹን ውክልን ብታስረዱን? በተለይ አንድነት አማራውን ይወክላል መባሉን አስመልክቶ ለዜጎች ግልጽ ምላሽ መስጠት ተገቢ ነው:: ዝምታ ግን አዎን ነው የሚወክለው::

ሰሞኑን ደግሞ ዋናው ሊቀመንበር የተናገሩትን ተቀዳሚው እኛ አናውቀውም የራሱ ጉዳይ ነው ማለታቸውን ሰምተናልና ይህ ለመድረክ አመራሮች በጎ ጅምር አይደለም:: ፖለቲከኞቻችን የራሱ/የራሷጉዳይ ማለትን እንደ አንድ የፖለቲክ ስራ ያዙት እንዴ!

ነገር ቢበዛ በአህያ አይጫንም ያላሉ አበው:: ብዛቱ ሳይሆን ቁም ነገሩ ላይ ነውና ፋይዳው:: ስለሆነም ለዛሬ እንደመነሻ ከበቂም በላይ ነው:: ማለባበስ ይቅር ብለን የለ ወደ ፊት እንቀጥላለን

ዝግጅት ክፍሉ ከፈቀደ:: አንባቢያንም ከተባበራችሁ::አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ የሚለው ተረት በእኛ ላይ በደንብ አልተገለጸም ትላላችሁ:: ማለባበስ ይቅር- በፖለቲከውም::

*/አቶ ታምራት ታረቀኝ የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ስራ አስፈጻሚ አባልና የወጣቶች ጉዳይ ኃላፊ ነበሩ/*

# የኢትዮጵያ አስከፊ የርሀብ አደጋና የመንግስት አቋም

**በጆፍሬይ ዮርክ**

*በመላው ኢትዮጵያ አስከፊ የምግብ እጥረት ቢባባስም፣ የአገሪቱ መንግስት ይህን የሚመለከት መረጃ ይፋ እንዳይወጣ ጥብቅ ቁጥጥር በማድረግ ላይ ይገኛል:: አለመረጋጋትትን ቢሚያስከትሉ እንቅስቃሴዎች ተሳትፈዋል በሚል ውንጀላ የተወሰኑ የእርዳታ ድርጅቶችን ከአገሪቱ አባሯቸዋል:: በኢትዮጵያ በምትገኘው በድርቅ በተመታችው ገጠሬማዋ መቂ ከተማ አቅራቢያ የሚኖረው ገበሬ ገዳ ሸኑ፣ ልጆቹን ለመመገብ ደፋ ቀና ማለቱን ቀጥሏል:: የመንግስት ድጋፍ እንዲደረግለትም አቤቱታውን አቅርቧል:: የኢትዮጵያ መንግስት ያ አስከፊ የምግብ እጥረት በሚዲያ እንዳይወጣ የገደብ እርምጃዎችን ወስዷል:: የዓለም አቀፍ የእርዳታ ቡድኖችንም ሥራ አደናቅፏል::*

በአቧራማዋ መቂ ከተማ፣ ዛሬ ቀኑ የገበያ ነው:: በነጋዴዎች የተሸጡ ጥቂት በቆሎዎች የቀጨጩ፣ የደበዘዙ፣ የጠወለጉና በጠቃጠቆ የተሸፈኑ ናቸው:: ብዙ ገበሬዎች የበቆሎ እርሻቸው ምርት አለመስጠቱን በመመልከታቸው፣ የነዚህ ዓይነት በቆሎዎች መሸጫ ዋጋ ከአለፈው ዓመት ጀምሮ እጥፍ ጨምሯል::

በዚህ ዓመት ድርቅ ምክንያት ከዘራቸው የበቆሎ ዘሮች ምርት መሰብሰብ ያለቻለው ገዳ፣ ከመቂ ገበያ በቆሎ ለመግዛት ተገዷል:: የ50 ዓመቱ ገበሬ ገዳ፣ ዝናብ ጠብ ባለማለቱ አንድም ከመሬት ብቅ ያላሉለትን የበቆሎና የባቄላ ፍሬዎች የዘራባቸውን ሌጣ አረም ወደወረሳቸው ማሳዎች እየጠቆመ፣ «በሞትና በህይወት መካከል እንገኛለን::» ይላል::

በህይወት ለመቆየት ከሁለት በሬዎቹ አንዱን ለመሸጥ የተገደደው ገዳ፣ ከሽያጭ በሚያገኘው ገንዘብ ቤተሰቡ ለአጭር ጊዜም ቢሆን በቀን ሁለቴ ብቻ እህል እንዲቀምስ የሚያስችለው ነው:: የመንግስት ድጋፍ የሚጠይቅ የአቤቱታ ፊርማ ለመፈረም እርሱና ጎረቤቶቹ ወደ አካባቢው የመንግስት ቢሮ ተጉዘዋል:: «ምንም እርዳታ የማናገኝ ከሆነ፣ መሞታችን አይቀርም» የሚለው ገዳ፣ «ልጆቻችንን እንዴት መመገብ ይቻለናል?» በማለት የመንግስትን ድጋፍ አስፈላጊነት በጥያቄ ያሰምርበታል::

አንድ ሚሊዬን የሚጠጉ ኢትዮጵያውያንን የገደለው የ1977ቱ ግርቅ በተከሰተበት 25ኛ ዓመት፣ ምንም ዓይነት የድርቅና የርሀብ ወሬ በዚህች በድህነት አረንቋ በተዘፈቀች አገር እስከአሁን በመንግስት ጥብቅ ቁጥጥሮች የሚደረግበት አይነኬ ጉዳይ ነው:: በአስከፊ የምግብ እጥረት በተከሰተ

ሕዝባዊ ተቃውሞ፣ ሁለት የመንግስት ሥርዓቶች በ60ዎቹ እና በ80ዎች እንደተገረሰሱ በአሁኑ ሰዓት በሥልጣን ላይ የሚገኘው መንግስት የሚያውቀው ነው፡፡

ስለጉዳዩ በይፋ ለመናገርና ሌላው ቀርቶ በመመገቢያ ማዕከል ያለን በተመጣጠነ የምግብ እጥረት የተጎዳ ሕፃን ፎቶ ግራፍ እንዲነሳ ለመፍቀድ የሚዳዳቸው የእርዳታ ድርጅቶች ቅጣጥ ወይም ከአገር የመባረር እርምጃ ሊወሰድባቸው ይችላል፡፡ ቪዛዎችን ወይም የስራ ፍቃድ ለማግኘት የተራዘመ ጊዜ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ፕሮጀክቶች ሊራዘሙ፣ መሰረታዊ ቁሶችን ወደአገር ውስጥ ለማስገባት የሚያስፈልግ ማረጋገጫ ከነአካቴው ላይሰጥ ይችላል፡፡ አብዛኞቹ የእርዳታ ኤጀንሲዎች ጋዜጠኞችን ወይም የውጭ ዜጎችን ለጉብኝት መፍቀድ አይችሉም፡፡

በዚህ ዓመት ውስጥ ከአደገኛ ተከታታይ የሰብሎች ምርት አለመስጠት በኋላ፣ አስቸኳይ የምግብ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ኢትዮጵያውያን ቁጥር ባለፉት አስር ወራት ውስጥ ከ4.9 ወደ 6.2 ሚሊዬን አድጓል፡፡ እንዲያም ሆኖ ድርቁን እንዳይመዘግቡ አብዛኞቹ ጋዜጠኞች ወደ ገጠራማ አካባቢዎች እንዳይጓዙ ተከልክለዋል፡፡ አብዛኞቹ የእርዳታ ሰራተኞቹ እየተባባሰ ስላለው የተመጣጠነ የምግብ እጥረት ምንም አስተያየት ከመስጠት ራሳቸውን ይቆጥባሉ፡፡ ስማቸው ካልተሸሸገ በስተቀር፣ አንዳቸውም በግላጭ ከጋዜጠኞች ጋር አይነጋገሩም፡፡

ሌላ የተጣለው ገደብ የበለጠ ጉጂ ነው፡፡ በተያዘው ዓመት የተመጣጠነ የምግብ እጥረትን በተመለከተ የውጭ ድርጅቶች ገለልተኛ ጥናት እንዲሰሩ አልተፈቀደላቸውም፡፡ ከዚያ ይልቅ፣ ከመንግስት ተወካዮች ጋር ነው የሚሰሩት፡፡ ይህም ለመግባባት አስቸጋሪና ጊዜ የሚያባክን አሰራር ነው፡፡ በመሆኑም፣ ክልላዊ አስቸኳይ የእርዳታ ምላሽ እንዲዘገይ ምክንያት ሆኗል፡፡

በመላ አገሪቱ በተካሄደ ጥልቅ ጥናት ውጤት መሰረትነት፣ በኢትዮጵያ በዚህ ዓመት ቢያንስ ሰባት ሚሊዬን ሰዎች አስቸኳይ እርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው ከሐምሌ ጀምሮ የእርዳታ ኤጀንሲዎች የሚያውቁት የነበረ ቢሆንም አምስት ነጥብ ሚሊዬን ህዝብ ብቻ ድጋፍ እንደሚያስፈገው የተከራከረው መንግስት መረጃውን ለማውጣት የተራዘመ ጊዜ ወስዶበታል፡፡

በመጨረሻም ከወራት አደናጋሪ ቆይታ በኋላ፣ 6.2 ሚሊዬን ሕዝብ አስቸኳይ እርዳታ እንደሚያስፈልገው በጥቅምት መጨረሻ ይፋ አደረገ፡፡ ቢሆንም፣ የገለፀው መረጃ ከትክክለኛው ቁጥር ዝቅ ያለና በዚህ ዓመት መጠነ ሰፊ የእርዳታ ጥሪ እንዲደረግ ያላስቻለ የዘገየ እወጃ ነበር፡፡ አሁንም ዳግም ካልዘገየ በስተቀር፣ ሌላ የተረጂዎች ግምት በሕዳር ወር አጋማሽ ይፋ ይደረጋል ተብሏል፡፡

አስቸኳይ እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ሰዎች ቁጥር በተመለከተ የመንግስት ግምት ፖለቲካዊ አንደምታ እየተሰጠው፣ ተቀንሶ ሲነገርና በይፋ ለመግለጽ እየዘገየ፣ ኢትዮጵያን ለመርዳት ዓለም አቀፍ ጥሪ ማቅረብ አዳጋች ነው ይላሉ የእርዳታ ድርጅቶች፡፡ በ2009 ሕዳር፣ የአስቸኳይ እርዳታ ጥሪ በተካሄደበት ወቀት፣ በዓመቱ ሁለት ወራት ብቻ ነበሩ የቀሩት፡፡ ትላልቅ ከሆኑ የእርዳታ ኤጀንሲዎች መካከል በሚጠቀስ ድርጅት የሚሰሩ ሰራተኛ፣ «የዚህ ዓመት ፍልሚያ አብቅቶለታል፡፡ . . . በክረምት የሞት አደጋ ተጋርጦባቸው የነበሩ ህፃናት እስከአሁን ህይወታቸው ያልፋል፡፡»

በአስከፊ ሁኔታ በተጎዱ በተወሰኑ ክልሎች ውስጥ የውጭ ድርጅቶች ለመሰማራት ያላቸው እድል በጣም የተገደበ ነው። በከፊል በሶማሊ ክልል በሚገኙ አማፂዎች ላይ በተሰነዘረው ወታደራዊ ዘመቻ ምክንያት እንቅስቃሴያቸው በጥብቅ ቁጥጥር ይደረግበታል። አብዛኞቹ ትላልቅ ዓለም አቀፍ የእርዳታ ኤጀንሲዎች፣ በ2000ና በ2001 ከክልሉ ተባረዋል ወይም በግፊት ለቀው ወጥተዋል።

መንግስት ከሚያገኘው አስቸኳይ የምግብ እርዳታ ውስጥ እስከ 20 በመቶ ያህሉ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ሰዎች ጋር ከመድረሱ በፊት «ይጠፋል»። እንደአንድ የእርዳታ ሰራተኛ፣ አቅጣጫቸውን የሳቱ የእህል ጆንያዎች በአብዛኛው በወታደራዊ መቀመጫዎች አካባቢ ይታያሉ ይላል።

በተደጋጋሚ እንደሚከሰተው፣ ኢትዮጵያ በኮሌራ በተመታችበት ወቀት መንግስት «ኮሌራ» የሚለው መጠሪያ የሚስበውን አላስፈላጊ ትኩረት ለማስወገድ አጣዳፊ ተቅማጥና ትውከት /አተት/ በማለት ጠርቶታል። በነሐሴ የጀመረው የቅርቡ ኮሌራ፣ በሺህዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን ህመምተኛ ቢያደርግም መንግስት ወረርሽኙን አተት ብሎ በመጥራት የተጠቂዎችን ቁጥር ዝቅ አድርጐ ገልጿል። በተ.መ.ድ. ዶክመንት ውስጥ ትክክለኛው የተጠቂዎች ቁጥር በሰፈረበት ወቅት መንግስት እጅግ በመቆጣቱ ከእርዳታ ድርጅቶች ጋር ያካሂድ የነበረውን ትብብር ለአንድ ወር አቋርጦ ነበር። በመንግስት ቅጣት ፍራቻ ብዙዎቹ ኤጀነሲዎች ራሳቸውን ሳንሱር ወደ ማድረግ ገብተዋል። «በምንሰራበት በጠቅላላ ሁላችንንም የሸፈነ የጭንቀት ብርድ ልብስ ተከናንበናል።» የመንግስት ቁጥጥር ካለፈው ዓመት በበለጠ ተጠናክሯል።

የተወሰኑ ምዕራባውያን ዲፕሎማቶች የሚሉት የመንግስት ማድበስበስና ከሕዝብ መሸፋፈን አስፈላጊ አለመሆኑን ነው ምክንያቱም እንቅጩ መረጃ ለአገሪቱ አስቸኳይ እርዳታ በሚያደርጉ ቁልፍ ድጅች ውስጥ ለወስጥ የሚታወቅ መሆኑ ነው። ከብዙዎቹ የአፍሪካ አገሮች ጋር ሲነፃፀር፣ ኢትዮጵያ እርዳታን በማከፋፈል አንፃራዊ ብቃት እንዳላትና የጤና ጥበቃንና የምግብ አቅርቦትን በገጠራማ አካባቢዎች በስፋት ለማዳረስ፣ ጥሩ ፕሮግራሞችን እያስተዋወቀች ነው ይላሉ ዲፕሎማቶቹ። ሆኖም ሌሎች የሚሉት የመንግስት ለጉዳዩ ያለው የአትንኩኝ አቋምና ገደቦች፣ ዓለም ለኢትዮጵያ የሚሰጠውን አስቸኳይ እርዳታ እያስተጓጎለ በመሆኑ ለወራት የወሳኝ እርዳታ ፍሰት እየተስተጓጎለ ነው የሚል ነው። አንደ የእርዳታ ሰራተኛ እንደሚሉት «ህይወት አድን ምለሽ የምታዘገይ ከሆነ፣ ህይወቶች አይድኑም። . . . ሰዎች ይዳከማሉ፣ ምርታማነትታቸውም ይቀንሳል። . . . አንድን ሁኔታ አስቀድመህ ካወቅከው ወደፊት ለችግሩ የሚሰጠው የምላሽ እድሎች አስቸጋሪነት ይቀንሳል። ሌላ ሰራተኛ «መንግስት በማሊዮኖች በሚቆጠሩ ህይወቶች እየተጫወተ ነው።» የሚል ምልከታውን ያንፀባርቃል።

አስቸኳይ እርዳታ ያሰፈልጋቸዋል ተብለው በፋይ ከተገለፁት 6.2 ሚሊዮን ሕዝብ በተጨማሪ፣ ሌሎች ሰባት ሚሊዮን ሰዎች አስቀድመው የምግብ እርዳታ እየተደረገላቸው ይገኛል። ለዚህም ምክንያቱ ለአስከፊ የምግብ እጥረት ተጋላጭ መሆናቸው ነው። ይህም ማለት ከአጠቃላዩ የኢትዮጵያ 80 ሚሊዮን ሕዝብ ውስጥ 1/6ኛው በእርዳታ እህል ነው የሚተነፍሰው ማለት ነው።

ይህ በአንዲህ እንዳለ፣ ዓለም አቀፉ የገንዘብ ቀውስ ከዓለም አቀፍ ለጋሾች ድጎማ ማግኘትን አስቸጋሪ አድርጎታል:: በዚህ ዓመት ለአስቸኳይ የምግብ አቅርቦት ኢትዮጵያ ለምታርገው ጥሪት ካናዳ 50 ሚሊዩን የአሜሪካ ዶላር ለግሳታለች:: ሆኖም ዓለም አቀፉ የልገሳ ደረጃ ከሚፈለገው መጠን በታች በመሆኑ ለአብዛኞቹ ኢትዮጵያውያን ተረጂዎች የሚሰጠው የምግብ ራሽን የሚያስፈልገውን ግማሹን እንኳን አይደርስም::

የኢትዮጵያ መንግስት ድጋፍ ለማግኘት ጥረቶቹን ድርብ ድርብርብ ከማድረግ ይልቅ በምርጫ 2002 መቃረብ የተሰሳ በአገሪቱ ውስጥ ያለውን ቁጥጥር እጅግ እያጠናከረ ይገኛል:: ኢትዮጵያ የምግብ ቀውስ ደርሶባታል የሚለውን በተመለከተ ጠ/ሚ መለስ ዜናዊ በተደጋጋሚ የካዱት ነው:: «የምግብ እርዳታ ኢንዱስትሪ» እና «የድህነት ጌቶች» የምግብ አርዳታ ሚያስፈልጋቸውን ሰዎች ቁጥር አውቀው አግንነዋል በማለት ይወነጅሏቸዋል::

የእርዳታ ሰራተኞች የስራቸው አስቸጋሪነት እየተባባሰ መሄዱን የሚጠቁሙ አስጨናቂ ዝርዝሮችን እያወጡ ነው:: በአንድ ክልል የሚንቀሳቀስ የእርዳታ ድርጅት ለሶስት ወራት የምግብ ማከፋፈል ስራውን ለማቆም ተገዶ ነበር:: ለዚህ ምክንያቱ በአገሪቱ ባለ አንድ ሚዲያ በወጣ ጽሁፍ መንግስት ደስተኛ ያልነበረ መሆኑ ነው:: በቅርብ በአዲስ አበባ በተከሰተ ከፍተኛ የቃጠሎ አደጋ 20 ቤቶች ከወደሙ በኋላ ድጋፍ ለማድረግ አንድ ድርጅት ሙከራ አድርጎ ነበር:: በመጀመሪያ በእሳት አደጋ ተከላካዮች ተቀባይነት አግኝቶ የነበረ ቢሆንም የደህንነት ሰዎች በስፍራው ከደረሱ በኋላ ወዲያው ድርጅቱ እንዲለቅ ታዟል:: እንደአንድ ሰራኛ «በጣም ግልጽ ለሆነ አንድ የሆነ አደጋ ድጋፍ ልናደርግ ብንችል እንኳ አያቀርቡንም፣ ይጠረጥሩናል::»

አብዛኞቹ የውጭ ጋዜጠኞች ከአዲስ አበባ ውጭ እንዲጓዙ አይፈቀድላቸውም:: ገጠራማ ክልሎችን ለመጎብኘት *«The Glob and Mail»* ሁለት ጊዜ የፍቃድ ጥያቄ ቢያቀርብም ሁለቱንም ጥያቄ ውድቅ ነበር የተደረገው:: በመጨረሻም፣ ከታወቀብኝ መታሰሬን በመቀበል ካለፍቃድ ለመጓዝ ተገደድኩኝ:: በገጠራማ ወረዳዎች ውስጥ ስለምን መዘገብ እንደተከለከልኩኝ አንድ የመንግስት ባለሥልጣን በጠየኩበት ወቅት በጣም በርካታ ጋዜጠኞች ድርቁን በተመለከተ ከፍተኛ የመዘገብ ፍላጎት እንዳላቸውና ሙሉ በሙሉ ድርቁ የተከሰተው በአየር ንብረት ለውጥ እንጂ ከመንግስት ጋር ምንም እንደማያገናኘው ነግሮኛል::

የመመገበያ ማዕከል ለመጎብኘት ፍቃድ ያገኙ በጣም ጥቂት ጋዜጠኞች ሁሌም ቢሆን በመንግስት «ተጆሮዎች» እንደታጀቡ ነው:: የማዕከላቱ ሰራተኞች ከውጭ ጋዜጠኞች ጋር ከተገናኙ በኋላ አንዳንዴ በመንግስት የደህንነት ሰዎች ምርመራ የሚደረግባቸው በመሆኑ አንድም ነገር ከመናገር በሚከለክላቸወ ፍርሃት ይወረራሉ:: ለሥርዓቱ ወዳጆች አይደሉም የተባሉ የውጭ ሪፖርተሮች «የአደገኛ ስም ዝርዝር» መንግስት አለው:: የተወሰኑ ጋዜጠኞች ከኢትዮጵያ ተባረዋል፣ ውደኢትዮጵያ እንዳይገቡ ታግደዋል ወይም ኢትዮጵያ ሲደርሱ በአዲስ አበባ አየር ማረፊያ በቁጥጥር ስር ውለዋል:: በርካታ ለውጭ ሚዲያ በዘጋቢነት የሚሰሩ ኢትዮጵያዊ ጋዜጠኞች የመንግስት ቅጣት ፍራቻ አገር ለቀው ተሰደዋል::

የኢትዮጵያ መንግስት፣ ከቻይና የኢኮኖሚ አጋሮቹ ቴክኖሎጂ በማግኘት እንደ «አመንስቲ ኢንተርናሽናል» እና «ሲ.ፒ.ጄ.» ያሉ ሥርዓቱን የሚተቹ በርካታ ድረ-ገጾችን አግዷል:: በተመሳሳይ

አንድ ዓይነት የቻይና ቴክኖሎጂ በመጠቀም የኢ-ሜይል እና የተንቀሳቃሽ ስልኮች መልዕክቶችን ለመጥለፍ የአገሪቱ ባለሥልጣናት ተችሏቸዋል:: ይህም የእርዳታ ኤጀንሲዎች እና ጋዜጠኞች ንግግሮቻቸውና መልዕክቶቻቸው በምስጢር ይጠለፋል የሚል ፍሀት አስጨንቋቸዋል::

ድርቅ ወዳጠቃት መቂ እንመለስና፣ ጉደታ በሪሶ የተባለ ገበሬ፣ በአና ሜዳዎች የተከበበ የደረቀ የበቆሎ ማሳ እየጠቆመ፣ «ድሮ በመልካም ጊዜ፣ ይህ ማሳ በጠቅላ በበቆሎ የተሸፈነ ነበር::» በማለት የአሁኑንና የቀድሞውን ሁኔታ ያነፃፅራል:: «አሁን ምንም አይታይህም:: ማሳዎቹ እንዲሁ ጥቅም የሌሸ ናቸው:: ለሁለት ዓመት ጥሩ የበቆሎ ምርት ለመሰብሰብ አልቻልንም:: መጭው ጊዜ አስጨንቆናል:: ለእርዳታ እየጮህን ነው::» ይላል ልብ በሚነካ አገላለፅ::

*/ጆፍሬይ ዮርክ በካናዳው «The Glob and Mail» የአፍሪካ አህጉር ዘጋቢ ነው::/*

# የቻይና አልባሳት፣ ሃይገር ባስ እና ቀለበት መንገድ፤ ቻይና የደረሰችበት ያደርሱን ይሆን?

**በፍስሐ ያዜ**

የተቀመጠው ርዕስ ባቀፋቸው ጭብጦች ዙሪያ፣ ከነአስገራሚ ገጽታዎቻቸው ጋር ፈታና ዘና ብለን በመጠኑም ቢሆን በስፋት በተከታይ እንዳስሳቸዋለን:: አስቀድመን፣ መንደርደሪያ የሚሆነንን ነጥብ ማለትም ከጭብጦቹ ጋር ስለሚዛመደውና የአገራችንን ሁኔታ ስለሚመለከተው ጉዳይ በጥቂቱ እናውጋ::

በአገራችን በተደጋጋሚ እንደምናየው፣ በጠቅላላ የመንግስት ባለሥልጣናትና እንዲሁም የእነርሱ (የመንግስት) ተቃዋሚዎች፣ ስለኢትዮጵያ ልማትና እድገት ብሎም መጪ ጊዜዎቿ በየመድረኩ ከልባቸው ይወያያሉ፣ ይስማማሉ፣ ይጨባበጣሉ . . . አጨብጭበውም ይለያያሉ:: ስለልማቷ፣ እድገቷና ስለወደፊት እጣዋ ሲወያዩም፣ እንደምሳሌ የሚጠቅሷቸው በርካታ አገራት አሉ::

እናም፣ «በአጭር ጊዜ» ውስጥ ከፍተኛ የኢኮኖሚ እድገት ያስመዘገቡ ወይንም አስመዝግበዋል ያሏቸውን አገራት ከየአህጉሩ በመምዘዝ፣ በስንት ዓመታት ውስጥ ለዚህ እንደደረሱ «በማውጠንጠን»፣ ለኢኮኖሚያዊ እድገት ያወጧቸው እቅዶችና ፖሊሲዎች ስለነበራቸው የአተገባበር ሂደቶችና ስኬቶች በተቻለ አቅም «ተንትኖ» በመግለጽ፣ የአገራችንን ባለሥልጣናት የሚስተካከላቸው አይገኝም:: መሰል ሂደቶችም ዛሬ ድረስ «ተጠናክረው» ስለመቀጠላቸው ኢትዮጵያዊና ሌሎች ዜጎችም ጭምር አብጠርጥረው የሚያውቁት ነው ብል ተቃውሞ የሚሰነዘርብኝ አይመስለኝም::

ብዙ ጊዜ፣ የኢትዮጵያ ሕግ አውጪ ምክር ቤት ሰፊ ጊዜውን የሚያባክነው፣ የየአገራቱን ኢኮኖሚያዊ እድገት እንደፀሎት በመደጋገም ነው:: ጭራሽ አንዳንዴማ የኢትዮጵያ ሕግ አውጭ ምክር ቤትነቱ የቀረ ይመስል፣ ስለቻይና ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ብቻ በማውራት፣ በሕዝብ የተሰጠውን የአስተዳድረኝ ታላቅ ፖለቲካዊና ሕገ መንግስታዊ ድጋፍ እንዲሁ በፌዝ ያሳልፈዋል::

ምናልባት አሁን አሁን ከቻይና ጋር በጥምረት ስማቸው በተደጋጋሚ የሚስተጋባላቸው አገሮች ብራዚልና ሕንድ ናቸው፡፡

እርግጥ፣ በሌሎች አገራት አርዓያነት ተነሳስቶ የራስን አገር ለማሳደግ መጣርና እነዚያ አገራት ፈጣን እድገት ያስመዘገቡበትን ምክንያቶች ወይም ፍልስፍናዎች በነቃ አእምሮ ማውጠንጠንና ለውጤታማነት መብቃትና ለመብቃትም መሞከር በጭራሽ የሚነቀፍ አይደለም፡፡ ነገር ግን አንድ አገር ከሌላ አገር፣ አንድ ሕዝብ ከሌላ ሕዝብ፣ የአንድ አገር የሀብት ምንጭ ከሌላው አገር የሀብት ምንጭና ሌሎች መለያየቶች ቢኖሩም፣ ለአገር እድገትና ብልፅግና ሰፊውን ሚና መጫወት የሚችሉ አካላት በአግባቡ ተለይተው መታወቅ አለባቸው፡፡ አለዚያ እንዲሁ በቃልና በመፈክር ብቻ ሌሎች ላይ እንደርሳለን የሚል ግምት ማስተጋባት ያልተገናዘበና አመክንዮአዊነት የሌለው ነው የሚሆነው፡፡

እንዲያ ያሉም ባለስልጣናት ሞልተዋልና ዳግም ስለሁነቱ ቢያስቡበት አይስከፋም፡፡ ለምሳሌ፣ በግማሽ ክ/ዘመን ውስጥ የቻይና ዓለም የተደመመበት እድገት የተመዘገበው፣ አገሪቱ «ከምንም» በመነሳት በካሄደቻቸው አብዮተኛ እንቅስቃሴዎች እንደሆነ ማንም ልቦና ያለው የሚያውቀው ነው፡፡ ይህ ጅማሬዋ ግን ልብ የተባለ አይመስለኝም፡፡ እንዲሁ «በዚህ በዚህ ዓመት ጊዜ ውስጥ ቻይና ላይ እንደርሳለን» ሲባል ስንሰማ፣ ምኞት አለመከልከሉን ብቻ እንረዳለን፡፡

እንዴ! ካለፍሬ እንዲሁ ሺህ ጊዜ ቻይና፣ ቻይና ሲባል መስማታ አያሳፍርም? ያሳፍራል፡፡ የቻይናን የእድገት ሂደት ማብራራት ይመስለኛል አንዱ የባለሥልጣኖቻችን የስራ ድርሻ ነው፡፡ በመሆኑም፣ እዚህ ጽሁፌ ላይ አልዘረዝረውም፡፡ ነገር ግን፣ ቻይና ላይ ለመድረስ ከቃል ያለፈ ጠንካራ መሰረት መጣል እንደሚያስፈልግ መገንዘብ ግድ ይለናል፡፡ ለማንኛውም ወደ ሌላኛውና ከቻይና ጋር ወደ ተያያዘው አግራሞት አዘል ነጥቤ ልዝለቅ፤ የውጭ ምንዛሬ እጥረት ከሚሉን ጋር የሚያያዝ ነው፡፡  ምናልባት ላይ ላዩን የምናውቀው ጉዳይ ሊሆን ይችላል፡፡ ፈጽሞ አስበነው ካላወቅንም ዛሬ በደንብ ለማሰብና ለመደመም እንዘጋጅ፡፡

ውድ አንባቢ፣ ነጥቡን የምንቃኘው በምናባችን ሁኔታውን በመሳልና ከራሳችንም ጭምር በመነሳት ነው፡፡ ለመነሻ፣ አንዲት ኢትዮጵያዊት እንስትን እንጠቀም፡፡ የቻይና ሱሪ በቻይና ቀበቶ ታጥቃ፣ ከንፃቱ የተነሳ የተባዘተ ጥጥ የመሰለ የቻይና «ስኒከር» በቻይና ካልሲ ተጫምታ እናያለን፡፡ በቻይና ግልገል ሱሪ፣ በቻይና ጡት ማስያዣና ከናቲራ እንዲሁም ለፀሀይ ጨረር መከላከያነት /ይመስለኛል/ የቻይና መነጽር አድርጋለች፡፡ የተኳኳለችባቸው የመዋቢያ «ማቴሪያሎች» በጠቅላላ ማለት ይቻላል፣ ቻይና ሰራሽ ናቸው፡፡ ኩሉ፣ ቻፒስቲኩ፣ ምናምን «ኩዎቹ» እዚያው ቻይና ተመርተው የመጡ ናቸው፡፡ አናቷ ላይ የሚታየው «ፀጉሯ» ቻይና ሰራሽ  ነው፡፡ ጆሮ ጌጧ፣ የእምብርቷ ሎቲ ሳይቀር! በእጇ ያንጠለጠለችው ቦርሳ እንኳን የቻይና ምርት ነው፡፡ ውስጡ የሚገኙ -ት ቁሳቁሶችም እንዲሁ፡፡ የያዘችው ተንቀሳቃሽ ስልክ «Made in China» ይላል፡፡ በቃ፣ ሁለመናዋ በቻይናና በቻይና የኢንዱስትሪ ውጤቶች የታጀለና የታጀበ ነው፡፡ ከዚያም በቻይና ሰራሹ ሃይገር ባስ ተሳፍራ፣ በቻይና ቀለበት መንገድ ተጉዛ ወደ ስራ ቦታዋ ወይም ወደ ት/ቤት ትደርሳለች፡፡ በመጨረሻ፣ «ወይ ቻይና!» ማለታችን አይቀርም፡፡

አግራሞቱ በዚህ ተወስኖ የሚቀር አይደለም:: ለምሳሌ፣ እህታችን የደረሰችበት የስራ ቦታ ወይም አንድ ት/ቤት ሊሆን ይችላል:: እናም፣ እዚያም የሚጠብቃት ቁሳቁስ ሁሉ የቻይና ምርት ነው:: የመፃፊያ ብዕሩና ወረቀቱን ጨምሮ ካርቦኑም ሆነ ሌላው ቁሳቁስ የቻይና ምርት ነው:: እንግዲህ ነገሩን ጠቅለል አድርገን እናምጣውና ወንዱም፣ ሴቱም፣ መ/ቤቱም ሆነ መጓጓዥ መንገዱና ኦቶሞቢሉ ሁሉ ቻይናን ሳያስታውሰን አይለቀንም:: ስለዚህም፣ እስኪ «እኛ» እያልን የእኛ ንና የቻይናን ምርቶች ቁርኝት በመጠኑ እንይ::

ከላይ እንዳየነው፣ መላ ኢትዮጵያውያን ማለት ይቻላል ከንጋት አስከ ምሽት፣ ከቤት እስከ መ/ቤት፣ ከት/ቤት እስከ መዝናኛ ቦታዎች . . . (ከምንመገበው ምግብ ውጭ ማለትም እንችላለን)፣ «ቻይና» መሆናቸው ፍንትው ብሎ ይከሰትልናል:: በአጠቃላይ፣ ውሎና አዳራችን ከ«ቻይና» ጋር ነው ቢባል፣ ልዩነቱ በስጋና በመንፈስ መሆኑን አስምረንበት ልንስማማበት እንችላለን::

ሰፊውን አግራሞት የሚያጭርብን ምንድን ነው፣ በየእያንዳንዷ እንቅስቃሴያችን የቻይናን ቁሳቁስ ሳንጠቀም አንዲትም እርምጃ መራመድ አለመቻላተን ነው:: ጓዳና ኩሽናችን ውስጥ የሞሉት (ከሞሉ ማለት ነው) የመገልገያ መሳሪያዎቻችን በአብዛኛው የቻይና ስራቶች ናቸው:: ይህን ስናስብ፣ ከዓለም የህዝብ ብዛት ሩብ የሚያህለውን የያዘችው ቻይና ምን ያህል ትጉህ አገር መሆኗን ተረድተን፣ ምናልባትም እንደባለውለታ ቆጥረናት፣ አቅምና ፍላጎታችንን በማወቋ ተገርመንና እንዲሁም ጠቅማን መጠቀሟ አስደስቶን በዝምታ ልናልፍ እንችላለን::

የቻይናውያን የእያንዳንዱን አገር ፍላጎት ጠንቅቀው ማወቃቸውን በማወቃችን እውነታ ከመደነቃችን ባሻገር፣ «መረጃ ሕይወት ነው» የሚለውንና ዘርፈ ብዙ ትርጓሜ ያለውን አባባል በአስገራሚ ገጽታው መተርጎምና መተግበራቸውን እንረዳለን:: የአንድን አገር ህዝብ ፍላጎት ጠንቅቆ ከማወቅ ያለፈ ምን መረጃ አለና?

መቼም የቻይናን ምርትና በአገራችን እየሰጠ ያለውን አገልግሎት ዘርዝሮ ለመጨረስ መሞከር፣ አባይን በጭልፋ ሳይሆን በማንኪያ ነው የሚሆነው:: እናም፣ የቻይና ምርት የሆኑ የእቃ መጠሪያ ቃላቶችን በማያያዝ፣ ዓረፍተ ነገር ሰርቼ ጥቂቱን ለመግለጽ ልሞክር:: በጠባብ ቤት ውስጥ ከሚገኘው የጥፍር መቁረጫ ተነስቼ፣ በፀጉር ማበጠሪያ አድርጌ፣ ሹካ ማንኪያውን፣ ትሪ ብርጭቆውን እያተራመስኩ፣ ሬዲዮና ባትሪውን እየጎረጎርኩ፣ «ቻርጀር» «አዳብተሩን»፣ ገመዳ ገመዱን እየበጣጠስኩ፣ መስታወት ሰዓቱን እየሰባበርኩ፣ ቡታ-ጋዝ በራድን፣ ድስት መክተፊያውን እየረጋገጥኩ፣ ፓስታ ማጥለያውን፣ ሾርባ ማቅረቢያውን እያጣመምኩ፣ «ቪሲዲ»ና «ዲቪዲ»ውን ካሴቱንም እያንኳኮትኩ፣ መጋረጃና አንሶላውን ቀዳድጄ ሁሉንም ባንድነት ሰብስቤ፣ ፍሊትና የማሽን ቀለሞችን እላያቸው ላይ አፍስሼ፣ በቻይና ላይተር ባነደው እንኳ የቻይናን ምርት አልጨርሰውም - እንኳንስ እያስታወስኩ በጽሁፍ ዘርዝሬም ማለት ነው::

መቀስ፣ ቢም መላጫና ምላጭን ለምን እንደረሳሁ አላውቀም:: ብቻ ምን አለፋችሁ፣ «ቻይናን የፈጠረ አምላክ ይባረክ!» ያላለ ሀበሻ የለም ቢባል አልተጋነነም:: እውነትም ቻይና ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም እያበረከተች ያለችው ሚና በቀላለ የሚታይ አይደለም (የዋጋው መርከስ ምክንያት ቢኖረውም)::

እና እላችኋለሁ፣ ቻይና ትገርመኛለች:: አገሯን ይሁን ህዝቦቿን አላውቅም:: ብቻ ግን ቻይና ሲባል ስሰማ ወይም ስንሰማ ከኢትዮጵያ ክልሎች አንዷ የሆነች ያህልና በቅርብ ርቀት የምናገኛት ጎረቤታችን ትመስለኛለች:: እያንዳንዱ ሀበሻ ቤቱ ገብቶ እቃዎቹን ሁሉ ቢያይ፣ ከአጠቃላይ ቁሳቁሱ መካከል በግምት 90 በመቶው የቻይና ምርት ሆኖ ያገኘዋል:: ቤታችን ከባህር-ዛፍ እንጨተ የተሰራ ነው ብንል እንኳን በመስኮትና በበሩ፣ አሊያም በኮርኒሱ ወይም ከወደ ቁልፉ እንመልከት:: ያኔ ቻይና ከነአስገራሚ ስራዋ ፊታችን መጥታ ድቅን ማለቷ አይቀርም:: ይህም የመሪዎቿንና የዜጎቿን ብርታት ከማድነቅ ያለፈ የቻይናና የቻይናውያን አቅርቦት በሁሉም ጓዳ አያንኳኳች መግባቷ፣ ለአንድ ብቻ ሳይሆን ለብዙና ለተደጋጋሚ አግራሞት ይዳርገናል::

ይህ ሁሉ ጥቃቅንና ከፍተኛ ቁሳቁስ፣ በሕገ-ወጥ መንገድም ይግባ በሕጋዊ፣ ዞሮ ዞሮ ከምንዛሬ ጋር መነካካቱ አይቀርም:: በግለሰብ ደረጃም ይሁን በመንግስት ደረጃ ቢገባ ያው ነው:: ስለዚህ ቻይና ያደገች አገር ብቻ ሳትሆን በማደግም ላይ ያለች አገር ናትና ስለሷ እድገት አውርቶ መጨረስ ስለማይቻል «ቻይናን ብንወስድ...» እየተባለ የሚጀመር ንግግር ቀርቶ ወደተግባር ይገባ ነው ለማለት የተፈለገው:: ያኔ ቻይና ላይ መድረስ ብቻ አይደለም መብለጥም ይቻላል::

እንግዲህ፣ «ቻይና እንደርስ ይሆንን - በእርሷ ሱሪ፣ ጫማ፣ ባስና ቀለበት መንገድ ተጉዘን?» በሚል ርዕስ ይህን ጽሁፍ የፃፍኩትና ለጊዜው የምደመድመውም በቻይና እስክሪብቶና ወረቀት መሆኑን እየገለጽኩ፣ በቻይና ማደግና መመንደግ እንዲሁም በእድገቷ እየማለሉ መቀመጥ እንደሚያበቃ ያለኝን ተስፋ አሰምርበታለሁ::

አማን ያቆየን!

# ስፖርት

# መዳን ያለባቸው ዓይኖች

**40 ዓመት በኢትዮጵያ ስፖርት ጋዜጠኝነት ውስጥ የጉላ ድርሻ ያበረከተው ደምሴ ዳምጤ ሁለት ዓይኖች ከፍተኛ ህክምና በቶሎ የሚያስፈልገው አደጋ ተጋርጦባቸዋል:: ከጋዜጠኛው ጋር ቆይታ ያደረገው የአውራምባ ታይምስ የስፖርት ዴስክ ኤዲተር *አቢል ዓለማየሁ* የደምሴን ታላቅነት እየዘከረ አጠገቡ መሆን እንደሚገባን ይነግረናል::**

በምኒልክ ሆስፒታል ቁልቁል ሲወርዱ ጀርመን ኤምባሲን ያገኛሉ:: እዚያ ደርሰው የጋዜጠኛ ደምሴ ዳምጤን ቤት ቢጠይቁ ማንም ተሽቀዳድሞ ቆርቆሮውን በር እንዲያንኳኩ ይነግርዎታል:: ወደ ጠባቧ የደምሴ ቤት ሲዘልቁ የዝናና የኑሮን ልዩነት በእጅጉ ይረዱበታል:: 40 ዓመት በጋዜጠኝነት የገነባው ስም ጥሩ ቤትና ኑሮ አልሆነውም:: ዛሬ ሁለት ዓይኖቹ ላይ ህመም አጋጥሞት በቶሎ በውጪ ሀገር ህክምና ማግኘት ወይም የዓይን ብርሃኑ ማጣት የተባሉ ሁለት የግዴታ አማራጮች ከፊቱ ተደቅነውበታል:: የጉዳቱ ከፍተኛነት ከሚወደው ሙያውም አርቆታል:: ግነት አይደለም ተወዳጁ፣ ትሁቱ፣ ሰው አክባሪው፣ ተግባቢው ጋዜጠኛ ደምሴ ዳምጤ ዛሬ ጽሁፍ መለየት የማያስችለው ደረጃ ላይ ነው::

## 40 ሻማ የማጥፋት ጉዞ

ወደ ስፖርት ጋዜጠኛነት ያመጣው «ቁጭት» ነው፡፡ የትውልድ ቦታው የሐረርጌ የስፖርት እንቅስቃሴ በመገናኛ ብዙሃን ላይ ሽፋን አለማግኘቱ ያንገበግበው ነበር፡፡ በተለይ ኢትዮጵያ በታሪኳ ያነሳቻው ብቸኛው 3ኛው የአፍሪካ ዋንጫን ካስገኙት ተጨዋቾች መካከል ስድስት ያህሉ ከዚሁ ክ/ሀገር የተገኙ ሆነው «እንዴት የሐረርጌ ስፖርት የዜና ሽፋን ድርቅ ይመታዋል?» የሚል የልጅነት እልህ ስፖርቱነተ እንዲቀርብ ዋና መንስዔ ሆኖታል፡፡

ደምሴ ከ1962-68 ዓ.ም. ድረስ ከሐረር አዲስ አበባ ዘገባዎቹን እየላከ ለ7 ዓመታት ያህል በአማተርነት አገልግሏል፡፡ በ1968 ዓ.ም የኢትዮጵያ ሬዲዮ ባልደረባ የነበሩት አቶ ነጋ ኃብተሥላሴ ካናዳ፣ ሞንትሪያል ኦሎምፒክን ለመዘገብ ተጉዘው በመቅረታቸው እሳቸውን በመተካት ጣቢያውን በቋሚ ሠራተኛነት ተቀላቅሎ ላለፉት 34 ዓመታት በድርጅቱ ውስጥ አገልግሏል፡፡ የጋዜጠኛነትን «ሀሁ» መቁጠር ከጀመረ ግን ባለፈው መስከረም 12 ቀን 40 ሻማ ለኩሷል፡፡

## ዳኙ ገላግሌና ደምሴ

በኢትዮጵያ ውስጥ በሕይወት የሚገኙ የስፖርት ጋዜጠኞች ስም ጥራ ተብሎ «ደምሴ ዳምጤ» ብሎ የማይጀምር ማን አለ? ደምሴንና በ1980 ዓ.ም. ኢትዮጵያ አዘጋጅታ ዋንጫ ያነሳችበትን የምስራቅና መካከለኛው አፍሪካ ዋንጫንስ እንደምን ለያይቶ ማየት ይቻላል?

በሻምፒዮናው ፍፃሜ የተገናኙት ኢትዮጵያና ዚምባብዌ የመደበኛውን የጨዋታ ሰዓት በአቻ ውጤት በማጠናቀቃቸው ወደ መለያ ምት ያመራሉ፡፡ የመጨረሻዋን ወሳኝ ምት ዳኛቸው ደምሴ መረብ ላይ አሳርፎ ሀገራችን ዋንጫ ማንሳቷን ሲያውጅ የመጨረሻውን የጨዋታ ክፍል እያስተላለፈ የነበረው «ደምሴ ዳምጤ» ያሰማው ከፍተኛ የጩኸት ድልን አብሳሪ ድምጽ [ዜማ] ማንም አይረሳውም፡፡ ከዳኛቸው (በአሁን ሰዓት የቅ/ጊዮርጊስ ቡድን ም/አሰልጣኝ ነው) ምት በፊት «ዳኙ ሊገላግለን ነው፣ ሊገላግለን ነው፡፡ ዳኙ ገላግለን» ሲል እንዲሁም ከምቱ በኋላ «ዳኙ ገላግሌ» እያለ ያወጣው የነበረው ስሜታዊ ድምጽ የደምሴ መታወሻ ትሩፋቶቹ ናቸው፡፡ «ዳኙ ገላግለን» የሚለውን ቅጽል ስምም ደምሴንም ሆነ ዳኛቸውን ለማስጠራት ላለፉት 22 ዓመታት ጠቅሟል፡፡

በዚህ ታሪካዊ ቀን ስታዲየም መግቢያ ትኬት ለመቁረጥ ከሌሊቱ 10 ሰዓት ጀምሮ ወረፋ ጠባቂዎች ተኮልኩለው የነበረ ሲሆን ደምሴም ከጠዋቱ 1 ሰዓት ጀምሮ እዚያው ነበር፡፡ ብዙዎችም እየቀረቡት «ዛሬ እንዴት ነው?» የሚል ጥያቄ ሲያቀርቡለት «በእርግጠኝነት እናሸንፋን» የሚል መልስ ይስጣቸው እንጂ ጨዋታው እንዳሰበው አልነበረም፡፡ ዚምባብዌ አስቀድሞ በማግባቱ ገ/መድኅን ኃይሌ ባለቀ ሰዓት አቻ የምታደርገውን ጐል እስኪያስቆጥር ድረስ ውጥረት ነግሶ ነበር፡፡ «በእለቱ ሰዉ ተስፋ ቆርጦ ከስታዲየም ይወጣ ነበር፡፡ ገ/መድኅን አቻ ሲያደርግ የህዝቡንም ሆነ የእኔን ደስታ መግለጽ ይከብዳል፡፡» የሚለው ተወዳጁ ጋዜጠኛ ደምሴ ዳምጤ የመጨረሻዋን መለያ ምት ዳኛቸው ሊመታ ሲዘጋጅ የነበረውን ስሜት ሲገልጽ ዛሬም ጭንቀት ይገባዋል፡፡ «እኔም ተጨንቄ ህዝቡንም አስጨንቄ ነበር፡፡ ዳኙ የመጨረሻውን ምት ሊመታ ሲል «ዳኙ ባክህን ገላግለን» እያልኩ የልመና ያህል የሲቃ ድምጽ አወጣ ነበር፡፡» ሲል ይገልፃል፡፡ ደምሴ ዛሬ ይህን ስሜታዊ ድምጽ መስማት አይመርጥም፤ ዛሬም ጭንቅ፣ ጥብብ ይለዋልና ነው፡፡

በወቅቱ የደምሴ ድምጽ «ዳኘ ገላግለን» የሚል ታርጋ ለጥፎ በጥቁር ገበያ ለሽያጭ ቀርቧል፡፡ ደምሴ በተጓዘባቸው ሀገሮች መኖሪያ ቤትም ሆነ ስቱዲዮ ሲጋበዝ «ዳኘ ገላግለን» ይከፈትለታል፡፡

## «የአቅሜን ያህል ሰርቻለሁ»

አራት አስርት ዓመታት በስፖርት ጋዜጠኛነት የሰራው ደምሴ ዳምጤን «የሚጠበቅብህን ያህል ለሀገርህ አገልግለሀልን?» ብዬ ለመጠየቅ አዕምሮዬ «በሚገባ» ሲል የሚሰጠኝን ምላሽ ሰምቼ ብቻ አልተውኩትም፤ ጠየቅኩት፡፡ ማመንታት ጀመረ፡፡ ባለበት የሙያ መስክ ጠብታ የማትሞላ ነገር ከውነው ያዙኝ ልቀቁኝ ባዮች በበዙበት ሀገር የደምሴ በቶሎ «በትክክል» ብሎ ምላሽ አለመስጠት «ራሳቸውን ዝቅ ዝቅ የሚያደርጉ ብፁዓን ናቸው» የሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ለማክበር ይሆን ስል ራሴን ጠየኩ፡፡ ደምሴም ፈጥኖ «አዎ» አይበል እንጂ የኢትዮጵያ ስፖርት አፍቃሪ አጥጋቢ መረጃ እንዲያገኝ መትጋቱንና መጣሩን ያምናል፡፡ «በተቻለኝ መጠን የውጪ ም ሆነ የሀገር ውስጥ መረጃ ለስፖርት አፍቃሪው እንዲደርስ ጥሬያለሁ፡፡ በተለይ ሀገራዊ ሥራዎችን ብዙ ሰርቻለሁ፡፡» የሚለው ደምሴ በቀድሞ ጊዜ የውጭ ሀገር ስፖርት አፍቃሪ እምብዛም በመሆኑ ትኩረታቸው አገራዊ መረጃዎች በፍቅርና በተቆርቋሪነት ስሜት ማንሸራሸር እንደነበር ይናገራል፡፡ «ከጓደኞቼ ጋር የምንችለውን ያህል ለሀገራችን ስፖርት ሰርተናል ብለን እናስባለን፡፡ የሚያሳዝነኝ ግን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ለታላቅ አህጉራዊ ድል በቅቶ አለማየቴ ነው» ይላል፡፡ «በአትሌቲክስ ግን በእጅጉ ረክቻለሁ፡፡ የእግር ኳስ ህመሜን መጠገኛዬም አትሌቲክስ ነው፡፡»

ደምሴ ስሜታዊነትን በማይፈልገው የጋዜጠኛነት ሕይወት ውስጥ መሆኑ ባይዘነጋም ሀገራዊ ስሜቱ በተደጋጋሚ ሲፈታተነው ኖሯል፡፡ «ስሜታዊ መሆኔ ጥሩ ነው አልልም፤ መረጃን በአግባቡ ማቅረብ እስከቻልኩ ድረስ ስሜታዊ መሆኔ መጥፎም ላይሆን ይችላል፡፡» ሲል የሚገልፀው ትሁቱና ሰው አክባሪው ጋዜጠኛ «ዳኘ ገላግለን» በካሴት የተሸጠው በስሜት የተሰራ የቀጥታ ስርጭት ስለሆነና ህዝብ ስለወደደው ነው ብሎ ቢያምንም ለወጣት ጋዜጠኞች ግን ዘወትር «ስሜታዊ እንዳትሆኑ» ሲል ይመክራል፡፡ «የአንተ ስሜታዊነት ፍቅርና እውቅና አስገኝቶልህ የለምን?» ብለው ቢሞግቱትም «የእኔ የስፖርት ሳይሆን የሀገር ፍቅር ጉዳይ ነው፡፡» ሲል ምላሽ ይሰጣቸዋል፡፡ «ሌሎች ሁለት ብ/ቡድኖች የሚያደርጉትን ጨዋታ አስተላልፍ ብትለኝ ቀዝቅዤ ቁጭ እላለሁ፡፡ የኢትዮጵያ ብ/ቡድን ሲጫወት ግን መሸነፉ ስለበዛ ከሀገር ፍቅር የመነጨ ስሜታዊነትን አምጥቷል» ይላል፡፡

## «ለሀገሬ ምን አደረኩ?»

የአሜሪካው የቀድሞ ፕሬዝዳንት የጆን ኤፍ ኬኔዲ «ሀገሬ ምን አደረገቺልኝ ሳይሆን ለሀገሬ ምን አደረኩ በሉ» የሚለውን መርህ የሚከተል ይመስላል፡፡ «ለስፖርት ምን አደረኩ እንጂ ስፖርት ምን አደረገልኝ ብዬ ራሴን አልጠይቅም» ባይ ነው፡፡ ይህም የታላቁ የስፖርት አባት የአቶ ይድነቃቸው ምክር መሆኑን ተናግሯል፡፡ «ማንም ሰው ሸንብራ ቆርጥሞ [ገንዘብ አጠራቅሞ] ሊያየው የማይችለውን 32 ሀገራት ጐብኝቻለሁ» ሲል አገኘሁ የሚለውን ትሩፋት ገልጿል፡፡ «የምኖረው በቀበሌ ቤት ውስጥ ነው፣ መኪና የለኝም፡፡ በዚህ ግን አልቆጭም፡፡ በማገኘው ደሞዝ

ቤተሰብ አስተዳድራለሁ፣ ልጆቼን አስተምራለሁ፣ ደስታዬም ይህ ነው» የሚለው ደምሴ ሁሌም በአገኘው አጋጣሚ «ቆንጆ» ሲል የሚገልፃቸውን 3 ሴት ልጆቹን በጥሩ ሁኔታ እያስተማረ እንደሆነ ገልፆ የመጀመሪያ ልጁም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሁለተኛ ዓመት ተማሪ መሆኗን ተናግሯል፡፡

«በስፖርት ብዙ ተጠቅሜያለሁ ባይ ነኝ፡፡ ትልቅ የህዝብ ፍቅር አግኝቻለሁ፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ በጣም እንደሚወደኝ አውቃለሁ፡፡ መንገድ ላይ ቆሜ የሚያልፈኝ መኪና የለም፡፡ ታክሲ ላይም ሰው ተሸቀዳድሞ ይከፍልልኛል፣ መዝናኛ ቦታ ገብቼ ማንም ይጋብዘኛል፡፡ 'ጥሬ ስጋ ትወዳለህ አሉ' ብሎ ልኳንዳ ቤት የሚከተኝ ብዙ ነው፡፡ ከስፖርት ጋዜጠኞች በርካታ ሀገር የመሄድ እድል ያጋጠመኝ እኔ ነኝ፡፡ በርካታ የአፍሪካ ሀገራት ሄጃለሁ፡፡ በአውሮፓ እንግሊዝ፣ ጣሊያን፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ፖላንድ፤ እንዲሁም አሜሪካና ካናዳ ተጉዣለሁ፡፡» የሚለው ደምሴ ዳምጤ የሚወዳቸው እና የሚወዱት አትሌቶች በአትላንታ፣ በአቴንስ እና በቤጂንግ ኦሎምፒክ ታላቅ ውጤት ሲያስመዘግቡ በቦታው ተገኝቶ ደስታቸውን ተጋርቷል፤ ጮቤ ረግጧል፡፡ «ከዚህ በላይ ታዲያ ጥቅም ምን አለ?» ሲልም ራሱንና የዚህን ጽሁፍ አዘጋጅ ጠይቋል፡፡

ደምሴ በስፖርት ከላይ የገለፃቸውን ትሩፋቶች ጠቅሶ «ተጠቅሜያለሁ» ቢልም በገንዘብ ደረጃ አይደለም፡፡ ከኦሎምፒክ መልስ ከአትሌቲክሱ ልኡካን ጋር ከሚያገኛቸው ጥቃቅን ገንዘቦች ውጭ ኑሮው ደስታ፣ ኪሱ ባዶ ነው፡፡ አገኘሁት የሚለው ትልቁ ብር ከቤጂንግ ኦሎምፒክ መልስ የተሸለመው የ10 ሺህ ብር ሽልማት ነው፡፡ «ከ100 ግራም በላይ ይሆናል» የሚለው የወርቅ ሽልማት በተለያየ ወቅት ከተለያዩ ክልሎችና አፍቃሪዎቹ አግኝቷል፡፡ ሱሉልታ ከተማ ላይ የ200 ካሬ ሜትር ቦታ በሽልማት ቢበረከትለትም የመስሪያ አቅም ስለሌለው መስራት አላሰበም፡፡ «አንድ ቀን ግን አይቀርለትም» ሲል እንደሚሰራበት አስምሯል፡፡ የኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ የሚሊኒየሙን ሽልማት ባበረከተ ጊዜ እንደ ታላላቆቹ አትሌቶች ሁሉ እሱም ከጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ እጅ ልዩ ሽልማት ተቀብሏል፡፡ «ይገባዋል» ያላለም አልነበረም፡፡ ይህ ልዩ ሽልማት «ሞራሌን ከፍ አድርጎታል» ብሏል፡፡

## የዓይን ነገር

የደምሴ አይኖች የእርሱ ብቻ አልነበሩም፤ የመላው የኢትዮጵያ ስፖርት አፍቃሪ ጭምር እንጂ፡፡ የስፖርት የመረጃ ክፍተትን ለመሙላት በፍቅር ላለፉት 40 ዓመታት ራሱን ሰጥቷል፡፡ ድርጊትን በአትኩሮት የሚከታተሉት ዓይኖቹ አንጀት አርስ ዘገባዎቹን በጉጉት ለሚጠብቁት አድማጮቹ ለማድረስ ዋና ተዋንያን ናቸው፡፡ ከዚያም ባሻገር ገሳጭ፣ መካሪ እና ለሀገር ተቆርቋሪነትን የሚያሳዩ ግላዊ አስተያየቶቹን ከመስጠት ተቆጥቦ አያውቅም፡፡

የኢትዮጵያ ብ/ቡድን ከሜዳውም ሆነ ከሜዳው ውጪ ጨዋታ ሲያደረግ በቀጥታ ሥርጭት ኮሜንትሪ የሚሰራው ደምሴ ከስሜታዊነቱ እየተሟገተ ስፖርት አፍቃሪው ጨዋታውን በዓይኑ ያየ እንዲመስለው ሲጥር የነበረ ጋዜጠኛ ነው፡፡ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ባለውለተኞችን ከቅድመ እውቅና እስከ ድህረ እውናቸው የሰሩትን ታሪኮች ሲዘክርና ሲዘግብ ኖሯል፡፡ በጆሮ ገዢ ድምፁ ሲያስተላልፋቸው የነበሩትን ፕሮግራሞች ማዳመጥ ሳይሆን አለማዳመጥ መቻል ከባድ ነው፡፡ ዛሬ እነዚያ ቀርፀው የማይረሱትና ተናፋቂ ዘገባዎቹን ለማንፎልፎል ዋና ተዋናይ የሆኑት ዓይኖቹ

ተዳክመዋል፤ ታመዋል፤ አስፈላጊ የሕክምና እርዳታንም ይሻሉ፡፡ ይህ ደግሞ በደምሴ አቅም የሚሞከር አይደለም፡፡

ከሃያ ዓመት በፊት የኢትዮጵያ ብ/ቡድን ወደ ግብፅ ተጉዞ 6-1 ሲሸነፍ ከቡድኑ ጋር አብሮ የነበረው ደምሴ በካይሮ የጀመረው ህመም አዲስ አበባ ሲደርስ ባሰበት፡፡ ሲመረመር «ስኳር» እንዳለበት ይነግሩታል፡፡ «በወቅቱ ስኳር ምን እንደሆነም አላውቅም ነበር» የሚለው ጋዜጠኛው ህመሙን ችላ ይለዋል፡፡ ከዓመታት በኋላ በድጋሚ ታምሞ ወደ ሐኪም ቤት ሲሄድ ስኳሩ ከፍ ማለቱንና አደገኛ ሁኔታ ላይ እንደደረሰ ተነገረው፡፡ በአሁን ሰዓት የስኳር ህመሙ በጥሩ ደረጃ ላይ ቢገኝም የወለደው ጦስ ግን አለቀቀውም፡፡ ከሦስት ዓመት በፊት ዓይኑን ያዝ ያደርገው በመጀመሩ ባለቤቱ ወ/ሮ ፀሐይነሽ መንግስቱ «መመርመር» አለብህ ብለውት ወደ ሐኪም ቤት ይሄዳል፡፡ «ዓይኖችህ በጣም ተጐድተዋል፤ ባለበት ለማቆየት እጥራለሁ» ሲሉ ያከሙት ዶ/ር ትልቅሰው ተሾመ ቢነግሩትም የደምሴ «ችላ» ባይነት ዓይኑንም ረስቶ ወደ ሥራው ብቻ እንዲያተኩር ያደርገዋል፡፡ ለድጋሚ ምርመራ ወደ ዓይን ሕክምና የተመለሰው ከወራት በፊት ሲሆን ዓይኑ በከባድ ሁኔታ እንደደከመ ተነገረው፡፡ ግራው ዓይኑ ወዳለማየት እንደቀረበ፣ ቀኙም በጣም በቶሎ ሕክምና እንደሚያሻ ተነግሮታል፡፡ ማንበብም እያቃተው ስለመጣ መ/ቤቱ ወጣት ጋዜጠኞችን እንዲያማክርና እንዲያስተባብር ፈቅደውለት ከሚወደው ሙያው ለመለየት ግድ ብሎታል፡፡

በቶሎ ህክምና ካላገኘ የዓይን ብርሃኑን እንደሚያጣ የተረዱት የምኒሊክ ሆስፒታል የሕክምና ቦርድ ውጪ ሀገር ሄዶ ህክምና ማግኘት እንደሚገባው አረጋግጠውለታል፡፡ በጋዜጠኛ አለምነህ ዋሴ የሚመራ የአስተባባሪ ኮሚቴም ደምሴን ለመታደግ እንቅስቃሴ ጀምሯል፡፡ «ኮሚቴ ያቋቋምኩት እኔ ሳልሆን በተቆርቋሪነት የተነሱ ወዳጆቼ ናቸው፡፡ እግዚአብሔር ከረዳቸውና ከተሳካልኝ ወደ ውጪ ሄጄ የዓይን ብርሃኔን ላቆይ እችላለሁ፡፡» ሲል ደምሴ ተስፋ አድርጓል፡፡ በሀገሪቷ የተለያዩ ክልሎች የሚገኙ የተለያዩ ነዋሪዎች ለደምሴ እርዳታ ለማድግ ፈቃደኝነታቸውን በስልክ እየደወሉ እየገለፁለት ነው፡፡ «ደዋዮችን ማስተባበር ከተቻለ ጥሩ ነገር እንደሚገኝ እርግጠኛ ነኝ» ሲል በሙያው አርዓያ መሆን የሚችለው ደምሴ ዳምጤ ተናግሯል፡፡

አትሌት ኃይሌ ገ/ሥላሴ፣ ቀነኒሳ በቀለ፣ ገዛኸኝ አበራ «አለንልህ ከጐንህ ነን» ብለውታል፡፡ የአስተባባሪ ኮሚቴውን የሚመራው አለምነህ ዋሴ የጋዜጠኛው የህክምና ጉዞ እንዲሳካ ጥረት እያደረጉ መሆኑን ይገልፃል፡፡ «የተወሰኑ አትሌቶችና የተለያዩ ድርጅቶችን አነጋግረናል፡፡ ጥሩ ምላሽም ሰጥተውናል፡፡ የህክምና ወጪው ምን ያህል ገንዘብ እንደሚፈጅ አጣሩና ንገሩን እንሸፍናለን ብለውናል» ይላል፡፡ በሦስት ቀን ውስጥ ደ/አፍሪካና ታይላንድ ከሚገኙ ሆስፒታሎች ጋር በመፃፃፍ ዋጋውን አጣርተው ለማወቅ እያጣሩ እንደሆነም ጨምሮ ለአውራምባ ታይምስ ገልጿል፡፡ «ህክምናው የተሳካ እንዲሆን ቃል ከገቡ ግለሰቦችና ድርጅቶች፣ የህክምና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላትና አስተባባሪ ቡድኑ አባላት ኃላፊነት የተሰማው ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡» የሚል መልዕክቱን አለምነህ አስተላልፏል፡፡

የደምሴ ዓይኖች መነጽር ተጠቅመው እንኳን ማንበብና የሚደወሉለትን የስልክ አቅቷቸዋል፡፡ የሚንቀሳቀሰው በባለቤቱ እርዳታ ነው፡፡ «ሲያነብ የኖረ ሰው ሲነበብለት አይረካም፡፡ ማንበብ ባለመቻሉም በጣም መበሳጨት ጀምሯል» ሲሉ ባለቤቱ ወ/ሮ ፀሐይነሽ ነግረውናል፡፡

ጋዜጠኛ ደምሴ ዳምጤ በ1980ው የምስራቅና መካከለኛ የአፍሪካ ዋንጫ «ዳኙ ገላግለን» ሲል የጠየቀው ተማጽኖን ዛሬ ተራው የዓይኑ ሆኗል፡፡ የሚወደው ወገኑ ከአጠገቡ ሆኖ ህክምናው እንደሚሳካ አይጠራጠርም፡፡ «ሁሉን አድራጊ እግዚአብሔር ነውና ነገሮችን ጥሩ እንደሚያደርጋቸው አምናለሁ» ይላል፡፡ ልበ ቀናውን ደምሴ ለማገዝ የሚሰንፍ አለመኖሩን ብዙዎች ይስማሙበታል፡፡ ጉዳዩ «የዐይን» ነውና ደጋግሞ ያባንናል፡፡ ለደምሴ ፍቅሩን መሰሰት የማያውቀው የኢትዮጵያ ህዝብ ብድሩን የሚመልስበት መልካምና ወሳኝ አጋጣሚ «አሁንና አሁን» ብቻ ነው፡፡ ይህ ከሆነ «በዳኙ ገላግለን» በቶሎ የምናስታውሰው ደምሴ ከህመሙ ተገላግሎ «ህዝቤ ህመሜን ገላገለኝ፤ ብርሃኔንም መለሰ» ብሎ ሲያመሰግን እናገኘው ይሆናል፡፡ ደምሴ ይህ እንደሚሳካ ቅንጣት ያህል አይጠራጠርም፡፡

## <u>የስፖርት ዜናዎች</u>

# ጥንዶቹ አትሌቶች አሸነፉ

በሆላንድ ናይሜገን በተደረገ የ15 ኪሎ ሜትር የጐዳና ላይ ሩጫ ኢትዮጵያውያኖቹ ጥሩነሽ ዲባባ እና ስለሺ ስህን አሸነፉ፡፡

ለ26ኛ ጊዜ በተካሄደው የሰቨን ሂልስ 15 ኪሎ ሜትር ውድድር ከ2005 በኋላ የመጀመሪያ የጐዳና ላይ ሩጫ ያደረገችው ጥሩነሽ ዲባባ 46:28 በሆነ ሰዓት በመግባት ***የዓለም ሪከርድ*** በማስመዝገብ ጭምር አሸናፊ መሆን ችላለች፡፡ የ15 ኪሎ ሜትር ሪከርድ አስቀድማ ይዛ የነበረችው ጃፓናዊቷ ካዮኮ ፉኩሺ [46:55] ነበረች፡፡ ሌላዋ ኢትዮጵያዊት ብዙነሽ በቀለ ከጥሩነሽ 1ደቂቃ ከ20 ሰከንድ በኋላ በመግባት ሁለተኛ ስትወጣ ዩክሬንያዊቷ ቴትያና ሆሎፍቭቼንኮ ሦስተኛ ሆናለች፡፡

በወንዶች በተደረገው ውድድር የጥሩነሽ የትዳር አጋር የሆነው ስለሺ ስህን ከዩጋንዳዊው ኒኮላስ ኪፕሮኖ ጋር እስከመጨረሻው ብርቱ ፉክክር ገጥሞት የነበረ ሲሆን ክሩን በጥሶ በመግባት ቀዳሚ ሆኗል፡፡ ውድድሩን ለማጠናቀቅ 42:14 ፈጅቶበታል፡፡ ኬኒያዊው አብርሃም ሮቲች ሦስተኛ ሲወጣ ሌላው ኢትዮጵያዊ አየለ አብሽሮ አራተኛ በመሆን ውድድሩን ፈጽሟል፡፡

ጥሩነሽ በተለይ በውድድሩ የመጨረሻ ኪሎ ሜትሮች ፍጥነቷ አይሎ የታየ ሲሆን አስሩን ኪሎ ሜትር የሮጠችበት 31:23 የዓለም ሪከርድ ነው፡፡ «ለዚህ ውድድር ልምምድ ሰራ የነበረው ከባለቤቴ ጋር አብሬ ነበር፡፡ የጐዳና ላይ ሩጫ የተለየ ነው» ያለችው ጥሩነሽ «ምን እንደሚጠብቀኝ አላውቅም ነበር፡፡ ስለሆነም ውድድሩ ሲጀመር በፍጥነት አሮጥኩም» ስትል አሯሯጧ ጥንቃቄ የተሞላበት እንደበር አስታውቃለች፡፡ «ውድድሩን [የጎዳና ላይ ሩጫን] ወድጄዋለሁ፡፡ ጥሩ ስሜትም ተሰምቶኛል፡፡ ከ10 ኪሎ ሜትር በኋላ ፍጥነቴን ጨምሬያለሁ፡፡ የመጨረሻውን ሦስት ኪሎ ሜትር የመብረር ያህል ተሰምቶኛል» ስትል ውድድሩ ምን ያህል እንደተመቻት የገለፀች ሲሆን የባለቤቷን ማሸነፍ ስትሰማም በጣም መደሰቷን ትናግራለች፡፡ የጐዳና ላይ ሩጫ የተመቻት ቢሆንም የትራክ ሩጫ አሁንም ቀዳሚ ምርጫዋ መሆኑን ተናግራለች፡፡

ስለሺ ስህንም በባለቤቱ አስተያየት ይስማማል፣ «በጋራ ልምምድ ሰርተናል፡፡ ውድድሩን ሁለታችንም በማሸነፋችን ደስ ብሎኛል፤ ጥሩ ነገር አድርገናል» ሲል አስተያየቱን ሰጥቷል፡፡

# ሞቲቬሽን

# ትላንት፣ ዛሬ፣ ነገ

## ትላንት

የትላንት ጊዜ ላይመለስ ቢሄድም ለብዙ ነገሮቻችን መሰረት መሆኑን ግን አያጠራጥርም:: ምክንያቱም ዛሬ እና ነገ ላይ የምንሰራቸውን ስራዎች ስንመለከት ትላንት በተሰሩ ስራዎች ላይ የተመረኮዙ ናቸውና:: ትላንት ላይ ጥሩ ከተሰራ መልካም ታሪክ አለ ማለት ነው፣ ስለዚህ ያን ታሪክ በማሰብ አሁን ላይ ለሚሰሩ ስራዎች ትልቅ ድጋፍ ይሆናል:: ትናንት ላይ ጥሩ ወይም ጠንካራ የሚባል ስራ ካልተሰራ ደግሞ ይህንን በመመልከት እና እንደ ምክንያት በመያዝ ዛሬ ላይ ሆነን መስራት እንድንችል ያደርገናል:: ትላንት ያልተሳካልንን ነገር ምክንያቶቹን ለመፈተሽ ትላንት መኖሩ ይጠቅመናል:: ያልተሰራን ስራ ለመስራት፣ የተሰራን የበለጠ ለማሻሻል፣ የተሻሻለን ነገር ይበልጥ ለማሻሻል፣ የትላንቱ ጊዜ እጅግ ጠቃሚ እንደሆነ አያጠያይቅም::

ትላንት ጠቃሚ አይደለም ሊባል የሚችለው ትላንት መስራት የነበረባቸው የቤት ስራዎች ሳይሰሩ ሲቀሩ ብቻ ነው:: «ትላንት ላይ እነዚህንና ሌሎች ነገሮች ተሰርተዋል» ብሎ ስለእነርሱ ብቻ ማውራትና ማድነቅ ጥቅም አለመኖሩ ብቻ ሳይሆኑ ጉዳትም አለው:: በቀረው ስራ ላይ ከማተኮር ይልቅ ለራሳችን ትላንት ብዙ ስራዎችን ሰርተናል ብለን የበዛ አድናቆትን መስጠት ዛሬ ላይ እንዳንሰራ ያደርገናል:: ከዚህ ይልቅ ባሳለፍነው ጊዜ ከሰራናቸው እና ካከናወንናቸው በጎ ተግባራት ይልቅ መስራት ሲገባን ያልሰራናቸውን የቤት ስራዎች ብንፈልግ እና እነሱን ለመስራትና ለማረም ብንሯሯጥ የተመረጠ ነው::

አዎ! ትላንት ያለፈ ጊዜ ነው:: እንመለስና የትላንትን ጊዜ እንለውጥ ብንል አንችልም:: ትናንትን በተመለከተ ማድረግ የምንችለው ምንም ነገር የለም:: ጥሩ ስራ ከተሰራ መልካም ታሪክ ነው፣ ጥሩም ካልተሰራ ያም ታሪክ ነው:: ማድረግ የምንችለው ወይ ታሪኩን የበለጠ ለማሳመር ሌላ ጥሩ ታሪክ መስራት ወይም የነበረውን ታሪክ ለመቀየር መስራት::

## ዛሬ

ሙሉ በሙሉ በእጃችን ያለ ጊዜ የዛሬ ጊዜ ነው:: ዛሬ ላይ ማድረግ የምንፈልጋቸውን፣ ማሻሻል የምንፈልጋቸውን፣ መለወጥ የምንፈልጋቸውን እና ማንኛውም ነገሮች ዛሬ ላይ ሆነን ሁላችንም ብንሆን ዕድል አለን:: ዛሬ ላይ ለውጥ ካጣን የነገው ታሪካችንን ቀየርን ማለት ነው:: ልክ እንደዚሁ ዛሬ ላይ ለውጥ ካላመጣን የነገ ታሪካችን ተመሳሳይ ነው የሚሆነው ወይም ታሪክ ለመለወጥ ዕድል አልተሰጠውም ማለት ነው::

የዛሬ ጊዜ ሁልጊዜም ቢሆን ይጠቅማል:: ጊዜውን የመጠቀም ወይም ያለመጠቀም ሁኔታ ነው ካልሆነ ለሁላችንም በእጃችን ላይ ያለ ትልቅ ነገር ነው:: ዛሬ ላይ ሆነን የትላንት ስራዎችን

እናሻሽላለን፣ አዲስ ስራዎችን እንፈጥራለን፣ ነገ የምንሰራቸውን ስራዎች ዝግጅት አናደርጋለን:: ትላንት የሰራናቸውም ስራዎች ሆነ ነገ ላይ ልንሰራቸው ያሰብናቸው ከዛሬ ጋር ሲፃፀሩ፣ ዛሬ የበለጠ ትኩረት ሊሰጠው ይገባዋል:: ዛሬ የትላንትን ታሪክ ጥሩ ከሆነ የማሻሻል ጥሩ ካልሆነም የመቀየር አቅም አለው:: ይህም ብቻ ሳይሆን ነገ ላይ ሊኖረን የሚችልን ታሪክም የመስራት ዕድልም አቅምም አለው::

አዎ ዛሬ አሁን ላይ ፊት ለፊታችን ያለ ጊዜ ነው:: የዛሬን ጊዜ ካልተጠቀምን ሲያልፍ ያ ጊዜ ትላንት ይሆናል:: የዛሬ ጊዜ ከትላንት ሙሉ በሙሉ እና በትልቁ የሚለየው የዛሬን ጊዜ በተመለከተ መለወጥ የምንፈልገው ነገር ካለ ማድረግ የምንችለው ነገር ሁሉ ማድረግ መቻላችን ነው:: ይህንን ዕድል የምናገኘው ዛሬ ላይ ብቻ ነው:: የትላንትም የነገም ጊዜዎች ግን ያኄ ዕድል የላቸውም::

**<u>ነገ</u>**

የነገ ጊዜዎች ሁላችንም ብንሆን እኛ የምንፈልገውን ዓይነት ጊዜ ለመፍጠር የምናልምበት ጊዜ ነው:: ለምሳሌ ዛሬ እነዚህን ነገሮች አድርገን ነገ እነዛ የምንፈልጋቸውን ነገሮች እናገኛለን ብለን እናልማለን ፣ ነገ ላይ ለሚጠናቀቁ ስራዎች ዛሬ ላይ እቅድ እናወጣለን፣ የመሳሰሉት:: ለነገ የምናስባቸው፣ የምናልማቸው እና እንዲሆኑ የምንፈልጋቸው ነገሮች ዛሬ ስላሰብናቸውና ስንለምናቸውም የምንከፍለው ምንም ነገር የለም:: ግን ስላሰብንና ስላለምን እነሱን ለማሳካት ዛሬ ላይ ሆነን እንሰራለን እንጂ::

ነገ ገና ያልመጣ ጊዜ ነው:: ነገ ሲመጣ ዛሬ ላይ ሆነን መለወጥ የምንፈልገውን ካልለወጥን ያ የሚመጣው ቀን ከዛሬ ጋር ተመሳሳይ ቀን ነው የሚሆነው:: ግን እንደፈለግን ማሰብ፣ ማለም እና ራዕይ ለነገ መያዝ እንችላለን:: ያንን የታሰበ ነገር እውን ለማድረግ ግን ዛሬ ላይ ጠንክሮ መስራትን ይጠይቃል::

ስለዚህ ትላነት፣ ዛሬ እና ነገ የተያያዙ እና ሊነጣጠሉ የማይችሉ ናቸው::